# ቤተክርስቲያንን በኃይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት

# መምራት

## ለመምራት መማር

## የተተኪ መሪ ስልጠና

Dynamic Churches
International

Dynamic Churches
International

# ቤተክርስቲያንን በኃይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት መምራት

## ለመምራት መማር
## የተተኪ መሪ ስልጠና

*Dynamic Churches International*

**International/Canadian Address:**
164 Stonegate Close,
Airdrie, Alberta, Canada, T4B 2V2
(403) 912-4438
dcimiddleton@shaw.ca
www.dynamicchurches.org

እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

Copyright © 2009 Dynamic Churches International.
All rights reserved including translation.
ከዚህ መጽሐፍ ማንኛውንም ክፍል መግለበጥም ሆነ ማባዛት ያለ ጽሑፍ ፍቃድ የተከለከለ ነው። ይሁንና ከዚህ መጽሐፍ በግል ለመጠቀም ቅያችን መገልበጥ ይቻላል።

# ማውጫ


**መግቢያ** 1

**ክፍል አንድ - አቀባበል**
- የመቆጣጠሪያ ቅፅ 3
- ዓላማ እና የስራ ዝርዝር 5
- አምስቱ ዋና የሕይወት ቡድን ዓላማዎች 8
- የማካፈል ጥያቄዎችን የመጠየቂያ መንገድ 9

**ክፍል ሁለት - የእግዚአብሔር ቃል**
- ስም መቆጣጠሪያ 13
- የትንንሽ ቡድኖች ጠቀሜታ 15
- የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ሚና ለቃል እውቀት 18

**ክፍል ሦስት - አምልኮና ፀሎት**
- ስም መቆጣጠሪያ 23
- የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን 25
- ትርጉም ያለው የሕብረት ጸሎት ስለማድረግ 27

**ክፍል አራት - ምስክርነት**
- ስም መቆጣጠሪያ 31
- የአገልጋይ መሪ ልብ 33
- ሰዎች ሰዎችን ሲደርሱ 36
- ለጠፉት ነፍሳት የመጸለያ መንገድ 38

**ክፍል አምስት - ሰዎችን በወንጌል መማረክ**
- ስም መቆጣጠሪያ 39
- የህይወት ቡድናችንን ማባዛት 41
- ለማጅ መሪህን መምረጥ 43
- ሰዎችን በወንጌል መማረክ - ለዓለማችን ራዕይ 43
- ሰዎችን በወንጌል መማረክ - ምስክርነትን የህይወት ዘይቤ ማድረጊያ መንገድ 46

**ክፍል ስድስት - ስራ (አገልግሎት)**
- ስም መቆጣጠሪያ 49
- አስተማማኝ አካባቢን መፍጠር 51
- ሌሎችን እንዲያስተምሩና እንዲያሰለጥኑ መሪዎችን ማሳደግ 52
- የመንፈሳዊ ስጦታን መለየት 55

**የምስክር ወረቀት** 69

# የመምራት መማር የተተኪ መሪ
# ስልጠናን የመጠቀሚያ መንገዶች

እነዚህ ክፍለግዜዎች አምስቱ የሕይወት ቡድን ዓላማዎችን ዕውን እንድታደርግ ያዘጋጁሃል። መሪው የእርሱን/የእርሷን ተተኪ መሪ (በማሰልጠን ላይ ያለ መሪ) ለማሰልጠን እንዲጠቀምበት /እንድትጠቀምበት ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

**ተተኪ መሪ፡-**

- መሪውን ከመገናኘቱ አስቀድሞ (ብዙውን ጊዜ ለአንድ ሰዓት በወር አንድ ጊዜ) ማጥናትና መዘጋጀት ይኖርበታል።
- ግልፅ የሆነ ግንዛቤ እንዳለ ለማረጋገጥ ከመሪው ጋር በአንድነት በመሆን የስልጠናውን ይዘት መከለስና መወያየት ይኖርበታል።
- በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ የተማራቸውን መርህዎች በቀጣዩ ሳምንት ባለው የሕይወት ቡድን ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል። አብዛኞቹ እነዚህ መርህዎች በህብረቱ ውስጥ በቀላሉ ተግባራዊ ይሆናሉ። አንዳንዶቹም ቡድኑን ለማስተማር በጣም ጠቃሚ ናቸው።በህብረቱ ውስጥ ጊዜ እንዲኖርህ ታደርጋለህ አልያም የመፅሀፍ ቅዱስ እውነታዎችን ለማስተማር የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜውን ትጠቀማለህ።

ከዚህ የሚከተለው የተተኪ መሪ ማሰልጠኛው እንዴት ሰዎችን ለማሳደግ በተያዘው ስልት ውስጥ እንደሚዛመድ ያሳያል

# የሰዎች ማሳደጊያ ስልት

| ዓላማ | የሕይወት ቡድን | መሪና ለማጅ | አሰልጣኝና መሪ |
|---|---|---|---|
| 1. **አቀባበል**<br>ፍቅር/ማካፈል | እርስ በእርስ መተዋወቅ | ወዳጅነትን ማጎልበት | ለቤተክርስቲያንና ለህብረተሰቡ ያለውን ሸክም ማካፈል |
| 2. **አምልኮ**<br>መዝሙር፣ መፀለይና ማመስገን | እግዚአብሔርን ማምለክ ለእርስ በእርስና ድነትን ላላገኙ ጓደኞች መጸለይ | **እግዚአብሔርን ማምለክና ለእርስ በእርስ፣ ለቡድኑ አባላት፣ ለወንጌል ስርጭትና ለእድገት መፀለይ** | እግዚአብሔርን ማምለክና ስለተተኪ መሪው፣ ስለ ቡድኑ አባላትና ስለተወለዱ አዳዲስ ቡድኖች ማመስገን |
| 3. **መማረክ**<br>መድረስ | ክርስቶስን ለመመስከር መማር፣ አዳዲስ ሰዎችን ለመድረስ መጸለይ | **የህብረቱን አባላት ክርስቲያን ላልሆኑ ጓደኞቻቸው እንዲፀልዩና እንዲደርሷቸው ማዘጋጀትና ማበረታታት** | የወንጌል ስርጭትን በህብረቱ ልዩ ጊዜዎችና በቤተክርስቲያን ደረጃ ማቀድ |
| 4. **የእግዚአብሔር ቃል**<br>መማር /መፅሀፍ ቅዱስ ጥናት «የማሰልጠንችሎታ» | የክርስትናን ህይወት የመኖሪያ መንገዶች | **ቡድናችንን የማሳደጊያና ማብዢያ መንገዶች** | ቡድንህን የምትመራበት መንገድ |
| 5. **ስራ**<br>ማገልገል/<br>መሪ እድገት<br>•አንድ ለአንድ | ዳይናሚክ መሰረታዊ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ | **ዳይናሚክ ማካፈልን ለመምራት መማር** | ቡድንህን መምራት |
| •**ትንሹ ቡድን** በአንድነት እንደ ህብረት | የትንሹ ህብረት ጊዜ | **በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወርክሾፕና አመታዊ የጾምና የጸሎት ጊዜ** | በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትና ዓመታዊ የጾምና የጸሎት ጊዜ |

# አጠቃላይ የሰዎች ማሳደጊያ ስልት

| ዓላማ | የህይወት ቡድን | መሪና ለማጅ | አሰልጣኝና መሪ | መጋቢና መሪዎች | ቤ/ክ ለቤ/ክ ክትትል |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. **አቀባበል**<br>ፍቅር/ማካፈል | እርስ በእርስ መተዋወቅ | **ወንድማማችነትን/ ጓደኝነትን ማጐልበት** | ለቤተክርስቲያንና ለህብረተሰቡ ያለውን ሸክም ማካፈል | ሰዎችን ለመድረስ ለሚደረገው አገልግሎት ራዕይንና ጥልቅ ስሜትን መፍጠር | - መጋቢያንን ሁሉ መተዋወቅ<br>- ለአንድነታችንን ዋጋ መስጠት<br>- እርሰ በእርስ መገላገልና ቤ/ክ ከቤ/ን ጋር |
| 2. **አምልኮ**<br>መዝሙር፣ መፀለይና ማመስገን | እግዚአብሔርን ማምለክ ለእርስ በእርስና ድነትን ላላገኙ ጓደኞች መጸለይ | **እግዚአብሔርን ማምለክና ለእርስ በእርስ፣ ለቡድኑ አባላት፣ ለወንጌል ስርጭትና ለእድገት** መጸለይ | እግዚአብሔርን ማምለክና ስለተተኪ መሪው፣ ስለ ቡድኑ አባላትና ስለተወለዱ አዳዲስ ቡድኖች ማመስገን | እግዚአብሔርን ማምለክና ለመሪዎች ለወደፊት ምሪቱ ማህበረሰቡን ለመድረስ ለቤተክርስቲያን ተከላና ለመስፋፋት መጸለይ፡፡ | እግዚአብሔርን ማምለክና ስለሚከተሉት ጉዳዮች ማመስገን<br>- በእርስ በእርስ አገልግሎቶች<br>- ለቤተክርስቲያን አንድ መሆን<br>- ለመስፋፋት/ሌሎች ቤ/ክ ለማዘጋጀት<br>- ከተማን/አካባቢን ሙሉ በሙሉ ለማውረስ የፀሎት ስልት |
| 3. **መማረክ**<br>መድረስ | ክርስቶስን ለመመስከር መማር አዳዲስ ሰዎችን ለመድረስ መጸለይ | **የህብረቱን አባላት ክርስቲያን ላልሆኑ ጓደኞቻቸው እንዲፀልዩና እንዲደርሷቸው ማዘጋጀትና ማበረታታት** | የወንጌል ስርጭትን በህብረቱ ልዩ ጊዜዎችና በቤተክርስቲያን ደረጃ ማቀድ | - በተለዩ ጊዜዎች ቤ/ክ አቀፍና ከተማ አቀፍ የወንጌል ስርጭት እቅድ ማውጣት<br>- ባህል ዘለል አገልግሎት<br>- የአጭር ጊዜ የአገልግሎት ኘሮጀክት | - ለአካባቢ ወይም ለከተማ ወንጌል ስርጭት ስልት ዕቅድ ማውጣትና ለተግባራዊነቱ መተባበር<br>- በአንድ ሌላ ከተማ/የአለም ክፍል መኖር |
| 4. **የእግዚአብሔር ቃል**<br>መማር/መፅሀፍ ቅዱስ ጥናት<br>«የማሰልጠን ችሎታ» | የክርሰትናን ሕይወት የመኖሪያ መንገዶች | **ቡድናችንን የማሳደጊያና ማባዣያ መንገዶች** | ቡድንህን የምትመራበት መንገድ | - ራዕዩን ማስፋፋት<br>- ታላቁን ተልዕኮ ለመፈፀም መፅሐፍ ቅዱሳዊ ስልትን ማዘጋጀት | ስለ ከተማችን፣ ሀገራችንና ዓለማችን እግዚአብሔርን ማመን |
| 5. **ስራ**<br>መሪ እድገት<br>• **አንድ ለአንድ** | ዳይናሚክ መሰረታዊ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ | **ለመምራት በሐይል የተሞላ ማካፈል** | ቡድንህን መምራት | የተረጋገጠለት/የተመሰከረለት ስልጣኝ የእግዚአብሔር ራዕይ መያዝ | - የህይወት በህይወት ክትትል<br>- የእግዚአብሔርን ራዕይ መያዝ<br>- ሌሎች አብያተክርስቲያናትን ማዘጋጀት |
| • **ትንሹ ህብረት**<br>በአንድነት እንደ ህብረት | የትንሹ ህብረት ጊዜ | **በተቀጣጣይ እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወርክሾኘና አመታዊ የፃምና የፀሎት ጊዜ** | በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትና ዓመታዊ የፃምና የፀሎት ጊዜ | - ቡድኑን መገንባት<br>- በሱስ ለተያዙ ሰዎች አገልግሎት<br>- ዓመታዊ የፃምና የፀሎት ግዜ | - ከተማችንን፣ ከሀገራችን ባሻገር ለመድረስ ስልት መንደፍ<br>- በከተማ አቀፍ የመዘጋጃ ልዩ ጊዜ መተባበር |

# *የሕይወት ቡድኑ የእርስ በእርስ ግንኙነት*

## *መግቢያ*

የቤተክርስቲያናችን የሕይወት ቡድን አገልግሎት በኤፌሶን 4÷12 ***«ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅድሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን»*** በሚል የተሰጠውን ኃላፊነት ለመተግበር አይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡ መጋቢው በራሱ የአካሉን ሁሉ ፍላጐት ማሟላት አይችልም፡፡ እርሱና እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያናችን የሰጠን ሌሎች መሪዎች እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል መነሳሳት የሌለበትን ሚና አስወግዶ እነርሱ የሚመኙትን ዓይነት አገልጋይ እንዲሆን ለማሰልጠን፣ ለማዘጋጀት፣ እና ለማሰማራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ኢየሱስ አስራሁለቱን በሚያሰለጥንበት ሁኔታ ውስጥ የትንሽ ቡድን ምንነትን አሳይቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም በርካታ የአንድ ለአንድ ጊዜን ከደቀመዛሙርቱ ጋር አሳልፏል፡፡ እነዚህ ደቀመዛሙርቶችም የእርሱን አርአያ በመከተል የቀድሞዋን ቤተክርስቲያን ጀምረዋት ነበር፡፡ እየተገናኙ እርስ በእርስ ህብረት ያደርጉ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የቤተክርስቲያን ህንፃ ስላልነበረ በአይሁድ ሙክራብና በትንንሽ የቤት ለቤት ቡድኖች ውስጥ ይሰበሰቡ ነበር፡፡ (የሐዋ. 5÷42፣2÷41-47 እና 20÷20 ተመልከት) ውጤቱም በጣም ኃይለኛ ነበር፡፡

***«ጌታም የሚድኑትን በቁጥራቸው ላይ ዕለት በዕለት ይጨምር ነበር፡፡» የሐዋ 2÷47***

ዛሬ እንደ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ጌታን ለማምለክ እንሰባሰባለን፡፡ ስለተትረፈረፈው በረከቱ ጌታን እናከብራለን ደግሞም ከእግዚአብሔር ቃል አብረን እንማራለን፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል እያጠኑና በመቀራረብና በተጠያቂነት መንፈስ አብረው እየፀለዩ ሕይወታቸውን ለማካፈል በትንሽ ቡድን ውስጥ የሚሰባሰቡ ሰዎች ያስፈልጋሉ፡፡ አንዳችን አንዳችንን ስንንከባከብና አንዳችን በአንዳችን ሕይወት ስንገባ እውነተኛ ሕብረት በሕይወት ቡድኑ ውስጥ ይከሰታል፡፡

***በህብረት ማድረግ የሕይወት ቡድኑ ዓላማ አይደለም፤ ነገር ግን ዋናው ክፍልና በእርግጥም ተጨማሪ ውጤት ነው፡፡ የሕይወት ቡድኖች ለወንጌል ስርጭት እና ለደቀመዝሙርነት እንደ ማስፈፀሚያ ሆነው መታየት አለባቸው፡፡ አዳዲስ ሰዎችን ከቤተክርስቲያን ቤተሰብ ጋር በማገናኘት እንዲቀላቀሉ ይረዳሉ፡፡***

ክርስቲያኖች ሲዘጋጁና የራሳቸውን ህይወት በአገልግሎት በሌሎች ህይወት ውስጥ ለማባዛት በሚጠመዱበት ጊዜ በመንፈስ ያድጋሉ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ ያላቸው ፍላጐት እና የእርስ በእርስ ጸሎትና እንክብካቤ ይጨምራል፡፡ ብዙዎች እንደሚያምኑት ቃሉን ማስተማር አገልግሎትንና የወንጌል ማሰራጨትን ያስገኛል፡፡ ከልምድ እንደሚታየው ማገልገል በእግዚአብሔር ቃል የመማር ፍላጐትን ይፈጥራል፡፡ ይኸም ደግሞ የተለወጡ ሕይወቶችን ያስገኛል፡፡ መሪነትንም በተግባር ስታሳይ በቡድንህ ውስጥ አዳዲስ መሪዎች ያድጋሉ፡፡ የሕይወት ቡድንህ ሲያድግና የሚባዙ ክርስቲያኖች ሲያድጉ አዳዲስ ቡድን ታቋቁማለህ፡፡

ደቀመዝሙርነት የዕድገት ቁልፍ ነው፡፡ ደቀመዛሙርትን ለማሳደግ የሚበልጠው ውጤታማ መንገድ የአንድ ለአንድ መንገድ ነው፡፡ የአንድ ለአንድ ስልጠና ምናልባትም የህይወት ቡድንህ በጣም ጠቃሚ የእርሰ በእርስ ግንኙነት ነው፡፡ በቡድንህ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው በዳይናሚክ መሰረታዊ (4 ትምህርቶች) እንዲሰለጥን አጋጣሚውን ያገኛል፡፡ እነኚህ የአንድ ለአንድ ክፍለጊዜዎች ከትንሹ ቡድን የስብሰባ ጊዜ ውጪ ይካሄዳሉ፡፡ በአመቺ ጊዜና ቦታ አንድ የሰለጠነ ሰው ከሌላው ሰው ጋር ይገናኛል፡፡ ወንድ ወንድን ሴት ሴትን ያሰለጥናል፤ ከዚህም ደቀመዛሙርት መሪዎች ይኀለብታሉ፡፡

# ለመምራት መማር
## ክፍለጊዜ አንድ
# አቀባበል

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው፡፡

**ከመሪዎች ቡድንህ ጋር ከመገናኘትህ በፊት**

☐ 1. **የቤተክርስቲያን ዓላማ ፣ የህይወት ቡድናችን አላማና የህይወት ቡድናችን ግቦች** በሚሉት ርዕሶች ስር የሰፈሩትን ፅሁፎች አንብብ፡፡ ይህ አገልግሎት እንዴት ህይወት እንደሚለውጥና ማህበረሰባችንን ለመድረስ እንዴት እንደሚያዘጋጀን ያለህን ዕምነት ለመግለፅ ተዘጋጅ፡፡

☐ 2. **የቡድኑ አጠቃላይ ይዘትና የስራ መመሪያዎች** የተሰኙትን ክፍሎች እያቸው፡፡ የአንተን የኃላፊነት ቦታ በመለየት ለመሪህ ግለፅለት፡፡

☐ 3. የህይወት ቡድናችን **አምስት ዋና ዓላማዎች** ምንድን ናቸው? ለምንድን ነው **የእንግዶች አቀባበል** (ሰላምታ፣ ማካፈልና መዝናናቶች) በጣም ጠቃሚ የህይወት ቡድናችን ግዜ የሆነው?

☐ 4. **ጥሩ የማካፈል መጠይቆችን የመጠየቂያ መንገዶች** የሚለውንና የጥያቄዎችን ዝርዝር አንብብ፡፡ **የማካፈል ጊዜ ሦስቱ አማራጮችን** በቃልህ ለመናገር የተዘጋጀህ ሁን፡፡ በዚህ ወር
ለየሣምንቱ የሚሆን አንድ ጥያቄ ምረጥ፡፡

**ከመሪህ ጋር በመሆን የሚፈፀም**

☐ 5. እርስ በእርሳችሁ ተዋወቁ፡፡ አንዳችሁ ለአንዳችሁ እንደሚያገባችሁ አሳዩ፡፡

☐ 6. ከላይ ከ 1-4 ያሉትን ነጥቦች ከተወያያችሁ በኋላ (✓) ምልክት አድረጉበት

**በዚህ ወር ከቡድናችን ጋር ልንካፈላችሁ የተያዙ ዕቅዶች**

☐ 7. የቤተክርስቲያናችንን ዓላማ የሕይወት ቡድናችንን ዓላማንና የሕይወት ቡድናችንን ግቦች መከፋፈል፡፡ ቀን ______________________ ማን ________________________

☐ 8. የቡድኑን አጠቃላይ ይዘትንና ለእያንዳንዱ ክፍል ማን ኃላፊነቱን እንደሚወስድ ግለጹ፡፡ ቀን ______________________ ማን ______________________

☐ 9. ማን በየሳምንቱ የሚደረገውን የማካፈል ጥያቄ እንደሚመራ ወስኑ
ስም ______________________

**በፀሎት መዝጋት**

☐ 10. ለእርስ በእርሳችሁና ለቡድናችን አባላት መፀለይ

☐ 11. የክፍለግዜ ሁለት የመዘጋጃ ስራን በጥንቃቄ መመልከት

☐ 12. ለሚቀጥለው ለመምራት መማር ክፍለ ግዜ ቀን ________________________
ሰዓት ________________________ ቦታ ________________________ መመደብ።

☐ 13. ለሚከተለው ዳይናሚክ ማካፈል ስልጠናችን ቀን ________________________
ሰዓት ________________________ ቦታ ________________________ መመደብ።

# ቤተክርስቲያናችን ዓላማ

የመጨረሻው የቤተክርስቲያናችን ዓላማ የታላቁ ተልዕኮ ነው፡፡ (ማቴ 28÷18-20) መላው ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ሰምቶ ምላሽ እስኪሰጥ ድረስ ደቀመዛሙርትን የሚያፈሩ ደቀመዛሙርት እናበጃለን፡፡ በቀላሉ ለማስቀመጥ፣ ደቀመዛሙርት ኢየሱስ እንደኖረው ለመኖር የሚፈልጉና ከእግዚያብሔር ጋር ባላቸው የህይወት እርምጃ በአያሌው የሚደሰቱና በክርስቶስ ኢየሱስ ስላገኙት አዲስ ህይወት ለሌሎች አለመናገር የማይሆንላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ የሕይወት ቡድን አገልግሎት እያንዳንዱን የቤተክርስቲያናችንን አባል እንደዛ ያለውን ሰው እንዲመስል ለመገንባት እንዲችል ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ስልጠና መሪ ለመሆን እድሉን አግኝተሃል፡፡

# የሕይወት ቡድናችን ዓላማ

በፍቅርና እንክብካቤ ወደ ክርስቶስ የሚያድግ፣ የሚዋደድና የሚተሳሰብ ብሎም የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች የሚያካፍል ቤተሰብ መሆን፡፡

## የሕይወት ቡድናችን ግቦች

- እያንዳንዱን ሰው መውደድና ተቀባይነት እንዲሰማው ማድረግ
- የእያንዳንዱን ሰው አካላዊ፣ ስነልቦናዊና መንፈሳዊ ፍላጐት ማሟላት
- በ6 ወር ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ከ 6-8 የሚደርሱ ትርጉም ያላቸው ግንኙነቶች በቡድኑ ውስጥ ካሉ ሌሎች ሰዎች ጋር እንዲያሳድግ ማድረግ ፡፡
- በሌሎች አገልግሎቶች ውስጥ እንዲገቡ ማደፋፈር፡፡ ለምሳሌ ማህበራዊ ጉዳዩች ፣ አምልኮ፣ የሰንበት ትምህርት
- እያንዳንዱን ሰው የራሱን መንፈሳዊ ስጦታ ለይቶ በማወቅ፤ ሌሎችን ለማገልገል እንዲጠቀምበት መርዳት፡፡
- እያንዳንዱን ሰው የውሃ ጥምቀት የወሰደና የቤተክርስቲያናችን ንቁ ተሳታፊ አባል ማድረግ
- እያንዳንዱን ሰው በዳይናሚክ መሰረታዊ፣በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግና በዳይናሚክ ማካፈል ማሰልጠን፡፡
- በየ6 ወር አንድ አዲስ ቤተሰብን ወደ ቤተክርስቲያን መጨመር
- ለማጅ መሪዎችን ማሳደግና በየ6 ወር አንድ አዲስ የህይወት ቡድን መመስረት
- ህብረተሰባችንን ለክርስቶስ ለመድረስ እንዲቻለን በቂ የህይወት ቡድኖችን መመስረት

## የቡድኑ ይዘት

ይህ በየሳምንቱ ሊለያይ ይችላል፤ ነገር ግን የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡፡
**አቀባበል** (15-20 ደቂቃ)

- መክፈቻ ፀሎት
- ማካፈል፣ ምስጋናና ሪፖርት

**አምልኮ** (15-20 ደቂቃ)

- መዝሙር መዘመር ወይም ከመዝሙር መፅሀፍት ማንበብ

**ወንጌል ስርጭት** (20-30 ደቂቃ)

- በተፅዕኖ ክልልህ ውስጥ ስላለው ለውጥ ሪፖርት አቅርብ፡፡
- ለወንጌል ስርጭት ስልቶችንና ዝግጅቶችን አቅድ
- በአንድ ለአንድ ስልጠና ውስጥ የተያዙትን ሰዎች ለውጥ መመልከት፡፡

**የእግዚያብሔር ቃል** (20-30 ደቂቃ)

- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
- ጸሎት

*መዝጊያ*

- ማስታወቂያዎችና ጸሎት
- መዝናኛዎች /ማነቃቂዎች/

*ስራ*

- ለደቀመዝሙርነትና ለመሪ ግንባታ የአንድ ለአንድ የስልጠና ክፍለግዜዎች (በሳምንቱ ውስጥ)

  እነዚህን መመሪያዎች መከተል ውጤታማ የህይወት ቡድን እንዲኖርህና እራስህም ሌሎችን

  በማሰልጠን ተመሳሳይ ስራ እንዲሰሩ ያስችልሃል።

- የፈጠራ ስራ ይኑርህ፤ ግልፅ ሁን፤ የሚያዝናኑ ነገሮችም ይኑርህ፤ አስታውስ ግብህ /ግባችሁ/በፍቅርና በመቀባበል በሆነ ህብረት ውስጥ ህይወታችሁን እርስ በእርሳችሁ መከፋፈል ነው። እየተጠቀምክበት ያለው ነገር የሚተላለፍ እንደሆነ እርግጠኛ ሁን። ምክንያቱም በቡድንህ ውስጥ የምታደርገው በአዲሱ ቡድን ውስጥ የሚዛመት ይሆናል።

በርካታ ሰዎች የባለቤትነትን ስሜት ይሰማቸው ዘንድ፤ የህይወት ቡድንህን የስራ ኃላፊነቶች ከፋፍለህ አስቀምጥ ። መሪዎችም በልምምድ ውስጥ ያድጋሉ።

# የስራ ምድብ

## መሪ

**ኃላፊነቶቹ**

1. የእሁድ የአምልኮ አገልግሎትን በታማኝነት መካፈል።
2. ለጌታ ስራ በታማኝነት አስራት ማውጣት።
3. በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወርክሾፕን መካፈል።
4. የሕይወት ቡድንህን መምራት
5. ዕጩ የቡድን አባላትን መጐብኘት ወይም ደውሎ ማግኘት
6. ከእያንዳንዱ የሕይወት ቡድን ክፍል ጊዜ በፊት ከተተኪ መሪውና ከአስተናጁ ጋር በመሆን ማቀድና መጸለይ
7. የመፅሀፍ ቅዱሱን ጥናትና ማዛመድ መምራት( ወይም ለማጅ መሪውን መመደብ)
8. የሕይወት ቡድኑን ጊዜ መዝጋት

   ሀ/ ማስታወቂያዎችን መናገር

   ለ/ በጸሎት መዝጋት
9. ለእያንዳንዱ ሳምንት ለወንጌል ስርጭት ራዕይንና ማበረታቻን መስጠት።
10. ተተኪ መሪህን የአንድ ለአንድ ስልጠናን በሚያስተባብርበት ጊዜ መርዳት።
11. በዳይናሚክ ማካፈል ተተኪ መሪህን ማሰልጠን (የወንጌል ጉብኝት ቀጠሮ በወር አንዴ) ።
12. ተተኪ መሪህን በ «**መምራትን መማር**» በወር አንዴ ማሰልጠን።
13. ከአሰልጣኝህ ጋር በወር አንዴ መገናኘት።
14. የመሪዎች ቡድንን ከአሰልጣኝህ ጋርና ከሌሎች የቡድን መሪዎች ጋር በየ4 ሳምንት መካፈል።
15. የአመቱን የመሪዎች የጾምና የጸሎት ጊዜ መካፈል።

# ተተኪ መሪ (በስልጠና ላይ ያለ መሪ)

**ኃላፊነቶቹ**

1. የእሁድ የአምልኮ አገልግሎትን በታማኝነት መካፈል፡፡
2. ለጌታ ስራ በታማኝነት አስራት ማውጣት፡፡
3. የሕይወት ቡድን መሪዎች ስልጠናን ማጠናቀቅ፡፡
4. የሕይወት ቡድን መሪውን መርዳት፡፡
5. የሕይወት ቡድን አባል ዕጩዎቹን መጐብኘት ወይም ስልክ ደውሎ ማግኘት፡፡
6. ከእያንዳንዱ ስብሰባ በፊት ከመሪህና ከአስተናጋጁ ጋር መገናኘት
7. የሕይወት ቡድኑን ጊዜ መጀመር
    - እንግዶችን ማስተዋወቅና ለእያንዳንዱን ሰው ሰላምታ ማቅረብ፡፡
8. የማካፈል ጊዜውን መምራት (የናሙና የማካፈል ጥያቄዎችን ተመልከት) ወይም ሌላ ሰው መድብ፡፡
9. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜውንና የውይይቱን ጊዜ አልፎ አልፎ በመሪው ጥያቄ መሰረት መምራት፡፡
10. የፀሎት ጥያቄዎችን፣ ቤተክርስቲያን አቀፍ ክስተቶችንና ሌሎች መረጃዎችን እንዲለዋወጡ ማድረግ (አልፎ አልፎ ሌላ ሰው ሊመራ ይችላል) እና የፀሎት ጊዜውን መምራት፡፡
11. የቡድኑን አባላት በአንድ ለአንድ ደቀመዝሙርነት ማቀናጀት፡፡
12. ለመምራት መማር የተሰኘውን ስልጠና ለመውሰድ በወር አንዴ ከመሪህ ጋር ተገናኝ፡፡
13. የዳይናሚክ ማካፈል ስልጠናን ለመውሰድ በወር አንዴ ከመሪህ ጋር ተገናኝ
14. የአመቱን የመሪዎች የጾምና የጸሎት ጊዜን መካፈል፡፡

# እንግዳ ተቀባይ

**ኃላፊነቶቹ**

1. የእሁድ የአምልኮ አገልግሎትን በታማኝነት መካፈል፡፡
2. ለጌታ ስራ በታማኝነት አስራት ማውጣት፡፡
3. ከሕይወት ቡድኑ የመገናኛ ሰዓት በፊት ከተተኪ መሪውና ከአስተናጁ ጋር በመሆን መጸለይ
4. ተስማሚ የስብሰባ ቦታና ወንበሮችን በክቡ ማዘጋጀት
5. የህፃን መቀመጫ ካስፈለገ ማዘጋጀት
6. እንግዶችን ሰላም ለማለት ይረዳ ዘንድ ምግቦችን ከስብሰባው ሰዓት በፊት ማሰናዳት፡፡
7. የራሳቸውን መፅሀፍ ቅዱስና እስክሪቢቶ ረስተው ለሚመጡ ይረዳ ዘንድ ተጨማሪ ማዘጋጀት፡፡
8. እውነተኛ የሆነ ፍላጐትን ለእያንዳንዱ እንግዳ ማሳየትና ሞቅ ባለ መልካም ሰላምታ ሰላም ማለት፡፡
9. የሳምንቱን የተገኙ ሰዎች መቆጣጠሪያ ቅፅ በመጠቀም የተገኙትን ሰዎች መቆጣጠር፡፡
10. በትንሹ ቡድን ጊዜ የእያንዳንዱን በአንድ ለአንድ ስልጠና ውስጥ በሚያሳየው እድገትና እያንዳንዱን ደረጃ በማጠናቀቁ ዕውቅና ሰጥቶ ማመስገን፡፡

# አምስቱ የሕይወት ቡድኖች ዋና ዓላማዎች

***አቀባበል፣ አምልኮ፣ መማረክ፣ የእግዚአብሔር ቃልና ማገልገል*** አምስቱ ዋና የህይወት ቡድኖች ዓላማዎች ናቸው፡፡ በእንዳንዱ ክፍለ ጊዜዎች ከእነዚህ በአንዱ ላይ እናተኩራለን፡፡

## አቀባበል

አፍቃሪ፣የሚያካፍልና ተንከባካቢ ሕብረት ለማጎልበት

በሕይወት ቡድን ውስጥ እያንዳንዱ ሰው በመደበኛ ሁኔታ ሊሰማ፣ክትትል ሊደረግለትና ሊጸለይለት ይችላል፡፡ ይሄ የባለቤትነት ስሜትን የሚፈጥር አንድን አውድ ይፈጥራል፡፡እውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር ለመሆን እርሃብንና ጥማትን የሚያመጣ ክፍት የሆነ የመንፈሳዊ ቤተሰብ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል፡፡

***«እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀመዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ»       ዮሐንስ 13÷35***

***«ፍጹም ትሑታንና ገሮች ሁኑ፤ እርስ በእርሳችሁም በፍቅር ተቻቻላችሁ ትእግስተኞች ሁኑ፡፡በሰላም ማሰሪ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ፡፡»    ኤፌሶን 4÷2፣3***

***«እግዚአብሔርን ወንጌል ብቻ ሳይሆን ሕይወታችንን ጭምር ልናካፍላችሁ ደስ እስከሚለን ድረስ ወደድናችሁ፤ምክንያቱም እናንተ በእኛ ዘንድ ተወዳጆች ነበራችሁ፡፡»*** 1 ተሰሎንቄ 2÷8

### አቀባበል

***ሰላምታ ማቅረብ፡-*** (እንግዳ ተቀባይ)

- እያንዳንዱን ሰው በጓደኝነት አኳሃን ሰላምታ አቅርብለት
- ሁሉንም አዳዲስ ሰዎችንና ሁሉንም ነባር የጉባኤው ተካፋዩችን መዝግብ፡፡
- በጸሎት ኘሮግራሙን ክፈት

***ማካፈል፡-*** (ለማጅ መሪ ወይም መሪ)

- *መሪዎች አዳዲስ ሰዎችን ለመርዳትና በቡድኑ ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ ሰው ማስተዋወቃችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡*
- *መደበኛ የማካፈልህን በሰዓቱ መጀመርህን እርግጠኛ ሁን፡፡*
- ቡድኑን በአንድነት ጥራና ከአንድ ተጨማሪ መቀመጫ ጋር በትንሹ በክብ አስቀምጣቸው
- *መሪዎች የቡድኑን አጠቃላይ ሁኔታ ግልጽና እውነተኛ በመሆን ይወስኑ፡፡*
- አንድ የማካፈል ጥያቄ ጠይቅ፡፡
- አልፎ አልፎ ለምስክርነት አጋጣሚውን መስጠት

***ማስታወሻ፡- ለአዳዲስ ወይም አይን አፋር ለሆነ ሰዎች ተጠንቀቅላቸው፡፡ እናንት መሪዎች አሳትፉ፤ ነገር ግን አትቆጣጠሩ፡፡***

***መዝናኛዎች (እንደአስፈላጊነቱ)፡-*** እንግዳ ተቀባይ

- ከቡድንህ ጊዜ በኋላ፣ ጉባኤውን በማዝናናት ለማገልገል ትፈልግ ይሆናል፡፡ በፋክክር አታድርገው፣ **በጣም ቀለል አድርገው፡፡**

# ጥሩ የማካፈል ጥያቄዎችን መጠየቂያ መንገዶች

የሚያስደስት የማካፈል ግዜ ለቡድንህ በጣም አስፈላጊ ይሆናል። ምክንያቱም ሰዎችን ዘና እንዲሉና እርስ በእርሳቸው እንዳይከባበዱ ይረዳቸዋል። ሰዎች በማካፈሉ ጊዜ ቢሳተፉ፣ በመፅሀፍ ቅድስ ጥናቱና በፀሎት ጊዜ የበለጠ ይሳተፋሉ።

አንድ ሰው ጥሩ የማካፈል ጥያቄን አስቀድሞ ተዘጋጅቶ እንዲመጣ መድብ። የማካፈል ጥያቄዎቹ ዝርዝር ተስማሚ ጥያቄ እንኪመርጡ ሊያግዛቸው ይችላል። በማካፈሉ ጊዜ ዘና በል። የደስታና የጨዋታ ጊዜ አድርገው።

ሦስት አማራጮችን ማቅረቡ ጥሩ ይሆናል።

1. የታሰበውን ጥያቄ ለማካፈል ጊዜ መምረጥ።
2. ባሳለፉት ሳምንት ተከስቶ ስላለው ማካፈል የሚፈልጉትን ማናቸውንም ነገር።
3. ማሳለፍ፣ ማለት የሚያካፍሉት ነገር የላቸውም ማለት ነው።

ከአንድ ሰው በመጀመር በክቡ መደዳውን አትሂድ። በእንዲህ አይነቱ አካሄድ አይናፋር የሆነውን ሰው ልታስፈራራውና ጫና በመፍጠር ማካፈል እንዳለበት እንዲሰማው ታደርገዋልህ። ሰዎች ማካፈል ሲፈልጉ ብቻ ፍቀድላቸው፤ ጥያቄው የተቀበለው ሰው ስለ ጥያቄውን ለማሰብ ጊዜ የነበረውና እንዴት መመለስ እንዳለበት አስቀድሞ የተዘጋጀ ስለሆነ ይሆናል ምናልባት መጀመር የፈለገው።

ይህ ጊዜ በቡድንህ ጠቃሚ ጊዜ ነው፣ ነገር ግን ከ15-20 ደቂቃ ልትወስነው ሞክር።

አልፎ አልፎ ለአንድ ሰው ምስክርነቱን ለቡድኑ እንዲያካፍል አጋጣሚውን ልትሰጠው ትችላለህ። አንድ ሰው ስለ እምነቱ ማካፈል ከፈልገ ወይም እንግዳ ስለሆነ የፀሎት መልስ ማካፈል ከፈለገ ለቡድኑ ያካፍል።

ለምስጋና እና ለፀሎት ሊሆኑ ስለሚችሉ ፍላጐቶችን ወይም በረከቶችን በምስክርነቱ ጊዜ አዳምጥ ወይም በሚያካፍሉበት ጊዜ አስቁመህ ለፍላጐቶች (ለእጦቶቸ) ፀልይ፤ ወይም ስለ በረከቱ እግዚአብሔርን አመስግን። እነዚህ እውነተኛ የሕይወት ልምምዶች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ጊዜ እንደገና እነዚህን ጉዳዩች ልታንፀባረቃቸውና በሕይወታቸው እንዲያዛምዷቸው አጋጣሚው ሊኖርህ ይችላል።

መሪዎች አስተባባሪ እንጂ የማካፈሉን ጊዜ ሊቆጣጠሩ አይገባም። በጨዋታ ደስ እያላችሁ እርስ በእርሳችሁ ተዋወቁ።

# የማካፈል ጥያቄዎች

1. በህይወትህ ደስ ስለተሰኘህባቸው ቀናቶች አካፍል።
2. ራስህን አንተን ለማያውቅህ አንድ ሰው እንዴት ነው የምታስተዋውቀው /የምትገልፀው?
3. በዛሬው ቀን ያለህበትን ስሜት የሚገልፀው የትኛው የቀለም አይነት ነው?
4. ከቅርብ ጓደኛህ በጣም የምታደንቀው ምንድን ነው?
5. እግዚአብሔር አንተን የተናገረበት ለየት ያለ መንገድ ምንድን ነው?
6. እስከዛሬ ካነበብካቸው መፃህፍት ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ነው? ለምን?
7. ስትሞት በመቃብርህ ላይ ፅሁፍ እንዲፃፍ ብትፈልግ፣ ምን ተብሎ እንዲፃፍ ትፈልጋለህ?
8. እቤት ውስጥ መስራት የምትወደው አንድ ነገር ምንድን ነው?
9. ከተቀበልካቸው ስጦታዎች የተመረጠው የቱ ነው? ለምን?
10. በህይወትህ መለወጥ የምትፈልገው አንድ ነገር ቢኖር ምንድን ነው?
11. እግዚአብሔር ላንተ ከቃል ያለፈ ሆኖ ያገኘህበት አጋጣሚ ከነበረ መቼ ነው?
12. በአስራ ሁለት ዓመትህ የት ትኖር እንደነበረና ስለምታስታውሰው አንድ ነገር አካፍል።
13. ልጅ እያለህ በጣም የምትወደው የጫወታ አይነት ምን ነበር?
14. በጣም ውድ ከሆኑ ንብረቶችህ ሁለቱ ወይም ሶስቱ የትኞቹ ናቸው? ለምንድነው ውድ የሆኑት?
15. በፊት ለፊትህ ባለው ዘመን ልታየው የምትፈልገው አንድ ነገር ምንድን ነው?
16. በግል ግንኙነትህ ልታሻሽለው የምትፈልገው አንድ ነገር ምንድን ነው?
17. መቼ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ኢየሱስ የሰማኸው? ስለ እርሱስ ምን ታስብ ነበር?
18. በአየር ንብረት ገለፃ መሰረት ህይወትህን ግለፅ?
19. ከፍተኛ እርካታ የሚሰጥህ አንድ ነገር ምንድን ነው?
20. በጣም የሚያስፈራ ጊዜ ____________________________
21. ወደ ____________________________ መጓዝ እወዳለሁ።
22. በትርፍ ጊዜህ ምን መስራት ትወዳለህ?
23. በቤተህ ውሰጥ የትኛውን ስፍራ ነው በጣም የምትወደው?
24. ልጅ እያለህ በተለየ ሁኔታ የምትወደው አጫዋች የቤት እንስሳ ነበረህ? ለምን ልዩ ሆነ?
25. በሚቀጥለው ዓመት በዚህ ጊዜ በሙያህ ልታየው የምትወደው መሻሻል ምንድን ነው?
26. ከክርስቶስ ቀጥሎ በህይወት ተፅዕኖ ያደረገብህ ሰው ማን ነው? ለምን?
27. ልጅ እያለህ የቅርብ ጓደኛህ ማን ነበር? ለምን?
28. ____________________________ መማር አላቋርጥም።
29. የሚመጣው ዓመት ለኔ ጥሩ ይሆናል ምክንያቱም ____________________________
30. እኔ ____________________________መሆኔን በማወቃቸው ሰዎች ሊገረሙ ይችላሉ።
31. በቀኑ ወይም በሳምንቱ መጨረሻ በኋላ ከውጥረት ለመርገብ ወይም ትንሽ ተንፈስ ለማለት ምንድነው የምታደርገው?
32. ምንድነው የሚያስጨንቅህ?
33. በጣም በተለየ ሁኔታ የምትወደው ሽታ የቱ ነው? ከእርሱስ ጋር ምን ትዝታ አለህ?

# የሕይወት ቡድን

## ሳምንታዊ መቆጣጠሪያ ቅጽ

| ሙሉ ስም ባል/ሚስት | ቀን | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |

ብዙ ጸሎት
ብዙ ኃይል
ብዙ ምስጋና

| የፀሎት ጥያቄዎች/አርዕስት | ቀን | መልስ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# ለመምራት መማር
## ክፍለ ጊዜ ሁለት
## የእግዚአብሔር ቃል

እያንዳንዱን ነጥብ ከመሪህ ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግበት።

**ከመሪህ ጋር ከመገናኘትህ በፊት ዝግጅት**

☐ 1. **የትንንሽ ቡድኖች ጥቅም** የሚለውን አንብብ። በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ስላሉት ስለተለያዩ
ትንንሽ ቡድኖች ለመወያየት ተዘጋጅ።

☐ 2. **የሕይወት ቡድኖች ጥቅም** የሚለውን አንብብ። በትንንሽ ቡድኖችና በህይወት ቡድኖች መሀል ያለውን ልዩነት ለመግለፅ ተዘጋጅ።

☐ 3. **«ለምን ትንሽ ከትልቅ የበለጠ ሆነ?»** የሚለውን አንብብ።
የቡድኖችን ትንሽነት ለመጠበቅ  እነዲቻለን ቡድናችን  አዳዲስ ቡድኖችን በማፍራት ለማብዛት  ያለህን መሰጠት ለማካፈል ተዘጋጅ።

☐ 4. **«የእግዚአብሔር ቃል - መማር/ መፅሐፍ ቅዱስ ጥናት»** የሚለውን አንብብ። **«ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት»** እና **«በእየለቱ ከእግዚአብሔር ጋር»** የተሰኘውን ክፍል ለመወያየት ተዘጋጅ። በመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ውይይት እና በመስበክ ወይም በማስተማር መካከል ያለውን ልዩነት ግለፅ።

**ከመሪህ ጋር የሚፈፀም**

☐ 5. እያንዳንዳችሁ የግል ደስታችሁንና የሚያሳስባችሁን አካፍሉ። ስለ ቡድኑ አስፈላጊነት አካፍሉ።

☐ 6. ከላይ ከ 1-4 ያሉትን ነጥቦች ከተወያያችሁ በኋላ ይህን (✓) መልክት አድርጉበት።

**በዚህ ወር ከቡድንህ ጋር ለመካፈል ያሉህ ዕቅዶች**

☐ 7. **«በየእለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝ ጊዜ»**ን የመስሪያ ወረቀት መግለፅ።
ቀን ______________________ ስም ______________________

☐ 8. **«በኃይል የሚንቀሳቀስ ሕይወት ሂደት»**ን መግለፅ።
ቀን ______________________ ስም ______________________

☐ 9. የራስህን የግል እድገት ማስመር። የእያንዳንዱን ሰው መሻሻልና ያጠናቀቁትን በማየት መመዝገብ።
ቀን ______________________ ስም ______________________

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 10. ለእርስ በእርሳችሁና ለቡድናችሁ አባላት መፀለይ

☐ 11. ለክፍለግዜ ሦስት የመዘጋጃ ስራን በጥንቃቄ ተመልከተው

☐ 12. ለሚቀጥለው ለመምራት መማር ክፍለ ግዜ ቀን ____________________________
ሰዓት ____________________________ ቦታ ____________________________
መደብ።

☐ 13. ለሚከተለው ዳይናሚክ ማካፈል ስልጠናችን ቀን ____________________________
ሰዓት ____________________________ ቦታ ____________________________መደብ።

# የትንሽ ቡድን አስፈላጊነት

ትንሹ ቡድን የአንደኛው ክፍለ ዘመን የቤት ቤተክርስቲያን የዚህ ዘመን ገፅታ ነው። ምናልባት 6-10 ሰዎች ትክክለኛው መጠን ነው፤ ነገር ግን ከ 4-12 ሰዎች ባለው ማንኛውም ቁጥር ሊሆን ይችላል። የዘመናዊው አለም የፍላጐት ግፊት እና የፍቅር፣ የአገልግሎትና በእድገት እርስ በእርስ መነቃቃት የሆነውን መፅሀፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ፤ ትርጉም ያለውን የእርስ በእርስ ግንኙነት በተሻለ ለሚያመቻቸውና በግለሰቦች እድገትና አገልግሎት ላይ ወደሚያተኩረው የትንንሽ ቡድን ሐሳብ መመለስ እንዳለብን ያሳስበናል፡

***የክርስቶስን አፍቃሪ ባህሪይ ለዓለማችን ስናንፀባርቅ፣ ትንንሽ ቡድኖች ክርስቲያኖች የጋራየእርስ በእርስ የኃላፊነት ግንኙነት ሊያገኙ የሚችሉበትን አንድ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማህበረሰብን ያቀርቡልናል።***

## የትንንሽ ቡድን አይነቶች

| | ክትትል/እንክብካቤ ደቀመዝሙር ማድረግ | መጽሐፍ ቅድስ ጥናት /ፀሎት | እርዳታ | አገልግሎት/ የአገልግሎት ቡድን |
|---|---|---|---|---|
| ትኩረት | በአቻ ለአቻ መጋቢያዊ እንክብካቤ የክርስቶስን መልክ መያዝ፣ የእርስ በእርስ መዋደድ፣ ሌሎችን ደቀመዝሙር ማድረግ | ለክርስቲያናዊ ኑሮ እንደ መመዘኛ መፅሀፍ ቅዱሳዊ መረጃዎችን ማቅረብ፣ ለፀሎት በአንድነት መስማማት | ኃላፊነት የሚሰማው አባል የግል ችግሩን ለማስወገድ በሚያደርገው ጥረት መርዳትና መደገፍ | ልዩ ኘሮጀክቶችንና ስራዎችን ማጠናቀቅ፣ ክርስቶስን መምሰል |
| ባሕሪያት | በቡድኑ ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታዎችን መለማመድ፣ ወንጌል ስርጭትን ማስፋፋት፣ መዋሀድና ደቀመዝሙርነት፣ ለመተማመንና ለግልፅነት መስራት | ጥናቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ፣ ርዕሰ ጉዳዩች ወይም በመፅሀፍቶች ላይ ሊያተኩር ይችላል ፤አንዳንድ ቡድኖች በፀሎትና በህብረት ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ ፤ ብዙውን ግዜ በአንድ አስተማሪ ወይም መሪ ይመራል | ትኩረትና የትምህርቱ ይዘት በክፍሉ ኃላፊ ይወሰናል፤ ውይይት፣ ጥናት ፀሎትና ተቃውሞ ይኖረዋል | ሰዎችን ለልዩ ስራ ማሰባሰብ፣ ኃይለኛ/ጠንካራ የአብሮነት ስሜትን መፍጠር፤ለስራው መፈፀም ጥሩ ሁኔታ መፍጠር |
| የቆይታ ጊዜ | በእድገት መቀጠልና አዳዲስ ቡድኖችን መውለድ | የቡድኑ የህይወት ዘመን የአዳዲስ ሰዎች ባለማቋረጥ መጨመር ወይም አለመጨመር ጋር ይያያዛል | በግል ፍላጐቶችና በቡድኑ ዓላማ ይወሰናል | በቤተክርስቲያን የአገልግሎት መዋቅር ይወሰናል |
| አረባብ /አበዛዝ/ | ቡድኖች ያድጋሉ ይባዛሉ፣ ተተኪ መሪን ማሰልጠን | ቡድኑ የተወሰነ ጊዜ ላይ ረዳት ይኖረዋል | ተተኪ መሪዎች አዳዲስ ቡድኖችን ለመጀመር ይሰለጥናሉ | የተመረጠው ቡድን ለአንድ ተርም ይሰራል የተሰየሙ ወይም ፍቃደኛ የሆኑት ቡድን ይበዛሉ |

የጉባኤውን ተካፋዮች የእድገት ደረጃ ፍላጐት ለማሟላት የተለያዩ አይነቶች ትንንሽ ቡድኖች ሳያስፈልጉ አይቀርም። ቡድኖች ብዙውን ጊዜ በሰዎች የጠበቀ ግንኙነት ይመሰርታሉ በጋብቻ ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ የግል ፍላጐት፣ የህይወት ደረጃ፣ ስራ ወይም አገልግሎት

**እነዚህ ሁሉ ቡድኖች ከጠበቀ ግንኙነታቸው አካባቢ አዲስ ሰዎችን በመማረክ ያድጋሉ።**

- ግብር ወይም አገልግሎት
- በእድሜ የሚበልጡ (በእድሜ የሚበልጡ ብቻ)
- ቅልቅል (ከሁሉም የዕድሜ ክልልና ከማንኛውም ደረጃ)
- ቅልቅል - ከኮሌጅ ዕድሜ በላይ የሆኑ ጉልማሶች ብቻ (ማንኛውም ደረጃ)
- ሴቶች
- ወንዶች
- ላጤዎች (ላጤዎች ብቻ)
- የኮሌጅ ዕድሜ (ኮሌጅ ብቻ)
- የሁለተኛ ደረጃ ዕድሜ (ብቻ)
- የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ እድሜ (ብቻ) - ልዩ ስርአተ ትምህርት ለዚህ የዕድሜ ክልል ሊቀረፅ ይገባል።
- ልጆች (ብቻ) - ልዩ ስርዓተ ትምህርት
- ቤተሰብ (ወላጅና ወጣት ልጆች በአንድነት)

# የሕይወት ቡድኖች አስፈላጊነት

ከላይ የተገለፁት ማናቸውም ትንንሽ ቡድኖች አስፈላጊዎች ናቸው።
አብዛኞቹ ትንንሽ ቡድኖች።

1. **አቀባበል - ፍቅር / ማካፈል**
2. **የእግዚአብሔር ቃል - መማር / የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት**
3. **አምልኮ - ምስጋና እና ፀሎትን ያካትታሉ።**

የሕይወት ቡድን በተለየ መንገድ ልዩ ነው! በሕይወት ቡድን ውስጥ መሪው የሁሉም ፍላጐት ይሟላ ዘንድ የተወሰኑ ሰዎችን ለአገልግሎት በማዘጋጀት ለቡድኑ አባላት መጋቢያዊ አመራርን ይሰጣል።

## የትንሽ ቡድኑ ጊዜ

የቡድኑ ግዜ ከሌሎች ትንንሽ ቡድኖች ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ የህይወት ቡድኖች ግን ለቡድኑ ህይወት ወሳኝ የሆኑና ለቤተክርስቲያን ህይወት የሆኑ ሁለት በጣም አስፈላጊ ግብአቶችን ይጨምራል።

## የአንድ ለአንድ ጊዜ

የአንድ ለአንድ ጊዜዎች ስልጠና፣ ማለትም **በዳይናሚክ መሰረታዊ፣ በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግና** እና **በዳይናሚክ ማካፈል** እና ለመሪውና ለተተኪ የመሪነት ስልጠናዎች «**ለመምራት መማር**» በተባለው ርዕስ ከስራ ልምድ ጋር ሌሎች ግብአቶችን ይጨምራሉ። ለምሳሌ፡-

4. **ስራ -- አገልግሎት/የመሪ ግንባታ እና የደቀመዝሙርነት ስልጠና**
5. **መማረክ - ሌሎችን መድረሰን ያካትታል**

ሰዎች ደቀመዝሙር ሲሆኑ መሪዎች እየታዩ ይመጣው። ብዙ መሪዎች ማለት ደግሞ ብዙ አልግሎት ነው። የአሁኖቹ የሕይወት ቡድኖች ወደብዙ የህይወት ቡድኖች ይበዛሉ።

**አስታውስ፡- አንድ ለአንድ ደቀመዝሙር ማድረግ + ትንሽ ቡድን = የህይወት ቡድን መሆኑን**

# ለምን ትንሽ ከትልቅ በለጠ

ብዙ ሰዎች ቡድኑ ትልቅ ሲሆን - የበለጠ ውጤታማ እንደሆነ ያስባሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ ትንንሽ ቡድኖች በብዙ ፍጥነት ማደጋቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ለመሪ ዕድገት ከፍተኛ አቅምን ይሰጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለብዙ ሰዎች አገልግሎትን በመስጠት ይገኛል፡፡

ለምሳሌ፡-

- ቡድን አንድ በ12 ሰዎች ጀመረ እና ወደ 18 አደገ፣ እንደገና ለበርካታ አመታት ቀጠሎ ወደ 16-20 ሰዎች - ጠቅላላ 20 ሰዎች አደገ
- ቡድን ሁለት በ5 ሰዎች ብቻ ጀመረና በፍጥነት ወደ 10 ሰዎች አደገ፡፡ ከስድስት ወሮች በኋላ አንድ አዲስ ቡድን ወለደ፡፡ አሁን ሁለቱ ባለ5 ሰዎች ቡድኖች እያንዳንዳቸው አንደ አዲስ ቡድን የሚወልዱ 2 ባለ 10 ሰዎች ሆኑ፡፡ 4 ባለ 5 (20 ሰዎች) ቡድኖች ወዲያው 8 ባለ 5 (40 ሰዎች) ቡድኖች ሆኑ፣እንደገና 8 ባለ 10(80 ሰዎች) ቡድኖች 10 (80 ሰዎች)፣ እንደገና ወደ 16 ቡድኖች ባለ 10 (160 ሰዎች) አደገ፡፡

| ቡድኖች | በዚህ ጀመሩ የሰዎች ቁጥር | ወደዚህ አደጉ | ሆኑ | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 5 | 10 | ባለ5 ሰዎች 2 ቡድን = | 10 |
| 2 | 5 | 10(20) | ባለ5 ሰዎች 4 ቡድን = | 20 |
| 4 | 5 | 10(40) | ባለ5 ሰዎች 8 ቡድን = | 40 |
| 8 | 5 | 10(80) | ባለ5 ሰዎች16 ቡድን = | 80 |
| 16 | 5 | 10(160) | ባለ5 ሰዎች32 ቡድን = | 160 |
| | | እንደዚህ እያለ ይቀጥላል | | |

ቡድን አንድ በመደመር አድጓል፡፡ ቡድን ሁለት በመባዛት አድጓል፡፡

***ለምን አንድ ቡድን ወደ አስር ሰዎች ሲደርስ እንዲወልድ ይደረጋል? ለምን ዝም ብሎ አያድግም?***

ከልምድ እንደታየው ያ ቡድን እስከ 10 በፍጥነት ያድጋል ነገር ግን ከ10 በኋላ እድገቱ በጣም አዝጋሚ ይሆናል፡፡ ግን ለምን እንደዚህ ሆነ?

ከ 4-10 ሰዎችን ያቀፉ ትንንሽ ቡድኖች፡-

- ከቡድኑ አባላት የነፍስ ወከፍ አገልግሎት ይኖራቸዋል፡፡ ምክንያቱም መሪዎች ለመንከባከብ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው ያሉዋቸው፡፡
- ግልፅና ታማኝ ናቸው
- አዳዲስ ሰዎችን በመሳብ ለማደግ ከፍተኛ ፍላጐት አላቸው
- አዳዲስ ሰዎችን ለመጋበዝና ወደጉባኤው እንዲመጡ የሚያስፈራሩ አይደሉም
- እያንዳንዱን ተሳታፊ እንዲያገለግል ስለሚጠይቁ እያንዳንዱም ሰው ፀጋውን ለማሳደግ፣ አገልግሎትን ለመማርና ሌሎችን ለመምራት እድሉ ይኖረዋል፡፡
- አዳዲስ መሪዎችን እንዲመሩ ለመመልመል ቀላል ናቸው (ብዙ ሰዎች የ 5 ሰዎች ቡድንን መምራት ይችላሉ፣ ነገር ግን ጥቂት ሰዎች ብቻ 20 ሰዎችን ቡድን መምራት ይችላሉ)

# የእግዚአብሔርን ቃል - መማር/ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

***የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናትና ተግባራዊ ለማድረግ***

*መፅሐፍ ቅዱስ እንዴት መኖር እንዳለብን የሚነግረን ልዩ የእግዚአብሔር መመሪያ ስለሆነ፣ እርሱን ማጥናታችንና መረዳታችን በጣም አስፈላጊ ነው። ይሁንና መረዳታችን በራሱ በጭራሽ የመጨረሻ መሆን የለበትም። ይልቁንም ለመሄድና ፍሬ ለማፍራት በእርሱ እንደተሾመ የእግዚአብሔር መሳሪያዎች እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል በህይወታችን ልንተገብረው ይገባናል።*

***«ኢየሱስም በእርሱ ያመኑትን አይሁድ እንዲህ አላቸው፤ በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ»።*** ዮሐንስ 8÷31

***«በክፋዎች ምክር የማይሄድ፣ በኃጢአተኞች መንገድ የማይቆም፣ በፌዘኞችም ወንበር የማይቀመጥ፣ ሰው ብፁዕ ነው። ነገር ግን ደስ የሚሰኘው በእግዚአብሔር ሕግ ነው፤ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያሰላስለዋል።»*** *መዝ* 1÷1-2

***«እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን፤»*** ቈላስያስ 1÷28

***«እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሰከረለት ሠራተኛ፣ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።»*** 2ጢሞቴዎስ 2÷15

**የእግዚአብሔርን ቃል - መማር / የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት (ለማጅ ወይም የሚመራ መሪ)**


- በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ትምህርት ሦስት «**ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት**» የሚለውን ክፍል አጥና ወይም ከልስ። ለቡድንህ ኃሳቡን አካፍል፤ «**የየዕለቱ ጊዜዬ ከእግዚአብሔር ጋር**» የተሰኘውን የስራ ወረቀት ናሙና አሳያቸው። በዚህ መጠቀም እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ህይወት በረከትን እንደሚያመጣ በማሳየት በረከትህን አካፍል ወይም ሌሎች እንዲያካፍሉ አድርግ።
- ለጥናት የሚሆኑ የተዘጋጁ ፅሁፍችን አጥና። ለምሳሌ፣ የህይወት ጥናቶች ከዳይናሚክ ቸርች ኢንተርናሽናል፣ ከመጋቢው የእሁድ መልዕኮት የውይይት ጥያቄዎችን ማዘጋጀት።
- እንዴት የህይወት ጥናቶቹን መጠቀም እንዳለብህ ልብ በል። «**የመጀመያዎቹ ደቀመዝሙር መጠራት**» የሚለውን ናሙና ተመልከት። ይህ ከ 24ቱ ተከታታይ ትምህርቶች አንዱ ነው። (ቅደም ተከተሉን ተመልከት)
- ሌሎች ተስማሚ የቡድን ጥናት ትምህርቶች ይገኛሉ።በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት የወርክሾኘ መፅሀፍ ወሰጥ የሚገኘውን **ለቡድን ስርዓተ - ትምህርትን መምረጥ** የተሰኘውን ክፍል አንብብ።ይሄ የቡድንህን ፍላጐት ለማሟላት ምርጥ የትምህርት መርጃ መፃህፍትን ለመመዘንና ለመምረጥ ይረዳሃል።

***ማስታወሻ፡- ይሄ ለጥልቅ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት አልታቀደም ፤ነገር ግን ለአጭርና ግልፅ ለሆነ ፅሞና ነው። እንደ አንድ ለአንድ ጥናት ምንም አይነት የቤት ስራ ሊኖረው አይገባም፤ ንቁ ሁን።***


እያንዳንዱ ሰው ቢሳተፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜህ በጣም የሚወደድና ትርፋማ ይሆናል። እንደ ጥናቱ መሪ የአንተ ኃላፊነት ለዚህ ተሳትፎ ሰዎችን ማበረታታት ነው። ማስተማር ወይም መስበክ እንዳለብህ አይሰማህ፤ ነገር ግን ሌሎች የቡድን አባላትን እርስ በእርስ እንዲገናኙ አመቻች። የራስህን መረዳት ልታንፀባርቅ ትችላለህ፤ ነገር ግን ቡድኑን አትቆጣጠር።

የውይይት ጊዜ፡-

እንደዚህ ሊሆን ይገባል




እንደዚህ ሊሆን አይገባም



ከላይ ያለውን ስዕላዊ መግለጫ አብራራ እና በኃይል የሚንቀሳቀስ ሕይወት ሂደት ውስጥ የተገለፀውን የአንድ ለአንድ ትምህርት አሳይ

# በኃይል የሚንቀሳቀስ ሕይወት ሂደት




# የግል እድገትህን መከታተል

እያንዳንዱ ሰው እስካሁን ያጠናቀቀውን ትምህርት በግራፍ ላይ ያመልክት

| ስም | ዳይናሚክ መሰረታዊ | ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ | ዳይናሚክ ማካፈል | ሌሎችን | ዳይናሚክ መሠረታዊ ማሰልጠን | ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ማሰልጠን | ዳይናሚክ ማካፈል ማሰልጠን | እገዛ | እንግዳ ተቀባይን ማገልገል | ተተኪ መሪን ማገልገል | መሪን ማገልገል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |

ግባችን ለእያንዳንዱ ሰው የደቀመዝሙርነት ስልጠና እና መሪ ግንባታን መስጠት ነው።

# የሕይወት ጥናቶች

**የመጀመሪያዎቹ ደቀመዝሙር መጠራት**
**ሉቃ 5፥1-11**

በገፅ 23 ላይ የሚገኘውን የማካፈል ጥቃቄዎች ተጠቀም ወይም የሚከተሉት ጥቃቄዎች መልስ ፣እያንዳንዱ ሰው አንድ ጥያቄ መርጦ ማካፈል ያስፈልገዋል፡፡ በህይወት ለመጀመሪያ ግዜ ምን ተሰማህ፡፡

1. ዋና ለመዋኘት ስትሞክር
2. አዲስ የሆነ ስፖርት ስትሞክር
3. ከክፍል ወደ ክፍል ስትዘዋወር
4. ከቤት ስትወጣ
5. ስራ ስታገኝ

==========================================================

**ከመጽሐፍ ቅድስ ጋር መገናኘት**

ሉቃስ 5-1-11 አንብብና የሚከተሉትን ጥቃቄዎችና መልሶች አንብብ፤ ከብዙ ሰዎች ጋር በመሆን የመረጥከው መልስ ለምን ያንተ መልስ እንደሆነ አካፍል፡፡

1. ኢየሱስ ጀልባ በፈለገ ግዜ ስምዖን ጴጥሮስ መረቡን ያጥብ የነበረው በአጋጣሚ እንደሆነ ታስባለህ ወይስ ያ የእግዜአብሔር ዕቅድ ነበር?
   ሀ/ በአጋጣሚ ነበር
   ለ/ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ነበር
   ሐ/ እርግጠኛ አይደለሁም
2. አንተ ስምኦን ጴጥሮስን ሆነህ ቢሆን ኖሮ ጌታ ኢየሱስ እርሱን «ወደ ጥልቁ ፈቀቅ ብለህ መረብህን ጣል» ባለው ጊዜ ምላሽህ ምን ይሆን ነበር?
   ሀ/ እንደ ጴጥሮስ ይሆን ነበር
   ለ/ ባለማድረግ ምክንያቶችን አስቀምጥ ነበር
   ሐ/ ኢየሱስ ስብከቱ እንዲቀጥልና እኔም አሳ ማጥመዴን እሰራ ነበር
   መ/ አሳዎቹ በሚከማቹበት ጊዜ እጠቁመው ነበር፡፡
   ሠ/ ዝም ብዬ እሄድ ነበር፡፡
3. መረባቸው እስኪቀደድ ድረስ በጣም ብዙ አሳ በያዙ ጊዜ፣ ስምኦን ጴጥሮስ ምን ያስብ እንደነበር ምን ትገምታለህ?
   ሀ/ ከዚህ ሁሉ አሳ ሽያጭ የሚያገኘውን ገንዘብ
   ለ/ ኢየሱስን መጠራጠሩ ትክክል እንዳልነበር
   ሐ/ ምን እንደሚያስብ አያውቅም ነበር
   መ/ ኢየሱስ ማን እንደሆነ አረጋገጠ ነበር
4. ስምኦን ጴጥሮስ «ጌታ ሆይ ከእኔ ራቅ እኔ ኃጢያተኛ ነኝ» ማለቱ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
   ሀ/ እኔ ትሁት ነኝ ምክንያቱም ስለማጥመድ ከእኔ ይልቅ አንተ ታውቃለህ፡፡
   ለ/ በኃጥያት የተበከለ ሕይወት ስላለኝ ያንተ በአጠገቤ መሆን ጥሩ ስሜት / ነፃነት እንዲሰማኝ/ አያደርገኝም
   ሐ/ አንተ እንደ ቃልህ እንደሆንክ አውቃአለሁ ነገር ግን አንተን ለመከተል ዝግጁ አይደለሁም፡፡
   መ/ እኔን የበደለኝነት ስሜት እንዲሰማኝ ማድረግህን ተው፡፡
   ሠ/ ግራ ተጋብቻለው፣ አንተን መከተል እፈልጋለሁ ነገር ግን እሺ ካልኩ በሕይወቱ የተወሰነ ለውጥ ማድረግ እንደሆነ ስለማውቅ እፈፈራለሁ፡፡

==========================================================

**ማዛመድ**

የአንተን የመንፈሳዊ ህይወት ጉዞ ተመልከት

1. ያንተ መንፈሳዊ ሕይወት ጅማሬና የስምኦን ጴጥሮስ ሕይወት የሚነፃፀረው እንዴት ነው?
   ሀ/ በቅፅበት ባለመሆኑ
   ለ/ በዕውቀት ስለመሆኑ
   ሐ/ እንደ ግራመጋባት
   መ/ በቅፅበት በመሆኑ
   ረ/ እርግጠኛ አይደለም
   ሠ/ በልዩ ሁኔታ ነገረ ግን ልክ እንደ እውነት
2. የአንተን መንፈሳዊ ጀልባ ሁኔታ እንዴት ነው የምትገልፀው?
   ሀ/ እየሰመጠ ነው
   ለ/ ተረጋግቶ (ፀንቶ) ነው ያለው፡፡
   ሐ/ በትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እየሄደ ነው
   መ/ ጥገና ያስፈልገዋል
   ረ/ በወጀቡ እየተናጠ ነው፡፡
   ሠ/ በትክክለኛ ሁኔታ እየሄደ ነው
3. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ወደ ጥልቁ ውሃ ፈቀቅ በልና አሳ ለመያዝ መረባችሁን ጣሉ» ብሎ ቢጠይቅህ መልስህ ምን ይሆን ነበር?
   ሀ/ እፈራ ነበር
   ለ/ የቂል ሃሳብ እንደሆነ እገምት ነበር
   ሐ/ እሺ ነገር ግን….
   መ/ ሌላ ሰው አብሮኝ ቢሆን አደርገዋለሁ
   ሠ/ መልካም መቼ እንጀምር
   ረ/ ምን እያልክ እንዳለህ አልገባኝም
4. እንድትሄድ የሚያደርግህ ነገር ምንድን ነው?
   ሀ/ ትርፍህን ለማስላት የምትወስደው ጊዜ
   ለ/ ለመዘጋጀት የምትወስደው ጊዜ
   ሐ/ እርግጠኛ አይደለሁም
   መ/ ከጓደኞቼ የማገኘው ድጋፍ
   ረ/ መታዘዝ
   ሠ/ ህይወቴን ለማስተካከል የሚያስፈልገኝ እርዳታ

## የመልዕክት ዋና ዋና ሀሳብ

ርዕስ ______________________________

ቀን ____________ ተናጋሪ ______________________
የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል
______________________________

ለእያንዳንዱ ዋና ዋና ነጥቦችንና ቁልፍ ሃሳቦችን ዘርዝር ____________

______________________________

በጣም የነካኝ የመልዕክት ክፍል______________________

______________________________

እግዚአብሔር ያስተማረኝ______________________

______________________________

የእኔ ምላሽ ______________________________

______________________________

## የየዕለት ጊዜዬ ከእግዚአብሔር ጋር

የ ____________ እስከ ____________ 20 _______ሳምንት

የዚህ ሳምንት የሚሰላሰል ጥቅስ (በየቀኑ መከለስ)

______________________________

______________________________ማጣቀሻ መፅሀፍት ______________________________

ቀን 1 የመፅሀፍ ቅዱስ ንባብ ማጣቀሻ______________________
በጣም ትርጉም ያለው ጥቅስ ______________________
እኔን የነካኝ ክፍል ______________________
______________________________
እግዚአብሔር ያስተማረኝ______________________
______________________________
የእኔ ምላሽ ______________________________
______________________________

ቀን 2 የመፅሀፍ ቅዱስ ንባብ ማጣቀሻ______________________
በጣም ትርጉም ያለው ጥቅስ ______________________
እኔን የነካኝ ክፍል ______________________
______________________________
እግዚአብሔር ያስተማረኝ ______________________
______________________________
የእኔ ምላሽ______________________________
______________________________

ቀን 3 የመፅሀፍ ቅዱስ ንባብ ማጣቀሻ______________________
በጣም ትርጉም ያለው ጥቅስ ______________________
እኔን የነካኝ ክፍል ______________________
______________________________
እግዚአብሔር ያስተማረኝ ______________________

የእኔ ምላሽ___________________________________________________

ቀን 4 የመፅሀፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል___________________________

በጣም ትርጉም ያለው ጥቅስ _______________________________

እኔን የነካኝ ክፍል_____________________________________

እግዚአብሔር ያስተማረኝ_________________________________

የእኔ ምላሽ __________________________________________________

ቀን 5 የመፅሀፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል __________________________

በጣም ትርጉም ያለው ጥቅስ ______________________________

እኔን የነካኝ ክፍል_____________________________________

እግዚአብሔር ያስተማረኝ_________________________________

የእኔ ምላሽ __________________________________________________

ቀን 6 የመፅሀፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል __________________________

በጣም ትርጉም ያለው ጥቅስ ______________________________

እኔን የነካኝ ክፍል_____________________________________

እግዚአብሔር ያስተማረኝ_________________________________

የእኔ ምላሽ __________________________________________________

ቀን 7 የመፅሀፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል___________________________

በጣም ትርጉም ያለው ጥቅስ ______________________________

እኔን የነካኝ ክፍል ____________________________________

እግዚአብሔር ያስተማረኝ ________________________________

የእኔ ምላሽ __________________________________________________

**ብዙ ፀሎት–**
**ብዙ ሃይል–**
**ብዙ ምስጋና-**

| ***የፀሎት ጥቃቄዎች/አርዕስት*** | ***ቀን*** | ***መልስ*** | ***ቀን*** |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# ለመምራት መማር
## ክፍለ ጊዜ ሦስት
## አምልኮና ፀሎት

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኂላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው።

**ከመሪዎች ቡድንህ ጋር ከመገናኘትህ በፊት**

☐ 1. **የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን** የሚለውን ክፍል አንብብ። የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመወያየት ተዘጋጅ። ከመሪህ ጋር ፀሎትህን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ተዘጋጅ። (እንደአስፈላጊነቱ)

☐ 2. **የአምልኮና ፀሎት ሦስተኛ ዋና አላማ** የሚለውን አንብብ። ኃላፊነትህን ለመወያየትና እንዴት አድርገህ ሌሎች የቡድንህ አባላትን የአምልኮና የፀሎት ጊዜውን ለመምራት እንደምታሳትፋቸው ለመወያየት ተዘጋጅ።

☐ 3. **ትርጉም ያለው አምልኮና ፀሎት የማድረጊያ መንገድ** የሚለውን አንብብ። ከመሪህ ጋር በቡድንህ ውስጥ ለመተግበር የምትፈልገውን የአምልኮና የፀሎት ስልት ለመወያየት ተዘጋጅ።

**ከመሪህ ጋር በመሆን የሚፈፀም**

☐ 4. እያንዳንዳችሁ የየግላችሁን ምስጋና እና ፀሎት ተከፋፈሉ። ስለ ቡድን አባላቶች አስፈላጊነት ተነጋገሩ።

☐ 5. ከላይ ከ 1-3 ያሉትን ነጥቦች ከተወያያችሁ በኂላ ይህን (✓) ምልክት አድርጉበት።

**በዚህ ወር ከቡድንህ ጋር ለማካፈል የያዛችሁት ዕቅድ**

☐ 6. መሪውና ለማጁ በሚቀጥሉት ሳምንታት መቼ ፣ ምን አይነት ስልት እና እነዚህን የአምልኮና የፀሎት አስተያየቶች የሚተገብረውን ሰው ተወያይተው ይወስኑ።

ቀን _______ስልት__________________________ ስም __________________________

ቀን _______ስልት__________________________ ስም __________________________

\`ቀን _______ስልት__________________________ ስም __________________________

ቀን _______ስልት__________________________ ስም __________________________

ቀን _______ስልት__________________________ ስም __________________________

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 7. ለእርሰ በእርሳችሁና ለቡድናችን አባላት መፀለይ

☐ 8. ለክፍለ ጊዜ አራት የመዘጋጃ ስራን በጥንቃቄ መመልከት

☐ 9. ለሚቀጥለው ለመምራት መማር ክፍለ ግዜ ቀን ____________________________
ሰዓት ____________________________ ቦታ ____________________________ መደብ።

☐ 10. ለሚከተለው ዳየናሚክ ማካፈል ስልጠናችን ቀን ____________________________
ሰዓት ____________________________ ቦታ ____________________________መደብ።

# የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን

በእግዚአብሔር አገልግሎት ውስጥ አገልጋይ መሪ ለመሆን የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን ያስፈልግሃል። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አገልጋይ መሪ ይገልፁታል። የሰው ዘርን ቤዛ በማድረግ የእግዚአብሔር ፍቃድ ለመፈፀም እንደ ባሪያ ሆኖ መጥቶ ነበር። ጳውሎስ የኢየሱስን የአገልጋይነት ሐሳብ በመግለፅ እንዲህ በማለት ያዘናል።

***«በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን፤ እርሱ በባህርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ግር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤ ነገርግን የባርያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ቦዶ አደረገ፤ ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።»***

ፊልጵስዩስ 2÷5-8

ትህትናንና መታዘዝን የሚያስከትለውን የክርስቶስን አመለካከት እያሳደግን ነን። ለደቀመዛሙርቱ ስለ አገልጋይነት በሰጠው መመሪያ ውስጥ፣ ኢየሱስ የራሱን የአገልግሎት ሚና እንዲህ በማለት ነበር የገለፀው፣ *«የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን፤ የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና።»*

*ማቴዎስ 20÷27-28*

የድነት ጥሪ ከዕርሱ ጋር በተልዕኮ የመሆን ጥሪ ነው። በዚህ አዲስ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር እርሱ እንደ ጌታና አዛዥ ሆኖልህ የባሪያነትን ሚና ለመጫወት ትሄዳለህ።

አንዳንዶች ባርያን እንደዚህ ይገልፁታል፣ ***«ባርያ ጌታው የሚፈልገውን ለይቶ በማውጣት የሚያደርግ ነው»*** ። ጌታው ይነግረውና ባርያው በራሱ ይሄድና ያደርገዋል። ያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የእግዚአብሔር ባርያ ፅንሰ ሀሳብ አይደለም። የእግዚአብሔር ባርያ መሆን ከዚህ የተለየ ነው። ለሰዋዊ ገዢ ባርያ የሆነ ለገዢው ይሰራል። ይሁንና እግዚአብሔር በባሪያዎቹ አልፎ ይሰራል።
የእኔ ስለ እግዚአብሔር ባርያነት ያለኝ መረዳት ልክ እንደ ሸክላና ሸክላ ሰሪ አይነት ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ለኤርሚያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፣ ***«ከእግዚአብሔር ወደ ኤርሚያስ እንዲህ የሚል ቃል መጣ፣- «ተነስተህ ወደ ሸክላ ሠሪው ቤት ውረድ፤ በዚያ መልዕክቴን እሰጥሃለሁ።» እኔም ወደ ሸክላ ሠሪው ቤት ወረድሁ፤ ሸክላውንም በመንኰራኵር ላይ ይሰራ ነበር። ከጭቃ ይሠራው የነበረውም ሸክላ በእጁ ላይ ተበላሸ፤ ሸክላ ሠሪውም በሚፈልገው ሌላ ቅርፅ መልሶ አበጀው። የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፤ «የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ሸክላ ሠሪው እንደሚሰራው፣ እኔ በእናንተ ላይ መስራት አይቻለኝምን?» ይላል እግዚአብሔር፤ «የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ጭቃው በሸክላ ሠሪው እጅ እንዳለ፣ እናንተም እንዲሁ በእጁ ውስጥ ናችሁ።»***

ኤርሚያስ 18÷1-6

ጠቃሚ ለመሆን፣ ሸክላው ቅርፅ ለማውጣት የተመቸ መሆን አለበት። አንዴ ወደ ሸክላ ዕቃነት ሲሰራ ሸክላው በሸክላ ሰሪው እጅ መኖር አለበት። ተራ የሆነ ሸክላ ተጠቅሟል! እግዚአብሔር እንደ ኤልያስ፣ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ እና ዲ.ኤል ሙዲ ያሉትን ተራ ሰዎች መጠቀሙ ያስደስተኛል። ዲ. ኤል ሙዲ ወንጌሉን ለመስበክ ጥሪ የደረሰው ብዙም ያልተማረ፣ ያልተሾመ ተራ ጫማ ሰፊ ሰው በነበረ ጊዜ ነበረ። አንድ ቀን ማለዳ እርሱና ጓደኞቹ በፀሎት ወቅት ለንስሀና ለመቀደስ በሳር ሜዳ ውስጥ ተሰባስበው ነበር። በዛ የፀሎት ስብሰባ ውስጥ ሔነሪይ ቫርሌይ እንዲህ አለ፣ «አለም እግዚአብሔር ራሱን በሙላትና በሁለንተናው ለእርሱ በሰጠው ሰው ጋር ፣ ለርሱ፣ በእርሱ በኩል እና በእርሱ በውስጥ ሊሰራ የሚችለውን ሊያይ ነው።»

ሙዲይ በእነዚያ ቃላቶች በኃይል ተወሰደ። ከእርሱና ለርሱ በእርሱ በኩል በርሱ ውስጥ የሚያደርገውን ሰው አለም ልታይ ነው!

ቫርሌይ ያለው ለማንኛውም ሰው ነው! ቫርሌይ የተማረ መሆን አለበት አላለም ወይም ብሩህ አዕምሮ ያለው ወይም ሌላ ማንኛውም ነገር! በቃ ሰው! ደህና፣ በውስጡ ባለው መንፈስ ቅዱስ ሙዲይ ከእነዚያ ሰዎች አንዱ ሆንዋል።

ዲ.ኤል ሙዲይ ለክርስቶስ በሙላትና በሁለንተና ለመስጠት ይፈልግ የነበረ ተራ ሰው ነበር። በዚህም አንድ ተራ ህይወት እግዚአብሔር አንደ የሆነ ነገር ለመስራት ጀምሮ ነበር። ሙዲይ ከዛ ዘመን ታላቅ ወንጌላውያን አንዱ ሆንዋል። አብዛኛውን ህይወቱን በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ክርስቶስ በሚመጡበት በእንግሊዝና በአሜሪካ ዙሪያ ባሉት የመነቃቃት አገልግሎቶች ላይ በመስበክ አሳልፏል።

እግዚአብሔር በአንተም ህይወት አልፎ እንግዳ በሆነ መንገድ ለራሱ መንግስት ትልልቅ ነገሮችን መፈፀም ይችላል?

እግዚአብሔር በብዛት ሊጠቀምበት የሚወደው ተራ ሰውን ነው። ጳውሎስ እግዚአብሔር ሆንብሎ ደካማ ነገሮችንና የተናቁትን ነገሮች እንደመረጠ ይነግረናል። ምክንያቱም ላቅ ያለውን ክብር ሊያገኝ የሚችለው ከነዚህ ነገሮች ነው። (1 ቆሮንቶስ 1÷26-31ን ተመልከት) ከዛም ማንም ሰው እግዚአብሔር ብቻ ያንን እንደሰራ ያውቃል። ደካማ፣ ውሱንና ተራ እንደሆንክ ከተሰማህ እግዚአብሔር በውስጡ አልፎ ሊሰራ የሚችልበት የተመረጠ ዕቃ ነህ።

እንደ ባርያ ቅርፅ ለማውጣት የተመቸና ለጌታህ ስራ ሁልግዜ የምትገኝ መሆን አለብህ። ምንም እንኳ ራስህን እንደ ተራ ሰው የምትቆጥር ቢሆን፣ እግዚአብሔር እርሱን ለሚያየው ዓለም ለመግለፅ በአንተ በኩል አልፎ ለሚሰራው ስራ ያዘጋጅሃል።

***«እግዚአብሔር እየሰራ ያለውን በመለየትና ከእርሱ ጋር መተባበር»***

የእግዚአብሔር ባርያ ለመሆን ትፈልጋለህ? ________________
እግዚአብሔር ብቻ ሊሰራ የሚችለውን ስራ እግዚአብሔር በህይወትህ ሲሰራ ማየት ትወዳለህ? ________________

ከዚያም ጌታህ የት እንዳለህ እወቅ - ያ አንተ መሆን ያለብህ ስፍራ ነው።
ጌታህ የሚያደረገውን ለይተህ እወቅ - ያ ነው አንተ ማድረግ ያለብህ።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ ***«የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፤ እኔም ባለሁበት አገልጋዬም በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝንም አባቴ ያከብረዋል።»*** ዮሐንስ 12÷26

የኢየሱስን ምሳሌ ተከተል፣ አንተ ምንም ማድረግ እንደማትችልና እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንደሚችል እወቅ።
አሁን በፀሎት ራስህን በእግዚአብሔር ፊት አዋርድ፣ ይህንንም ዕውነት ዕውቅና ስጠው። እንድትሆንለት ወይም እንድታደርግለት ለሚጠራህ ለማንኛውም ነገር ፍፁም የሆነ መገዛትህንና መታዘዝህን ለእርሱ ቃል ግባ።
ፀሎትህን በፅሁፍ ለእግዚአብሔር አቅርብ፦________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

# አምልኮና ፀሎት

*«ፀሎትን አስፈላጊ ለማድረግ አትሞክር - እግዚአብሔር ብቻ ነው*
*አስፈላጊ፤ ፀሎት አስፈላጊ የሚሆነው እግዚአብሔር አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው፡፡»*
*እግዚአብሔር ፍላጐትህ በሆነ ግዜ እርሱም ፍላጐት ይሆናል፡፡*
*ፀሎት ለአንተ አስፈላጊ ካልሆነ፣ እግዚአብሔር ላንተ*
*አስፈላጊ ያለመሆኑ ምልክት ነው፡፡*

ሴርጊኦ ጋርሲያ

*«እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ፣ በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው፡፡ ለሚፈሩት ፍላጎታቸውን ይፈፅማል፤ ጩኸታቸውን ይሰማል፤ ያድናቸዋልም፡፡»* መዝሙር 145÷18-19

## አምልኮ (መሪ)

- አንድ ወይም ሁለት የምስጋና መዝሙሮችን ወይም ዝማሬዎችን መዘመር፡፡
- የመዝሙር መጽሐፍትን ወይም ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን ማንበብ
- ለተመለሱ ፀሎቶች ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ
    - በእግዚአብሔር ባህሪይ ላይ አተኩር
    - የሚመች ከሆነ የጌታን እራት መካፈል
- እያንዳንዱን ሰው ተሳታፊ እንዲሆን ማበረታታት፡፡ መደዳውን/ዙሪያውን/ በመፀለይ ማንንም እንዳታሳፍር ተጠንቀቅ፡፡

## ፀሎት፡- (ለማጅ መሪ ወይም መሪ)

- ጭውውታዊ ፀሎት (አጭር፣ ሙሉ ዐ.ነገር ፀሎት)
- እያንዳንዱ ሰው እንዲሳተፍ ማበረታታት ነገር ግን ማንንም አለማሳፈር
- አጭርና ግልፅ በሆነ መልኩ የፀሎት ጥያቄዎችን ወይም መልሶችን መጠየቅ፡፡
- በእርስ በእርስና ለተወሰኑ የተገለፁ ፍላጐቶች መፀለይ፡፡
- በሳምንቱ ውስጥ እርስ በእርስ መፀለይ
- ለቤተሰብና ለጓደኞች በስማቸው መፀለይ
- በተፅዕኖ ክልላቸው ላሉት ሰዎች የመመስከር አጋጣሚው ይገኝ ዘንድ መፀለይ፡፡
- ወደ ሕይወት ቡድኑ ሊጋበዙ ለታጨት ሰዎች ወይም ለወንጌል ስርጭት ዝግጅት መፀለይ፡፡

# ትርጉም ያለው የህብረት ፀሎት የማድረጊያ መንገድ

*«በጸሎትና በልመና ሁሉ፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህንንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ፡፡»* ኤፍሶን 6÷18

የቡድንህ የፀሎት ጊዜ በቡድኑ ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ ሰው ለህይወት የሚያስፈልግና ደስ የሚያሰኝ ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ለአንዳንዶች ሁልጊዜ እንደዛ አይነት አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ ይህ የሚሆንበት ምክንያት በፀሎት ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት ስለሌላቸው ነው፡፡ በቡድንህ ያሉትን ሰዎች እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር በግል በአጠገባቸው የተገኘ እስኪመስል ድረስ መነጋገርን የማስተማር አስደናቂ አጋጣሚ አለህ፡፡

## ንግግራዊ /ጭውውታዊ/ ፀሎት

ቡድንህን እንዴት በጭውውት ለመፀለይን እንድታስተምር ልጠቁምህ ነው። ጭውውታዊ ፀሎት ማለት በቀላሉ ከእግዚአብሔር ጋር መጨዋወት ነው። ከአንድ አቅጣጫ ብቻ የሆነ የፀሎት ንግግርን ለጌታ ከማቅረብ ይልቅ፣ ይህንን ጊዜ እንደ ቡድን ከእርሱ ጋር ነገሮችን ለማውራት እንደ አጋጣሚ ተጠቀሙበት። አንድ ሰው የፀሎት ርዕስ ያምጣና አጭርና ግልፅ አድርጉ ሰለ እርሱ ይፀልይ። የሚቀጥለው ሰው፣ወደ ሌላ ሃሳብ ከመሄዱ ይልቅ በተመሳሳይ ርዕስ ላይ ለመቀጠል ይችላል። አስፈላጊው ነገር እያንዳንዱ ለፀሎት ለመሳተፍ የፈለገ ሰው ሁሉ እስኪደርስ ወደፊትና ወደኋላ በርዕሱ ላይ ለመፀለይ እድሉን መስጠት ነው። ከዛ በኋላ አንድ ሰው አዲስ የፀሎት አርዕስት ሊጀምር ይችላል።

የሚከተለው ምሳሌ በድንገት የሚደረግ ጭውውታዊ ፀሎትን ያሳያል።
አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ሊጀምር ይችላል፣ «ጌታ ሆይ እወድሃለሁ።» ሌላው በመከተል፣ «ዛሬ እዚህ በመገኘትህና አንተ እንደምትሰማን በማወቅ ካንተ ጋር መነጋገር በመቻላችን እናመሰግንሃለን» ሌላው እንዲህ ይፀልያል፣ «ጌታ ኢየሱስ ለኃጥያታችን እንዲሞት በመላክ ስላሳየኸን ፍቅር እናመሰግንሃለን።»አንዱ ከመዝሙረኛው ይጠቀሳል፣ «እግዚአብሔር ትልቅ ነው፣ በታላቅ ሊመሰገን ይገባል» ሌላው ድካሙን ይቀበላል፣ «ጌታ ሆይ በዚህ ምሽት እዚህ ላለመምጣት አለመፈለጌን እናዘዛለሁ፤ ነገር ግን እዚህ መሆን ስለቻልኩና ስለተናገርከኝም አመሰግንሃለሁ።» ሌላው ጥያቄ ያቀርባል፣ «ጓደኛዬን ተሸመን ወደ ራስህ እንድታመጣው እፀልያለሁ፣ የዳግም ልደትን ያገኘ ዘንድና የአንተ ደቀመዝሙር በመሆን ዋና መስካሪ ይሆን ዘንድ።»ሌላው ይስማማል፣ «አባት ሆይ በዚህ ፀሎት እስማማለሁ። እንዴት አድርገን በፍጥነት ይህንን ሰው መቅረብ እንዳለብን አሳየን።» እያለ ይቀጥላል።

### የፀሎት ጊዜያችሁ ይዘት

- ጌታን ስለማንነቱ፣ ስል መልካምነቱና ፍቅሩ፣ ፍላጐትህን ሁሉ ስለሚሞላው ብቃቱ፣ ስለዘላለም ህይወት እና ስለየግል የፀሎት መልሶች ጌታን ማመስገን።
- እግዚአብሔርን ስለተመለሱ የፀሎት መልሶች ማመስገን እና ለሌሎች የፀሎት ጥያቄዎች መፀለይ። በአንድነት በመሆን፣ ስለእያንዳንዱ የቡድኑ አባል ፍላጐት፣ ስለቤተሰብ ፍላጐት፣ ስለቤተክርስቲያናችሁ መሪዎችና ሚሲዮናዊያን እና ስለሌሎች የተገለፁ ፍላጐቶች መፀለይ። ላለህበት ህብረተሰብ፣ ሐገርና ለአለም መንፈሳዉ ተሃድሶ መፀለይ።
- ለራሳቸሁ የግል ፍላጐቶች መፀለይ።
- ስለ ፀሎት መሰማትና መመለስ ለእግዚአብሔር ያለህን አድናቆት ግለፅ።
- በየሳምንቱ የፀሎት ይዘቱን ለዋውጠው
    - እንደ አጠቃላይ ቡድን በአንድነት መፀለይ
    - ለበለጠ መቀራረብ ትንንሽ ቡድኖችን መስርት፣ ቡድኑን ወንዶችን ከሴቶች ጋር በመቀላቀል ወይም ወንዶችንና ሴቶችን በመለየት በ2 ቡድኖች ወይም በ3 ወይ በ4 ሰዎች መከፋፈል።

### የፀሎት መመሪያዎች

1. ብዙ ጐልማሶች የፀሎት አስፈላጊነቱ ቢታያቸውም ነገር ግን በቡድኑ ውስጥ ጮክ ብለው ለመፀለይ ያመነታሉ። እንዲጀምሩ በመርዳት ማበረታታታ ሳያስፈልግህ አይቀርም።
    - ስለ ፀሎት አስፈላጊነት ደጋግሞ ማሳሰብ አስፈላጊ ነው።
    - የታወቀ ኃጥያትን የመናዘዝ፣ ጥፋተኛ እንደሆኑ በእግዚአብሔር ፊት መቀበል እና ስለ ይቅርታው እርሱን የማመስገን አስፈላጊነት መወያየት።
    - እግዚአብሔር ወደ ህይወታችን ስላመጣቸው ማናቸውንም ነገር ስለማመስገን አስፈላጊነት መነጋገር።
    - እውተኛ፣ አጭርና ግልፅ እና የእምነታቸው ነፀብራቅ የሆነ ፀሎት እንዲፀልዩ እነርሱን ማበረታታት።

- ከእግዚአብሔር ጋር በሚያሳስባቸው ነገር ላይ በመንኛውም ጊዜ እንዲነጋገሩ አበረታታቸው፡፡
- ስለ እግዚአበሔር ያላቸው ግንዛቤ እንዲያድግ ማበረታታት
- የራሳቸውን የፀሎት ድምፅ እየሰሙ ይፀልዩ ዘንድ ድምፃቸውን አውጥተው እንዲፀልዩ ማበረታታት፡፡
- ፀሎቶቻቸውን በፅሁፍ በመፃፍ ወደ ቡድኑ አምጥተው እንዲያካፍሉ ማበረታታት

2. ዙሪያውን ከመፀለይ ይልቅ፣ መፀለይ የፈለገ ማንኛውም ሰው ይፀልይ፡፡

3. ዝምታን አትፍራ፡፡ በፀሎት መሐል ያለን አጭር ጊዜ እግዚአብሔር ለአንተ የሚናገርበት አጋጣሚ እንዲሆን ተጠቀምበት፡፡

4. ፀሎቱን በአንድ ወይም በሁለት ዐ.ነገር መወሰን፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው እንደፈቀደ መጠን ይፀልይ፡፡

5. አስተውል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በእርግጥ በክፍሉ ውስጥ ነው፡፡ ለመገኘቱ እንደሚታይ ማስታወሻ/ምልክት/ መሐል ላይ አንድ ባዶ ወንበር ማስቀመጥ ሊረዳህ ይችላል፡፡ በማቴዎስ 18÷19-20 እንዲህ ሲል ቃል ገብቶልናል፣ ***«ደግሞም እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ላይ ሁለት ሆናችሁ ስለምንም ነገር በመስማማት ብትጠይቁ በሰማይ ያለው አባቴ ያደርግላችኋል፤ ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ አገኛለሁና፡፡»***

6. የፀሎት ጥያቄ ምናልባት ልታቀርብ ትችላለህ ወይም ከጊዜ በፊት ቀድመህ ስለፀሎት ጥያቄ መግለፅ ወይም በቀላሉ ሌሎች በሚፀልይበት ግዜ ስለ ጉዳዩ በመፀለይ ጥያቄህን መግለፅ፡፡ ሌሎች የቡድኑ አባላት በጥያቄህ ላይ ስትፀልይ ይተባበሩህ፡፡ በልብህ ተጨማሪ ጥያቄዎች ከመጡ ጨምሮ ለማቅረብ አትጨነቅ፡፡

7. ለአይነት ያህል፣ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል  በራስህ አባባል በድጋሚ እየገለፅክ በመጠቀም ተመልሰህ ወደ እግዚአብሔር መፀለይ፡፡
ለምሳሌ፡- መዝሙር 145 በመጠቀም አንድ ሰው ቁጥር 1 ያነባል፡ «አምላኬና ንጉሤ ሆይ፤ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፤ ስምህን ከዘላለም እስከ ዘላለም እባርክሃለው፡፡» ከዚያ በኋላ ይሄው ሰው እንዲህ ይፀልያል፣ «አባት ሆይ! አመልክሃለሁ፡፡ አምላኬና ንጉሴ ስለሆንክ አመሰግንሃለሁ፡፡ ዛሬ ስምህን መባረክ ምንኛ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው፤ እስከ ዘለአለምም ላደርገውም እንጓለሁ»፡፡ ሌላ ሰው አንድ ቁጥር ወይም ሀረግ በማንበብ እና ወደ እግዚአብሔር በሚፀልየው ፀሎት ውስጥ ከህይወቱ ጋር አያይዞ ይቀጥላል፡፡ እስከቀረው የመዝሙር ክፍል ወይም ጊዜ እስከፈቀደ ድረስ እንዲሁ ይቀጥላል፡፡ ይህንን ልምምድ በአንድ ላይ ደስ ትሰኙበታላችሁ፡፡ ሞክሩት፡፡

8. በተመሳሳይ መንገድ፣ ለተለዩ ጥያቄዎች የእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም መፀለይ ትፈልጉ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡-
   - ለህመምና ከበድ ላለ ሸክም - ለድንገተኛ - ያዕቆብ 5÷14-15 1ጴጥሮስ 1÷5
   - በእኛ ላይ ስልጣን ላላቸው - ለመንግስት፣ ቤተክርስቲያን - 1ጢሞ 1÷1-6- ሮሜ 13÷1
   - ለድነት ጥያቄ - ሮሜ 10÷1 ፣ ዩሐንስ 14÷12-13 2ጴጥሮስ 3÷9
   - ለአማኞች - መጋቢያን - ኤፌ 3÷14-20 ፣ ቆላ 1÷9-12
   - ለመከሩ ሰራተኞች - ላሉትና ለሚያስፈልጉት፣ ማቴ 9÷38-38፣ሮሜ 10÷13-15

9. ጥያቄዎችህንና መልሶችህን መዝግብ
እነዚህን ሁሉ ሀሳቦች በአንድ ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብህ አይሰማህ፤ ነገር ግን ፀሎት ዋና  እና የግል ሆኖ እንዲቀጥል የተለያዩ ዘዴዎችን መሞከር፡፡ ደግሞም ለእነዚህ ስልቶች ተግባራዊነት ሌሎች ሰዎችን ለፀሎት ማሳተፍ እንዳለብህ አስታውስ፡፡ ይህ ለወደፊት ለሚነሱ መሪዎች ከምትሰጠው ስልጠና አንዱ አካል ነው፡፡

ብዙ ጸሎት-
ብዙ ኃይል-
ብዙ ምስጋና!

| የፀሎት ጥቃቄዎች/አርዕስት | ቀን | መልስ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# ለመምራት መማር
## ክፍለ ጊዜ አራት
## መማረክ

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው፡፡

**ከመሪዎች ቡድንህ ጋር ከመገናኘትህ በፊት**

☐ 1. **«የአገልጋይ መሪ ልብ»** የሚለውን ክፍል አንብብ፡፡ በታማኝነት የሆነ ግንኙነት በአንድ መሪ ህይወት ውስጥ ለምን ወሳኝ እንደሆነ እና የፍቅርና የማመን አስፈላጊነት ለመግለፅ ተዘጋጅ፡፡

☐ 2. **መማረክ** የሚለውን ክፍል አንብብ፡፡ ለቡድናችን ሰዎችን መድረስ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ለማካፈል ተዘጋጅ፡፡

☐ 3. **የሰዎች ሰዎችን መድረስ** የሚለውን ክፍል አንብብ፡፡ ከተፅዕኖ ክልልህ ውስጥ የመረጥካቸውን ሰዎች ስም ከመሪህ ጋር ለመካፈል ተዘጋጅ፡፡ ደግሞም በወንጌል ስርጭት ፀሎት የሚጫወተውን ሚና ግለፅ፡፡

**ከመሪህ ጋር በመሆን የሚፈፀም / የሚከናወን፡-**

☐ 4. እያንዳንዱ በዚህ ወር እግዚአብሔር በህይወቱ እንዴት እንደ ሰራ ያካፍል፡፡

☐ 5. ከላይ ከ1-3 ያሉትን ነጥቦች ከተወያያችሁ በኋላ ይህን (✓) ምልክት አድርጉበት፡፡

**በዚህ ወር ከቡድንህ ጋር ለመካፈል ማቀድ፡፡**

☐ 6. **«የሰዎች ሰዎች መድረስ»** ን ግልባጭ በማባዛት ለእያንዳንዱ ሰው ስጥ፡፡ የቡድኖች አባላት የራሳቸውን በፀሎት በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርቧቸው 7 ሰዎች እንዲመረጡ አጭርና ግልፅ ማብራሪያ በመስጠት መርዳት፡፡

ቀን ____________ ስም ________________________________

☐ 7. ለመረጧቸው ሰዎች በመደበኛው መፀለይ፡፡ ይህንን በቡድኑ ፊት ይዞ ለማቅረብ ኃላፊነቱን የሚወስደውን ሰው ወስን

ስም ________________________________

**ፀሎት እና መዝጊያ**

☐ 8. ለእርስ በእርስና ለቡድናችን አባላት መፀለይ

☐ 9. ለክፍለግዜ አምስት የመዘጋጃ ስራን በጥንቃቄ መመልከት

☐ 10. ለሚቀጥለው **ለመምራት መማር** ክፍለ ግዜአችን ቀን ______________________ ሰዓት

______________________________ ቦታ መመደብ።

☐ 11. ለሚቀጥለው ዳይናሚክ ማካፈል ስልጠና ቀን ______________________
ሰዓት ______________________ ቦታ መመደብ።

# የአገልጋይ መሪ ልብ

የባህሪይ መጐልበት የልብ መጐልበት ነው፡፡

**ልብን ለማገልገል ያለ የአገልግሎት ሂደት**
ልብን ለማጎልበት የፀጋ፣ የእውነት፣ የፍቅር አገልግሎት እና የልብ እንክብካቤ መርህዎችን መረዳት አለብን፡፡
በጊዜ ውስጥ እና በግንኙነቶች ውስጣዊ ባህሪዎችንን (ልባችንን) እናጎለብታለን፡፡

*«አገልግሎት ከግንኙነቶች ውስጥ ይወጣል»* አል ብሩም

**የአገልጋይ መሪ ግንኙነቶችን ለማጎልበት**

1. ፍቅር መኖር አለበት፡፡ ዮሐንስ 3÷16 ፣ የፍቅር አይነት፡፡ ***«ምንም ያህል ውደዱኝ፣ ልትወዱኝ የምትችሉት እኔን እድትወዱኝ የፈቀድኩላችሁን ያህል ብቻ ነው የምትወዱኝ፡፡»***

2. እምነት መኖር አለበት፡፡
   ***«ምንም ያህል ውደዱኝ፣ እናንተን ያመንኩበትን መጠን ያህል ነው እኔን እንድትወዱኝ የምፈቅደው፡፡»***

3. ለእምነት መኖር *ታማኝነት* መኖር አለበት፡፡
   ***«ታማኝነት የልብ መርህ ነው፡፡ የሙሉነት - ያለነቀፋ የሆነ ያልተሸራረፈ ህይወት ሁኔታ ነው፡፡»***
   ***ታማኝነት በሌሎች እንድንታመን ያደርጋል***
   ***ታማኝነት እኔ ያንተን እምነት ለማግኘት የምችልበት የእኔ የማንነት ጥራት ነው፡፡***

***ታማኝነትን ማጐልበት፡-***
ላደርገው የምችለውን (የማልችለውን) ነገር በርግጠኝነት መማር ነው፡፡
የሆንኩትንና ያልሆንኩትን በእርግጠኝነት ለመናገር መማር ነው፡፡
ታማኘነታችን በጊዜና በቀጣይነት የሚፈተን ነው፡፡

***ታማኝነት እንዴት ይፈተናል፡፡***

- ተግዳሮቱ ለውስጥ ለሆነ ፅኑ እምነት ይሆናል፡፡
- ምላሽ የምትሰጥበትን ፈተና እግዚአብሔር ያዘጋጃል፡፡
- ታማኝነትን ወይም አለመታመንን ለፈተናው ምላሽ እሰጣለሁ፡፡
- የታማኝነትን ፈተና ባለፍኩ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የታማኝነት ፈተናዎችን የማለፍ አጋጣሚዎቼን ያሰፋቸዋል፡፡
- ታማኝነት የጐደለው ልብ በጭራሽ ለእውነት ምላሽ አይሰጥም፡፡

## ግንኙነትን ለማጎልበት ጊዜ ይወስዳል፡፡

4. የግንኙነት እድገት ሂደት
   **ደረጃ 1 ግንኙነት**
   የሚያስፈልጉኝን ነገሮች አላውቃቸውም
   አንተም/ አንቺን ማመን ማለት ምን እንደሆነ አላውቅም
   አንተ/አንቺ በህይወቴ ውስጥ መግባት አትችሉም

**ደረጃ 2 ግንኙነት**

ፍላጐቶች እንዳሉኝ አውቃለሁ።

አንተን/አንቺን ማመን መቻሌን እርግጠኛ አይደለሁም።

እንድታይ የምፈልገውን ነገር ብቻ ገብተህ ማየት ትችላለህ።

**ደረጃ 3 ግንኙነት**

በራሱ ጊዜ ፍላጐቶቼን ለማሟላት ነው የምፈልገው

አንተን/አንቺን ለማመነ እየሞከርኩ ነው።

በህይወቴ ለመግባት የተወሰነ መንገድ ይኖርሃል።

**ደረጃ 4 ግንኙነት**

በራስህ ጊዜ ፍላጐቶቼን እንድታሟላ እፈልጋለሁ።

አምንሃለሁ።

በህይወቴ መግባት ትችላለህ።

5. መገዛት መኖር አለበት። መገዛት የፍቅርና የእምነት ምላሽ ነው።
   - መገዛት የእኩልነት ጉዳይ አይደለም - በአንተ ጥበቃ ስር መሆን ነው
   - መገዛት የስልጣን ጉዳይ አይደለም - ወደ አቅርቦትህ መምጣት ነው
   - መገዛት የቁጥጥር ጉዳይ አይደለም - መጠጋት ነው፤ ከኃላፊነት ነፃ መሆን ነው።

በሕይወት ቡድናችን ግንኙቶች፣ ወደ ሙሉ መተማመንና አንዳችን በአንዳችን ህይወት ለመግባት አስተማማኝ ሁኔታን ወደሚፈቅደው ወደ ደረጃ 4 የግንኙነት ግብ መስራት አለብን።

ቡድናችንን አስብ። የደረጃ 4 አይነት የግንኙነት ሁኔታ አለን? ________________________

***እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ እንዲኖረን የሕይወት ቡድናችንን ለመሻሻል ምን ማድረግ አለብን?***

_______________________________________________________________

❖ ሊደርሺፕ ካታሊስት ከተሰኘው የቢል ትራል እና የዶ/ር ቡሩስ ማክኒኮል መፅሀፍ ተከልሶ የተዘጋጀ።

# ሰዎችን መማረክ

**ሰዎች ሌሎችን ለክርስቶስ እንዲደርሱ ለማዘጋጀትና ለማነቃቃት**

እንደ ክርስቲያን በዚህ ዓለም የመኖራችን ምክንያት አለማችንን ለክርስቶስ ለመድረስ ነው። የክርስቲያኖች ቤት ደግሞ በዚህ ዘመን ለወንጌል ስርጭት ከምንጠቀምባቸው በጣም ውጤታማ መሳሪያዎች አንዱ ነው።

> ***«ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው ፤ እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስታርቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን፤ »*** (2 ቆሮንቶስ 5÷18)

> ***«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።»*** (የሐዋ 1÷18)

> ***«ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅድስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዝሙር አድርጓቸው፤ ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው።» ማቴ 28÷18-20***

## ሰዎችን መማረክ - መድረስ - ማዛመድ (መሪ)

- **በግል የሆነ የወንጌል ስርጭትን እንዲከተሉ ማድረግ**
- እያንዳንዱን ሰው አንድ የተቸረገን ሰው ለመረዳት አጋጣሚዎችን እንዲፈልግ ማበረታታት።
- እያንዳንዳቸው በራሳቸው የተፅዕኖ ክልል ውስጥ ለመረጡት ሰው በየጊዜው በመደበኛ እንዲፀልዩለት ማበረታታት።
- እያንዳንዱ ሰው ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች ጋር ግንኙነቶችን እንዲመሰርት ማበረታታት።
- እያንዳንዱ ሰው እምነቱን ለቤተሰቦቹ፣ ለጓደኞቹና ለጐረቤቶቹ ወ.ዘ.ተ እንዲያካፍል ማበረታታት።
- እያንዳንዱን ሰው ጓደኛውን ወደ ህይወት ቡድንህ ወይም የወንጌል ስርጭት ዝግጅት ላይ እንዲጋብዝ ማበረታታት። (ለተጋበዙት ሰዎች በስማቸው መፀለይ)

*የጨዋታ ምሽት፣ ድራማ ሙዚቃዊ ድራማ፣ የጠራጴዛና መረብ ኳስ፣ የሲኒማ ምሽት (ለምሳሌ የኢየሱስ ፊልም) ወይም ልዩ አመቺ ጊዜዎች እንደ ገና፣ ፋሲካ፣ ብሔራዊ በአላትና የስፖርት ዝግጅቶች፣ ለወንጌል ስርጭት ዝግጅት አመቺ ጊዜያት ናቸው።*

- በቤተክርስቲያንህ፣ በቤተእምነትህ፣ ወይም በአንድ ጓደኛህን ወይም በአንድ ቡድን የአባላት ዘመድ የሚረዳ አንድ የወንጌል መልዕክተኛ ምረጥ።
  - ለእነርሱ ባለማቋረጥ በመደበኛው ፀልይ።
  - በደብዳቤ፣ በፋክስ፣ በኢ.ሜል ወይም በስልክ ሀሳቦችን ተለዋወጥ
  - እናንተ እንደ ቡድን ልትረዷቸው ትችላላችሁ ወይም በአንድ የሐገር አቀፍ ቤተክርስቲያን ተካይ ይሰልጥኑ።
  - የሚቻል ከሆነ ጐብኛቸው።
  - ቡድንህ ወይም ቤተክርስቲያናችሁ የአጭር ጊዜ የሚሲዮን ኘሮጀክት መላክ ያስፈልጋት ይሆናል።

❖ ለእርዳታ ዳይናሚክ ቸርችስ ኢንተርናሽናልን ማግኘት ትችላላችሁ። አስደሳችና ውጤታማ ኘሮጄክት ይኖራችሁ ዘንድ ቡድናችሁን ማዘጋጀትና ለማሰልጠን የሚረዳችሁን መረጃዎች ለመላክ ደስተኞች ነን።

# የሰዎች ሰዎችን መድረስ

*ማስታወሻ:- የሚከተሉት ነጥቦች የቡድናችን አባላት የተፅዕኖ ክልላቸውን እንዲለዩ ይረዳቸዋል።*

## በሌሎች ላይ በክርስቶስ በተሳካ ሁኔታ ተፅዕኖ ለማምጣት የሚረዱ አስፈላጊ መርህዎች

ቈላስይስ 4፥2-6

***«ከማመስገን ጋር ነቅታችሁ በትጋት ጸልዩ። እኔ እስረኛ የሆንኩለትን የክርስቶስን ሚስጥር ማወጅ እንድችል፣ እግዚአብሔር የቃሉን በር እንዲከፍትልን ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ፤ ደግሞም መናገር እንደሚገባኝ ቃሉን በግልፅ እንድናገር ፀልዩልኝ። በውጭ ካሉት ሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት በጥበብ ተመላለሱ፤ በተገኘውም ዕድል ሁሉ ተጠቀሙ። ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መልስ መስጠት እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ በጨው እንደ ተቀመመ ሁልግዜ በጸጋ የተሞላ ይሁን።»***

**የተፅዕኖ ክልልህ - ከምታስበው ይልቅ ትልቅ ነው!**

አንተ የምታውቃቸው ሰዎችንና ልታውቃቸው የምትችላቸውን ሰዎች የሚያቅፍ የተፅዕኖ ክልል አለህ። አንተ የምታውቃቸው በቀጥታ የተፅዕኖ ክልልህ ውስጥ ናቸው። በዚህ የቀጥታ የተፅዕኖ ክልልህ ውስጥ ካሉ የተወሰኑት ሰዎች ጋር ምናልባት የዕለት ተዕለት ግንኙት ይኖርሃል። ከሌሎቹ ጋር ደግሞ ለተወሰኑ ጥቂት ወራት ወይም ዓመታት በኋላ ሊሆን ይችላል። የማታውቃቸው ሰዎች ነገር ግን ልታገኛቸው የምትችላቸው ሰዎች ቢሆኑም የተፅዕኖ ክልልህን ያበጁልሃል። ለምሳሌ፣ የህብረተሰብህ ቡድን አባል ወይም የጓደኛህ ጓደኛ የተፅዕኖ ክልልህ ሊሆን ይችላል።

**የቀጥተኛ የተፅዕኖ ክልል ምሳሌዎች**

1. *ማን ነበር እንድርያስን ወደ ክርስቶስ ያመጣው?* ዮሐንስ 1፥35-42__________________
2. *ማን ነበር ፊልጶስን ወደ ክርስቶስ ያመጣው?* ዮሐንስ 1፥43-49____________________

**የቀጥተኛ የተፅዕኖ ክልልህ**

ብዙዎቻችን የተፅዕኖ ክልላችንን ዳርቻ አናውቅም። የሚከተለውን ቀመር በቀጥታ የተፅዕኖ ክልልህ ውስጥ የሚኙትን ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ቁጥር ለመገመት ተጠቀምበት።

**ዘመዶች + የስራ ባልደረዶች + ጐረቤቶች + ጓደኞች + የሚታወቁ ሰዎች**

_____________+ ___________ + ____________+ ____________

ከላይ ያሉት ጠቅላላ ድምር፡- _______________________ (ጠቅላላ "*ሀ*")

ከእነዚህ ሰዎች 7ቱ ክርስቶስን ቢቀበሉ ና የራሳቸውን የተፅዕኖ ክልል መድረስ ቢችሉ፣ በእነዚህ ሰዎች በኩል ምን ያህል ሰዎችን ተፅዕኖ ልታደርግ ትችላለህ?


ከላይ (ጠቅላላ *ሀ*) x 7, _____________________ (ጠቅላላ *ለ*)

(*ሀ*) ________________ + (*ለ*) __________________ = _______________

እግዚአብሔር ልባቸው የተዘጋጀውን ወደ አዕምሮህ እንዲያመጣቸውና በሚያመጣቸው ጊዜ በድነታቸው ውስጥ አንተን ለማሳተፍ እንዲጋብዝህ እድሉን እንዲሰጥህ እንድትገነዘብ ጠይቀው።

ማድረግ ያለብን ቀዳሚው ነገር ለእንደዚህ ላሉት ግለሰቦች ለመፀለይ እራሳችንን መስጠት ነው፡፡ በነፍስ ወከፍ ባለን የተፅዕኖ ክልላችን ውስጥ ሰዎችን በአንድነት ስንጨምር፣ የቡድናችን ጠቅላላ ሰዎች ቁጥር ____________________ ይሆናል፡፡

በፀሎት 7 ሰዎችን ምረጥ፡፡ እግዚአብሔር እንደሚመራህ ለአንደኛው ከዛም ለሌላው መፀለይ ጀምር፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው ክርስቶስን ለማካፈል ጥረት አድረግ፡፡




ሁልግዜ በመደበኛነት ለ፡-

1. __________________________ 2. __________________________ 3. __________________________

4. __________________________ 5. __________________________ 6. __________________________

7. __________________________ እጸልያለሁ፡፡

ከነዚህ ሰዎች መሐል አንዱ ክርስቶስን በተቀበለ ጊዜ፣ የራሱን የተፅዕኖ ክልል እንዲደርስ ማገዝህን እርግጠኛ ሁን፡፡
**በቡድናችሁ የህብረት ግዜ ባለማቋረጥ በመደበኛነት ለእነዚህ ግለሰቦች ፀልዩ፡፡**

# ላልዳኑ ጓደኞች መፀለይ

ሁላችንም በራሳችን የተፅዕኖ ክልል ውስጥ በርካታ ሰዎች አሉን፡፡ አንዳንዶቹ ክርስቲያን ሲሆኑ፣ ሌሎች አይደሉም፡፡ እንደ ቡድን፣ በጣም ትልቅ የተፅዕኖ ክልል አለን፡፡ እንፀልይላቸው ዘንድ እና ለእነርሱ ክርስቶስን ለማካፈል ለምንፈልገው መንገድ ይረዳን ዘንድ፣ በግል የምናውቃቸውን ሰዎችንና እስካሁን ክርስቶስን ያላወቁትን ሰዎች መለየት ያስፈልገናል፡፡

# ድነትን ላላገኙ ሰዎች የመፀለያ መንገድ

በፀሎታችን መካተት የሚገባቸው ሦስት የፀሎት አቅጣጫዎች አሉ፡-

### ሀ. በሰይጣን ላይ የነጣጠረ፣ ኃጥያተኞችን የያዘ ኃይል

1. 2 ጢሞቲዎስ 2÷25-26 አንብብ። ኃጥያተኛ በሰይጣን ________________________ ነው

2. 2 ቆሮንቶስ 4÷3-4ን አንብብ። ኃጥያተኛ ለወንጌል ___________________________ ነው

ደህንነትን ያላገኘ አንድ ሰው ከመዳኑ በፊት ሁለቱ ነገሮች የግድ መሆን አለባቸው።

1. 2 ቆሮንቶስ 10÷4ን አንብብ። ከ ______________________________ ነፃ መሆን አለበት።

2. 1 ቆሮንቶስ 2÷4፣5ን አንብብ። ማን ነው አብርሆትን የሚሰጥ? ____________________

ወንጌሉን መቀበል የማይፈልግ አንድ ጓደኛ ወይም ወዳጅህን አስብ። እንዴት ነው ሰይጣን፡-
አስሯት/ሮት ያለው? (ለምሳሌ፡- በፍርሃት ፣ ኩራት፣ ሱስ፣ ዘፈን፣ ኃይማኖት) ___________
አሳውሯት/ሮት ያለው? (ለምሳሌ፡- የጓደኛ ማጣት፣ ከእንግዲህ ደስታ አይኖርም) ___________
እነዚህ በምልጃ ፀሎት ሊሰበሩ የሚችሉ ምሽጐች ናቸው።

### ለ. በክርስቲያኖች ላይ ያተኮረ

እግዚአብሔር ኃጢያተኛውን ካዘጋጀ በኋላ ወደ ክርስቲያኑ በመዘርጋት ሁለቱንም በአንድነት ያመጣቸዋል። ክርስቶስን ለሌሎች ለማካፈል እግዜአብሔር እንዲጠቀምባቸው ፍቃደኛ የሆኑ በርካታ ክርስቲያኖች ያስፈልጉናል። በማቴዎስ 9 ÷ 37-38 ___________________________

እንዴት ነበር ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ያስተማረው? _______________________________

ያ ዛሬም እግዚአብሔር የሚሰራበት መንገድ ነው።

### ሐ. በአዳኛችን ላይ ያተኮረ

ዮሐንስ 6÷44ን አንብብ። እግዚአብሔር ንስሀን እንኪሰጠው ድረስ፣ አንድ ደህንነትን ያላገኘ ሰው ከዲያቢሎስ ወጥመድ ሊያመልጥ አይችልም። 2 ጢሞቲዎስ 2÷25-26

**ላልዳኑ ሰዎች ፀልይ**
ይህ እግዚአብሔር ለሚመራህ አንድ ሰው ለድነቱ የምትፀልይበት መንገድ ነው። በሰይጣን ላይ ያለህን ስልጣን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አረጋግጥ። ሰይጣን መታዘዝ አለበት። መልቀቅም አለበት። እግዚአብሔር ለፀሎትህ መልስ መስካሪዎችን ያስነሳል። የእግዚአብሔር መንፈስ ድነት ያላገኘውን ሰው በመውቀስ ሊያቀርበውና ንሰሀን ሊጠው ይችላል። እየሱስን ብትጠይቀው፣ በልቡ በር ላይ ያንኳኳል።
**አሁን ቆም በልና ለዛ ጓደኛህ ወይም ወዳጅህ ፀልይ።**

# ለመምራት መማር
## ክፍል አምስት
## መማረክ

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው።

**ከመሪዎች ቡድንህ ጋር ከመገናኘትህ በፊት**

☐ 1. «**የህይወት ቡድናችንን ማብዛት**» የተሰኘውን ክፍል አንብብ።
አዲስ ቡድን የሚወለድበትን ሂደት ለመግለፅ ተዘጋጅ።
አዲሱን ቡድናችንን ለመጀመር ጥሩ የሆነው ቀን የቱ ነው? ቀን ____________________
የራስህን ቡድን ለመምራት በፀሎት ራስህን አዘጋጅ።

☐ 2. «**ተተኪ መሪህን መምረጥ**» የሚለውን ክፍል አንብብ። የመረጥከው

ተተኪ መሪ አለህ? ________________________ ማነው? ______________________

ለምን መረጥከው? ___________________________

________________________________________________________________________

☐ 3. *መማረክ*። «**ለራሴ አለም ያለኝ ራዕይ**» የተሰኘውን ክፍል አንብብ። ክርስቶስን ለሌሎች ለማካፈል ያለህን የራስህን መሰጠት ለማካፈል ተዘጋጅ። እንዴት ዳይናሚክ ማካፈል ስልጠና ስለ ክርስቶስ ለመመስከር መተማመን በመስጠት እየረዳህ እንዳለ አካፍል።

☐ 4. *መማረክ*። «**የራሴን አለም ለመድረስ የሚረዱ ተግባራዊ ስልቶች**» የተሰኘውን ክፍል አንብብ። ቡድናችን የትኛውን ስልት አብሮ መስራት ይወዳል?

☐ 5. *መማረክ*። «**መመስከርን የኑሮ ዘይቤ ማድረጊያ መንገድ**» የተሰኘውን ክፍል አንብብ። ለመሪህ እንደ ኑሮ ዘይቤ የመመስከር የግል ምሳሌህን ለማካፈል ተዘጋጅ።

**ከመሪህ ጋር በመሆን የሚከናወን፡-**

☐ 6. እያንዳንዱ ሰው ለሌሎች ሲመሰክር እግዚአብሔር እንዴት እየባረከው እንዳለ ይመስክር።

☐ 7. ከላይ ከ1-5 ያሉትን ነጥቦች ከተወያችሁ በኋላ ይህንን (✓) ምልክት አድርጉባቸው።

**በዚህ ወር ከቡድናችን ጋር ለመካፈል የያዝነው እቅድ፡-**

- ☐ 8. መሪው ለቡድናችን ስለ አዲስ ቡድን መወለድ እቅዶች ማካፈል ጀምር፤ እቅዶቹ እየጐለበቱ እያለ ቡድኑ ከአንተ ጋር እንዲፀልይ ጠይቅ። ቀን ____________________

- ☐ 9. እንደ ቡድን ለመስራት የወንጌል ስርጭት ስልት መምረጥና መወያየት። ቀን መድብ ____________________ የተለያዩ ኃላፊነቶችን ስጥ።

- ☐ 10. መመስከርን እንደ ኑሮዘይቤ ማድረግን አበረታታ። እንደ ቡድን ከተፅዕኖ ክልላችሁ ለተመረጡት ሰዎች መፀለዩን ቀጥሉ። የቡድኑን አባላት ለነዚህ ሰዎች ለመመስከር የፀለዩትን የፀሎት ውጤት እንዲያካፍሉ ጠይቃቸው።

**ፀሎትና መዝጊያ**

- ☐ 11. ለግል ፍላጐቶችህ እና ለቡድኑ አባላት ፍላጐቶች ፀልይ።

- ☐ 12. የክፍል ስድስት የመዘጋጃ መልመጃን በጥንቃቄ ተመልከት።

- ☐ 13. ቀን __________________ ሰዓት __________________ ቦታ __________________ ለቀጣዩ ለመምራት መማር ክፍለ ግዜአችን መድብ።

- ☐ 14. ቀን __________________ ሰዓት __________________ ቦታ __________________ ለቀጣዩ ዳይናሚክ ማካፈል ስልጠና መድብ።

# የሕይወት ቡድናችንን ማብዛት

በህይወት ቡድኖች አገልግሎት፣ በግንኙነትና በወንጌል ስርጭት ማህበረሰብን ለመድረስ ራሳችንን ሰጥተናል። የህይወት ቡድናችን አባላት በማህብረሰባቸው ውስጥ ሌሎችን በመድረስ የበለጠ ውጤታማ ሲሆኑ፣በመንፈስና በቁጥር እድገት ይኖራል። አዳዲስ ሰዎች ያለማቋረጥ ይጨመራሉ። እድገቱ እንዲቀጥል የቡድኖቹ መውለድና መባዛት በጣም አስፈላጊ ይሆናል።

የማይበዛ ቡድን የማያድግ ይሆናል። ወደ መሙላት መጠን ይደርሱና ከዚያም መውረድ ይጀምራሉ።የራሳቸውን ፍላጐት ብቻ የሚመለከቱ እራሳቸውን የሚያገለግሉ ይሆናሉ ። በእንደዚህ ያለ ሁኔታ እንግዶች አቀባበል እንደማይደረግላቸው ይሰማቸዋል። በተጨማሪም አባላት በጌታ ላይ ከመደገፍ ይልቅ እርስ በእርሳቸው ላይ ወይም በመሪው ላይ ይደገፉ ይሆናል። በቡድናችን ውስጥ በጣም ሊመቸንና የመኖራችንን ምክንያት መርሳት እንችላለን። የህይወት ቡድኖች ሌሎችን ለማገልገል መቆም አለባቸው።ያ ለእኛ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው። እንደ መሪያቸው ደስ እንዲላቸው ቡድንህን አስተምር።

## ቡድንህን ለማራባትና ለማብዛት የሚጠቅም መመሪያ

**የቡድን መጠን** - «ትንሽ ቡድን» ለፊት ለፊት ግንኙነት የሚመች ቁጥርን ያመለክታል። እያንዳንዱ ሰው በውይይቱና በማካፈሉ እንዳይሳተፍ እንዳያግዳቸው ብዙ መሆን አይገባውም። የአንድ ቡድን ቁጥር ሦስት እስኪሆን ሊያንስና አስራሁለት እስኪሆን ትልቅ ሊሆንና ውጤታማ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ማንኛውም ቁጥሩ ከአስራሁለት የበለጠ ቡድን ውጤታማነቱ እየቀነሰ ይሄዳል። አንድ ትንሽ ቡድን ከ 8-12 በመደበኛነት የሚገኙ ተካፋዮችን ሲይዝ፣ ያ ጊዜ አዲስ ቡድን የመውለጃ ግዜ ይሆናል።

ቡድናችን መራባት ቢችል፣ እግዚአብሔር ሌሎች ብዙ ሰዎችን እንደሚባርክ ራዕይ ይኑርህ።

### *ቡድናችን በብዙ እጥፍ ሊራባና የብዙ ሰዎችን ህይወት ሊባርክ ይችላል።*

**1 X 2 = 2 X 2 = 4 X 2 = 8 X 2 = 16 X 2 = 32 X 2 = 64 X 2 = 128 X 2 = 256**

እቅዳችን እያንዳንዱ ቡድን በየስድስት ወሩ አንድ አዲስ ቡድን እንዲወልድ መሆን ይገባዋል።

**የመውለድ ዝግጅት፡-** ትክክልኛ ውልደት ከመከሰቱ አስቀድሞ ፣ መሪው በዝግጅት መጠመድ አለበት።

1. ከህይወት ቡድኑ አላማዎች አንዱ መሪዎችን ማሳደግ ነው። መሪዎች ሊመለመሉና ለማጅ መሪዎች አዳዲስ ቡድኖችን ለመምራት ሊኰለብቱ ይገባል።

2. ከመጀመሪያው ጀምሮ መሪው እድገትን ለሚያመጣውና ለመዋለድ አስፈላጊ ስለሆነው ስለወንጌል ስርጭት አስፈላጊነት ቡድኑን ማስተማር አለበት። የመውለጃው ጊዜ ሲቃረብ፣ ቡድኑን ምን ሊከናወን እንደሆነ ግንዛቤን መስጠት አለበት። ለአዳዲስ ለማጅ መሪዎች በመፀለይ እና የእግዚአብሔር ጥበብና ምሪት በመጠየቅ በሂደቱ ውስጥ ይሳተፍ።

3. ስለመዋለድ ለመወያየት አንድ ጊዜ መታቀድ ይገባል። ከግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ጉዳዮች፡-
   - መቼ እና ለምን መዋለድ ይካሄዳል
   - ማነው አዲስ መሪ የሚሆነው (በመጋቢያን አመራሮች የፀደቀ)
   - ከእያንዳንዱ መሪ ጋር የሚገናኘው ማነው (እያንዳንዱ ሰው ይምረጥ)
   - እያንዳንዱ ቡድን የት ይሰብሰብ።

አዲሱ ቡድን ከመወለዱ በፊት፣ቡድኑ ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በሚገባ ጠንቅቆ ማወቅና መረዳት አለበት።

## አፅንኦት

1. ሰዎች አንድን ነገር የመደጋገም ተፈጥሮ እንዳላቸውና ለውጥን እንደሚቃወሙ አረጋግጥ፣ በተለይ ደግሞ አስቀድመው ያልተዘጋጁ ከሆነ።

2. የቀረበውን አዲስ መሪ ደግሞ ለመጠቀም መጀመር፣ በቡድኑ ፊት እድሉን መስጠትና ብቃቱን ማረጋገጥ።

3. አንድ አዲስ ቦታ ሲወሰን ስለ እርሱ በጋለ ስሜት ለመናገር ጀምር። መጓጓት የሚዛመት ነው። ሰዎች በተፈጥሮአቸው በህይወታቸው ውስጥ ያገለገላቸውን መሪንና ሌሎችን ይመርጣሉ። እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ሁለቱን ቡድኖች በአንድነት እንዲያስቀምጥ ፀልይ።

4. እንደ መሪ፣ ሰዎች ወደ አዲሱ ቡድን እንዲሄዱ በደንብ ፍቀድላቸው። ***«አንዱ በለጋስነት ይሰጣል፤ ሆኖም ይበልጥ ያገኛል ሌላው ያለመጠን ይሰስታል፤ ግን ይደኸያል።»***
   ምሳሌ 11፥24

5. ከውልደቱ ጥቂት ሳምንታት በኋላ በሽግግሩ ጊዜ ሰዎች ጠፍተው እንደሆነ ወይም አልታዩ እንደሆነ ለማየት አዲሱን መሪ አግኘው።

## የመሪዎችና የተተኪ መሪዎች እጥረት

አንድ ቡድን እስከ አስራሁለት ሰዎች ሊያድግና ለአዲስ ቡድን መሪነት የማይበቃ ምንም ተተኪ መሪ በዛ ቡድን ውስጥ ላይገኝ የሚችልበት አጋጣሚ አለ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ መሪው ፍላጐቱ እየቀረበ ሲመጣ ለራሱ አሰልጣኝ ማማከር ይገባዋል። ምናልባት የመምራት ብቃት ያለው እና አዲሱን ቡድን ሊመራ የሚችል መሪ ከውጪ ሊመደብ ይችላል። ይህ በጣም የሚፈልግ ባይሆንም ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

### እያንዳንዱ አዲስ ቡድን ከተተኪ መሪ እና ከእንግዳ ተቀባይ ጋር በመሆን መጀመር ይገባዋል።

# ተተኪ መሪህን መምረጥ

## የመሪ ምልክቶች

1. ከተጠየቀው በላይ ይሰራል፡፡
2. እስኪነገረው ድረስ አይጠብቅም (በራሱ ይጀምራል)
3. በመርህዎችና በአሰራሮች መሃል ያለውን ልዩነት ያውቃል፡፡
4. እንደ ቅደም ተከተላቸው ነገሮችን ይሰራል
5. ሀ. አላውቅም
   ለ. ተሳስቻለሁ
   ሐ. ይቅርታ ለማለት የሚችል ነው፡፡
6. ሁልጊዜ ለቡድኑ መሻሻል መንገዶችን ይፈልጋል፡፡
7. ጥሩ የግንኙነት ሰው ነው፡፡
8. ስለ ሰዎች እጦት አዛኝ ነው፡፡
9. ሁልጊዜ የሚገኝ ነው፡፡
10. ሌሎችን ወደ ላይ ያሳድጋል
11. አንድ የሆነን ሰው እርሱ የደረሰበት ቦታ ለመውሰድ የቆረጠ ነው፡፡
12. እራሱን በሌላ ሰው ለመተካት ይፈልጋል
13. ለአዳዲስ አሰራሮችና ሃሳቦች ክፍት ነው፡፡

ለማጠቃለል፣ ለሕይወት ቡድን አገልግሎት ከልብ የተሰጡና ለሰዎች በልባቸው ሸክም ያላቸው ወንዶችና ሴቶች ያስፈልጉናል፡፡ አንድ መሪ የክርስቶስን ህይወት በቅርበት ሊያጠና እና የኢየሱስን የሚሰራ እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ ኢየሱስ በሰዎች ላይ ተፅዕኖ ባመጣበት መንገድ ክርስቲያን መሪም በቤተክርስቲያን እና በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ ሰዎች ተፅዕኖ ለማምጣት መፈለግ ይኖርበታል፡፡

# ለራሴ ዓለም ያለኝ ራዕይ

ለክርስቲያኖች የዚህ ሰዓት አንገብጋቢ ፍላጐት እየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛመርቱ በሰጠው ትዕዛዝ ውስጥ የሚገኘውን ራዕይ እንደገና መያዝ ነው፡፡ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ » ማርቆስ 16፥15

ይህ ከጌታ የሆነ ታላቁ ተልዕኮ ደቀመዛሙርቱ በራሳቸው ኃይል ሊፈፅሙት ያልቻሉት አስቸጋሪ እንደ ነበር ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም መንፈስ ቅዱስ በወንዶችና በሴቶች ውስጥ አልፎ ለመንቀሳቀስ በመቻሉ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በሚታወቀው አለም የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የሰሙ የአዳዲስ ክርስቲያኖችን ምላሽ ፈጥሮ ነበር፡፡ ወንጌሉ ጣኦት የሚያመልከውን የሮማውያን ግዛት ገለባብጦ በነበረበት በእንደዚህ አይነት ኃይል የብዙ ሰዎችን ህይወት ዘልቆ ገብቶ ነበር፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ እና የወንጌሉ ኃይል ዛሬም ህያው ነው፡፡ ይሁንና የዛሬው የክርስቲያኖች ተፅዕኖ እንደ መጀመሪያ ክፍለ ዘመን እኩል አይደለም፡፡ ይሄ ደግሞ ዛሬ በአለማችን ላይ ከሚኖሩት ሰዎች ግማሽ ያህሉን በጭራሽ ወንጌል ያልሰሙ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

ጌታችን አለም ወደ ክርስቲያኖች እንድትሄድ በጭራሽ አልተናገረም ይልቁንም፣ ክርስቲያኖችን ወደ አለም እንዲሄዱና ብቻውን ለድነት የእግዚአብሔር ኃይል የሆነውን የወንጌሉን መልዕክት እንዲያስተላልፉ ነግሯቸዋል፡፡ የዚህ ትምህርት ክፍል ግብ ቡድንህን ሌሎችን በክርስቶስ ተፅዕኖ ለማድረግ ስላላቸው አቅም ለማስተማርና ለማነቃቃት እንድትችል አንተን ለመርዳት ነው፡፡

ዛሬ በርካታ ክርስቲያኖች ለሌሎች የሚሰጡትን ምስክርነት በሚጐዳና በተሸነፈ ህይወት ይመላለሳሉ። ብዙ ትኩረት በዘመናዊው ማህበረሰብ ውስጥ ስላሉት ጠቅላላ አሉታዊ ተፅዕኖ አምጪ ስለሆኑ ነገሮች ተሰጥቷል፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች እንዴት እግዚአብሔር ለአዎንታዊ ተፅዕኖ ሊጠቀምባቸው እንደሚችል ግንዛቤ አልተሰጣቸውም። ጳውሎስ ሁኔታውን እንደ፣ ***«በድካምና በፍርሃት፣ እንዲሁም በብዙ መንቀጥቀጥ»*** 1 ቆሮንቶስ 2፥3 በሚሉ ቃላት እስኪገለፅ ድረስ አለመብቃት ተሰምቶት ነበር። ብዙ ክርስቲያኖች ባላመኑት ሰዎች ምንም ተፅዕኖ ማድረግ እንዳይችሉ በጥራጥሬ ተከበዋል:ጳውሎስ በራሱ የበታችነት ስሜቶች ተሸንፎ እንዳልነበረ ማየት ያስፈልግሃል። አገልግሎቱ ሐይለኛ ነበር ፣***«እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን፤ እኔም በብርታት በውስጤ በሚሠራው በእርሱ ኃይል ሁሉ እየታገልሁ በዚህ አላማ እጥራለሁ።»*** ቈላስያስ 1፥28-29 ደፋር ወይም ጠቢብ ስለሆንክ አይደለም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ ስለሚሰራ ሊጠቀምብህ ይችላል።

# ሰዎችን መማረክ - የራሴን ዓለም ለመድረስ ተግባራዊ ስልቶች

ወንጌል መስበክ በብዙ ክርስቲያኖች ልብ ውስጥ ፍርሃትን የሚጭር ይመስላል። ለምን? ምክንያቱም አብዛኛው አማኝ እምነቱን ለአንድም ሰው በጭራሽ አካፍሎ አያውቅም። ለምን አልሆነም? ያላመኑት ሰዎች ጠማሞችና ወንጌሉን ስለሚቃወሙ ነው? አይደለም! ብዙ ሰዎች በጓደኛቸው ቤተክርስቲያን እንዲካፈሉ ሲጠየቁ «እሺ እፈልጋለው » ብለዋል። አብዛኛዎቹ ሰዎች ሲመሰክርላቸው ለወንጌል ክፍት ናቸው። ሁሉም ክርስቶስን ለመቀበል ዝግጁ አይደሉም፤ ነገር ግን ለመነጋገር ክፍት የሆኑና ግንዛቤ የሚፈልጉ ናቸው።

አለማችን እየተቀየረች ነው! ምንም ነገር ስሜት በማይሰጥበት ብጥብጥ ውስጥ ነች! ወንጌሉ ግን ስሜት ይሰጣል! ተስፋቢስ ለሆነችው አለም ተስፋ ይሰጣል፤ አብዛኛው ሰው መስማት ይፈልጋል።

አግባብነት ያለውንና ግልፅ የሆነውን አሰራር ልንመርጥ ያስፈልገናል።

1. **ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያን መጋበዝ።**
   ጓደኛህን ወይም የምታውቀውን ሰው ወደ ትንንሽ ቡድኖች ወይም ቤተክርስቲያን እንዲካፈል መጋበዝ ልምድህ አድርገው።

2. **የቤት ለቤት መጠይቅ** (ናሙናውን በዳይናሚክ ማካፈል ትምህርት ስድስት ተመልከት)
   ይህ ለማድረግ ቀላልና በጣም ውጤታማ ነው። በቅርብ ጊዜ አንድ ሰው ከአጋሩ ጋር በአንድ ሰዓት ውስጥ 12 ቤቶችን አንኳኩ። ከ 8 ሰዎች ጋር ተነጋገሩ፣ ለ5 ሰዎች ወንጌል መስክሩና ሦስቱ ክርስቶስን ተቀበሉ። ሰዎች በጣም ክፍት ናቸው፣ ከእንግዳ ጋር ይነጋገራሉ። አንዳንድ ጊዜ እንኳ በበራፋቸው ላይ በመሆን ክርስቶስን ይቀበላሉ።

3. **የግል ምስክርነት**

አጋጣሚውን ባገኘህበት ጊዜ ሁሉ አጭርና ግልፅ በሆነ መልኩ ምስክርነትህን አካፍል። እግዚአብሔር ለአንተ ያደረገልህን ሰዎች መስማት ያስፈልጋቸዋል። ማንኛውም ክርስቲያን የርሱን/የእርሷን ምስክርነት የሚገልፅበት ቀላል መንገድ ሊኖረው ይገባል። ጓደኞችህን የህይወት ታሪካቸውን ሲያዘጋጁ አግዛቸው። የአንድ ለአንድ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ክፍል ስምንት ወርክሾፕን፣ ዳይናሚክ ማካፈል ትምህርት አንድ ወይም የሚመሩ መሪዎች ክፍል አምስትን ተጠቀም።

4. **የወንጌል መመስከሪያ ትንንሽ መፃህፍት**
እግዚአብሔርን በግል ማወቅ ወይም አራቱ መንፈሳዊ ህጐችና የመንፈስ ቅድስ ትንንሽ የወንጌል መመስከሪያ መፅሀፍትን ለመመስከር ትዘጋጅ ዘንድ ሁልግዜ በኪስህ ወይም በዋሌትህ ውስጥ ያዝ።

5. **ፊልሞች ወይም ቪዲዮዎች**
• የኢየሱስ ፊልም • ጋብቻ • ወላጅና አፍላ ወጣት • ሱሰኝነት ወ.ዘ.ተ

ከእነዚህ አንዱን ለጓደኛ በመስጠትና በመከታተል ወይም በምሽት ፊልም ለማየት ጓደኛን መጋበዝ። ይህ በማንኛውም ሰዓት ሊደረግ ይችላል። ልዩ ጊዜያት በተለይ እንደ ገና ወይም ፋሲካ ያሉት አመቺ ናቸው።

ለምሳሌ በትንሹ ቡድንህ ውስጥ የኢየሱስ ፊልምን ለማካፈል ትፈልግ ይሆናል። እያንዳንዱ ሰው ወይም ጥንድ የሚፈልጉ ከሆነ ቪዲዮውን በመጠቀም ጐረቤቶቻቸውን ወይም ጓደኞቻቸውን ቪዲዮውን ለማየት በምሽት መጋበዝ። የተቀረው የቡድኑ አባላት ለተጋበዙት ጥንዶችና ሰዎች ለመጸለይ ራሳቸውን ይስጡ። ፊልሙ ከታየ በኂላ የሚከተሉት ጥያቄዎች መጠየቅ ይኖርባቸዋል።

- ስለፊልሙ ምን ታስባለህ?
- መልእክቱ ለአንተ ስሜት ሰጥቶሃል?
- ፊልሙ እንደሚያሳስበው ከዚህ በፊት ክርስቶስን ወደ ህይወትህ ጋብዘህ ነበር? ካልሆነ እንዲህ ብለህ ጠይቅ።
- መጋበዝ ትፈልጋለህ ወይስ አትፈልግም።

6. የአንድነት ጊዜ እንዴት የአብሮነት ግዜ እንደሚዘጋጅና እንደሚደረግ ግልፅ መመሪያ ለማግኘት ወደ ክፍል አምስት የሚመሩ መሪዎች ሂድ። ከትንሹ ቡድንህ ወይም ከሌሎች ጓደኞችህ ጋር ለመጠቀም በጣም ጥሩ ስልት ነው።

7. **የአንድ ለአንድ የወንጌል ስርጭት - ዳይናሚክ ማካፈል**

የአንድ ለአንድ የመባዛት ተፈጥሮ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች እንዲደረሱ ያደርጋል። ለመጀመሪያ ጊዜ ሲተገበር ትዕግስትን ይጠይቃል ምክንያቱም ከትንሽ ቁጥር ስለሚጀምር ነው። ሌሎችን የሚያሰለጥኑ ሌሎች ሰዎችን ስታሰለጥን ቁጥሩ እየጨመረ ይሄዳል፤ ልክ አንድ ሰው አሰልጥነህ እንዳበቃህ ወዲያው ሌላ ሰው ለማሰልጠን ጀምር። ለቤት ከቤት ጉብኝት ከመጋቢህ ወይም ከጉብኝት አስተባባሪው ጋር መገናኘት። በቤተክርስትያን ያለ እያንዳንዱ አገልግሎት ያገኛቸውን እያንዳንዱን ሰው የእንግዳ ግንኙነት ሪፖርት ቅፅ እንዲሞሉ አድርጋቸው። በተፅዕኖ ክልልህ ውስጥ ያሉ ሰዎችን የስም ዝርዝር ማስፈርህን ቀጥል። ለእያንዳንዱ ሰው ለመፀለይና ክርስቶስን ለመመስከር ሞክር።

8. **እንደ ህይወት ዘይቤ ክርስቶስን መስበክ።**
በየትኛውም ስፍራ ለማንም ሰው ሁልግዜ ለማካፍል የተዘጋጀህ ሁን። ለበለጠ ግንዛቤ የሚቀጥለውን ገፅ ተመልከት።

# ሰዎችን መማረክ - መመስከርን እንደ ህይወት ዘይቤ የማድረጊያ መንገድ

### ሀ. ለእግዚአብሔርና ለሰዎች የተገኘህ ሁን

2ጢሞቲዎስ 4፥2 ሀን አንብብ፡፡ ለአንተ ይህ ቁጥር ምን ማለት ነው፡፡
እግዚአብሔር ከችሎታህ ይልቅ በመገኘትህ የበለጠ ያስደስተዋል፡፡ ለእርሱ ከተገኝህለት ሰዎችን በአንተ ወደ ክርስቶስ ያመጣቸዋል፡፡

### ለ. ለምስክርነት እግዚአብሔር እድሉን እንዲሰጥህ ጠይቀው፡፡

1. ለይተህ ፀልይ፡፡ እግዚአብሔር መለኮታዊ ቀጠሮዎችን/ግንኙነቶችን እንዲያዘጋጅ ፀልይ፣ ወደ አንድ ሰው እንዲመራህ ጠይቀው፡፡
2. ከአንድ ሰው ጋር ለጥቂት ደቂቃዎች ለብቻችሁ ከሆናችሁ ያንን እንደ ፀሎት መልስህ አድርገህ ቁጠር፡፡
3. ምስክርነት እንደ እድል እንጂ እንደ ግዴታ አድርገህ አትቁጠር፡፡

### ሐ. ሰዎችን ባሉበት ቦታ አግኛቸው፡-

ብዙ ክርስቲያኖች ትንሽ እድል ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች በመተው አብዛኛውን ጊዜያቸውን ከአንድ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ወደ ሌላው በመሄድ ያጠፉታል፡፡

ክርስቶስን ክርስቲያን ላልሆኑት መመስከር ትችል ዘንድ እነርሱ ወዳሉበት መሄድ አለብህ፡፡ ጌታ እድሉን በሰጠህ ጊዜ ለመመስከር ንቁ ሁን፡፡

### መ. ለእያንዳንዱ ለምታገኘው ሰው እግዚአብሔር ፍቅርን እንዲሰጥህ ጠይቀው፡፡

1. የወዳጅነት መልክ አሳይ

2. ጥያቄ በመጠየቅ መነጋገርህን ጀምር፡፡ የት፣ ማን፣ እንዴት፣ ምን፣ መቼ እና ለምን የሚሉት ጥያቄዎች ንግግርህን ለማጐልበት ይረዱሃል፡፡
   ሀ. ዮሐንስ 4፥7ን አንብብ፡፡ በጉድጓድ አጠገብ የነበረችውን ሴት ኢየሱስ ምን ብሎ ነበር የጠየቃት?

   ______________________________________________

   ለምን ነበር ይህንን ጥያቄ የጠየቃት?______________________________

   ለ. የሐዋርያት ስራ 8፥30ን አንብብ፡፡ ፊሊጶስ የጠየቀው ጥያቄ ምን ነበር?__________

   ለምንድነው ይሄንን ጥያቄ የጠየቀው?____________________________

3. ለመጠይቅ የቀረቡ ጥቂት ጥያቄዎች
   ሀ. ጐረቤት
   «ጤናይስጥልኝ ስሜ ____________ ይባላል፡፡ አንተን የማግኘት እድል ማግኘት እፈልጋለሁ፡፡ ለምን ያህል ግዜ እዚህ አካባቢ ኖርክ?»
   ለ. አብሮ ለሚጓዝ መንገደኛ
   «ጤናይስጥልኝ ስሜ _____________ ይባላል፡፡ ወዴት እየተጓዝክ ነው?»

ሐ. ሌሎች

«በዚህ ከተማ ነዋሪ ነህ?»
«ምን እየሰራህ ነው የምትተዳደረው»
«ላግዝህ?»_________________________ ልትረዳኝ ትችላለህ?»

**ሠ. ስለክርስቶስ መናገር፦**

የሐዋርያት ስራ 8፥43 አንብብ። ስለአማኞች ምን ይላል? _________________________

የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች በሚሄዱበት ስፍራ በእለት ተዕለት የሰዎች ግንኙነት የክርስቶስን የምስራች ቃል ይመሰክሩ ነበር። ዛሬ የሰዎችን ፍላጐት ለማሟላት ለሚረዱ ለበርካታ አጋጣሚዎች አይናችን ሊከፈትና ክርሰቶስን ልንመሰክር ይገባናል። አንተ ልዩና በሌሎች ሊኮረጅ የማይችል የራስህ የተፅዕኖ ክልል ያለህ ሰው ነህ። ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ልምምድህን በማካፈልና ከዚያም ወንጌሉን ለእነርሱ ለማካፈል የሚረዳህን ትንሽ መሽጋገሪያ በመጠቀም ከግለሰቡ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት መመስረት ጀምር።

**እንደ አራቱ መንፈሳዊ ህጐች ወይም እግዚአብሔርን በግል ለማወቅ ትፈልጋህ? የሚለውን የወንጌል መመስከሪያ ትንንሽ መፅሀፍ በመጠቀም በመመስከር ሂደት ውስጥ የሚያገለግሉ የናሙና መሽጋገሪያዎች።**

1. «በእውነት ትርጉም የምትሰጥ ትንሽ መፅሀፍ ሳጠና ነበር። እንዳካፍልህ ትወዳልህ? »
2. «ክርስቲያን ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚገልፅ ትንሽ መፅሀፍ አለኝ። እንዳካፍልህ ትወዳለህ?»
3. አጭር የግል ምስክርነት ከሰጠህ በኋላ እንዲህ በል፣ «እስቲ የክርስቶስ ተከታይህ በመሆን ውስጥ ምን ምንን እንደማያካትት ላሳይህ።»
4. «ስለመንፈሳዊ ነገሮች አስበህ ታውቃለህ?» ወይም «ስለመንፈሳዊ ነገሮች መስማት ደስተኛ ነህ?»
5. «እንዴት ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሁኑ ህይወት ጋር እንደሚገናኝ ላካፍልህ ትወዳለህ? ትንሽ ደቂቃ ይኖርሃል?»
6. «በህይወትህ ውስጥ የእግዚአብሔር ስለመሆንህ እርግጠኛ ወደሆንክበት እና አሁን ብትሞት ወደ መንግስት ሰማይ ለመግባትህ እርግጠኛ ወደሆንክበት ስፍራ ደርሰሃል?» አዎ ካለህ « ዛሬ ብትሞትና በእግዚአብሔር ፊት ቆመህ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ቢጠይቅህ፣ ለምንድነው ወደ መንግስቴ እንድትገባ የምፈቅድልህ? ምላሽ ምንድነው?» እርግጠኛ ካልሆነ እንዲህ በል፣ «እንዴት እርግጠኛ መሆን እንደምችል ላካፍልህ ትወዳልህ?»

የአንተና የእግዚአብሔርን ፍቅር ለማካፈል እዱሉን ላገኝህባቸው የተለያዩ ሰዎች የሚሆን አመቺ ስልቶችን ተጠቀም።

**አስታውስ፦**
**ለእግዚአብሔርና ለሰዎች ለመገኘት**
**እግዚአብሔር ለመመስከር እድሎችን እንዲሰጥህ ለመጠየቅ**
**ሰዎችን ባሉበት ቦታ ለማግኘት**
**እግዚአብሔር የምታገኘውን ሰው ሁሉ የምትወድበትን አቅም እንዲሰጥህ ለመጠየቅ።**
**ስለ ክርስቶስ ለመናገር**

እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስን የምስራች ቃል ሰታከፍልና ሌሎችም ተመሳሳይ ስራ እንዲሰሩ ስታሰለጥን ይባርክህ!

# ለመምራት መማር
## ክፍል ስድስት
## ስራ (አገልግሎት)

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው።

**ከመሪዎች ቡድንህ ጋር ከመገናኘትህ በፊት**

☐ 1. **አስተማማኝ አካባቢን መፍጠር** የሚለውን ክፍል አንብብ። ለሌሎች መገዛት ምን እንደሆነና ለቡድናችን ያለውን ጥቅም ለመወያየት ተዘጋጅ።

☐ 2. **የቡድናችን ጠንካራ ጐን የመለያ መንገዶች** የሚለውን ክፍል አንብብ ከመሪህ ጋር የቡድንህ አባላትን የራሳቸው መንፈሳዊ ስጦታዎችንና ጠንካራ ጐኖችን ለመለየት የሚረዳ ዕቅድ ላይ ለማካፈል ተዘጋጅተህ ና።

☐ 3. **ስራ (አገልግል**) የሚለውን ክፍል አንብብ። ይህ የቡድናችን አምስተኛ አላማ ነው።

☐ 4. የአንተን የመንፈሳዊ ስጦታ መለያ አጠናቅና ያገኘኸውን ውጤት ለመሪህ ለማካፈል ተዘጋጅ።

**ከመሪህ ጋር በመሆን የሚፈፀም**

☐ 5. የግል ፀሎትና ምስጋና ተከፋፈሉ

☐ 6. ከላይ ከ1-4 ያሉት ነጥቦች ከተወያያችሁ በኋላ ይህንን (✓) ምልክት አድርጉበት።

**በዚህ ወር ከቡድናችን ጋር ለመካፈል የያዝነው እቅድ፦**

☐ 7. ለአዲሱ ቡድን መወለድ የተያዘውን ዕቅድ ማጠናቀቅ። እያንዳንዱ ሰው በየትኛው ቡድን እንደሚካፈል እንዲወስን መርዳትህን እርግጠኛ ሁን።

☐ 8. ከቡድኑ ጋር በወንጌል ስርጭቱ ዝግጅት ስለተገኘው ውጤት ተደሰት

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 9. ለግል ፍላጐቶችህ እና ለቡድኑ አባላት ፍላጐቶች ፀልይ፡፡

☐ 10. ቀን ________________ ሰዓት ________________ ቦታ ________________
ለቀጣዩ ለመምራት መማር ክፍለ ግዜአችን መድብ፡፡

☐ 11. ቀን ________________ ሰዓት ________________ ቦታ ________________
ለቀጣዩ ዳይናሚክ ማካፈል ስልጠና መድብ፡፡

☐ 12. የፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ክፍለ ጊዜዎችን መካፈል፡፡
ቀን ________________ሰዓት ________________ ቦታ ________________

☐ 13. እንደ መሪ የምስክር ወረቀት መቀበል፡፡

☐ 14. የራስህን ቡድን መጀመር፡፡ ቀን ________________

☐ 15. ከ ________________ አሰልጣኝህን ለመገናኘት ጊዜ አመቻች

# አስተማማኝ አካባቢን መፍጠር

በአራተኛው ክፍል ውስጥ ግንኙነት በሐቀኝነት እንደሚመሰረትና ሐቀኝነትም ከፍቅርና ከመተማመን እንደሚመጣ ተምረናል። ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር እና በእግዚአብሔር መታመን ወይም በሰዎች መታመን እነርሱን ለማወቅ በጣም እየቀረብናቸው ስንመጣ በጊዜ ውስጥ የሚመጣ ይሆናል። የህይወት ቡድናችን አስተማማኝ ስፍራ ሊሆን ያስፈልገዋል፤ ስለሆነም እውነተኛ ማንነታችንን መደበቅ አያስፈልገንም ወይም አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው ለመሆን አናስመስልም። ቡድኑ ግልፅና እውነተኛ ይሆን ዘንድ፣ መሪው የራሱን ግልፅነት በማሳየት ግንባር ቀደም መሆን ያስፈልገዋል። መሪው የቡድኑን አባላት ራሳቸውን፣ እግዚአብሔር እና ሌሎችን እንዲያውቁና እንዲገነዘቡ ሊረዳቸው ይችላል። ለእያንዳንዳችን ጠንካራ ጐኖች መገዛትን በመማርና እርስ በእርስ ደካማ ጐኖች በመሸፈን አስተማማኝ አካባቢን መፍጠር እንችላለን።

## ለእግዚአብሔርና እርስ በእርስ መገዛት

መገዛት የሚለው ቃል ልክ ካንሰር እና ሞት እንደሚለው ቃል በአብዛኞቻችንን ልብ ውስጥ ፍርሃትን ይጭራል። ይህ የሆነበት ምክንያቱ መገዛት ሞት ስለሆነ ነው። ለፍቃዴ መሞት፣ ለራሴ መንገድ መሞት፣ ለራሴም ወይም ለማንኛውም ውድ ነው ብዬ ለያዝኩት ነገር መሞት ነው።

ሞትን እንደ መጨረሻ ፍፃሜ ካየነው፣ ይህ በጣም አሉታዊና ሊወገድ የሚገባ ነው። እግዜአብሔር በጭራሽ በዛ መንገድ አያየውም። ለእርሱ፣ ሞት ወደ እርሱ ህይወት እንገባ ዘንድ በእርሱ በኩል ማለፍ ግዴታችን የሆነ አይቀሬው በር ነው።
እርሱ የሁልግዜ የመፅሀፍ ቅድስ ርዕስ ጉዳይ ነው። የሚከተለውን ተመልከት፡-

> ***«የኢየሱስ ሕይወት ሟች በሆነው ሥጋችን እንዲገለጥ፣ እኛ ሕያዋን የሆንን ሁልግዜ ስለ ኢየሱስ ለሞት አልፈን እንሰጣለንና።»*** **2 ቆሮንቶስ** 4፥11
>
> ***«እውነት እላችኋለሁ፤ የስንዴ ቅንጣት መሬት ላይ ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።»*** ዮሐንስ 12፥24

ገላትያ 2፥20 በመጀመሪያ ***«እኔ አልኖርምን»*** መለማመድ አለብን። ***«ነገር ግን ክርስቶስ»*** ን ከመለማመዳችን በፊት፤ ያ የእግዚአብሔር መንገድ ነው።

መገዛት ከሰዎች ጋር በፈቃደኝነት የምናደርገው ስምምነት አይደለም። ነገር ግን መገዛት ከልብ ይመነጫል። እንደ ክርስቶስ አካል የተሰጠህን ነገር ሁሉ ማስገዛት ትችል ዘንድ እግዚአብሔር በሌሎች እያደረገ ባለው ነገር እመን።

ጠንካራ ጐናችንን ማወጅን መማር ያስፈልገናል። ጠንካራ ጐናችንን ለማጉላትም መጀመሪያ መለየት ያስፈልገናል። አንዴ በቡድኑ ውስጥ በሌሎች ሰዎች ህይወት ውስጥ ባሉት ጠንካራ ጐኖች ከተስማማን ለእነዛ ጠንካራ ጐኖች እራሳችንን ማስገዛት ይኖርብናል። ይሄ ለዛ ሰው የክርስቶስን አካል የሚጠቅምበትን ጠንካራ ጐኖቹን በሌሎች ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድር ፈቃድ ይሰጠዋል።

## ቡድናችን ጠንካራ ጐኖቹን እንዲለይ የምንረዳበት መንገድ

1. የራስህን መንፈሳዊ ስጦታዎች ለመለየት "**የመንፈሳዊ ስጦታዎች መለያ**" ቅፅን ሙላ።
2. የ "**መንፈሳዊ ስጦታዎች መለያ**" ቅፅ በቂ ግልባጭ ለእያንዳንዱ የቡድን አባል አግኝ (የማዘዣውን ፎርም እየው) እንዴት በራሳቸው ህይወት ውስጥ እንደሚሰሩ ግለፅላቸው። ይሄንን ጥናት በራሳቸው ሊያጠናቅቁት ይችላሉ።

3. በቡድኑ ውስጥ፣ ግንዛቤ እንዲኖራቸው መረዳትና የክርስቶስን አካል ያገለግሉ ዘንድ እግዚአብሔር ስጦታን እንደሰጣቸው አድንቅ፡፡
4. የቡድኑ አባላት የእያንዳንዱን ሰው ስጦታዎችና ጠንካራ ጐኖች እንዲመሰክር እርዳቸው፡፡

# ጠንካራ ጐናችንን መለየት

- ለእያንዳንዱ ሰው ባዶ ወረቀት መስጠት፡፡
- በቡድንህ ውስጥ ያለ አንድ ሰው መምረጥ፡፡ ሌሎች የቡድኑ አባላት የዛን የመጀመሪያ ሰው ጠንካራ ጐኖች ናቸው ብለው የለያቸውን ማካፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ፡- ተባባሪነቱን፣ ተንከባካቢነቱን፣ ተግባቢነቱ፣ ብልህነቱን ወ.ዘ.ተ
- መሪው እንዲህ ብሎ ይጠይቅ፣ «የዚህ ሰው መንፈሳዊ ስጦታዎች ምንድን ናቸው?»
- እየተገመገሙ ያሉት ሰዎች ስለራሳቸው ከቡድኑ የተነገራቸውን በእያንዳንዱ ጠንካራ ጐናቸው እና ስጦታዎች መስማማታቸውን ያሳውቁ፡፡
- እንደ ቡድን በእያንዳንዱ ጠንካራ ጐንና ስጦታ ላይ መስማማታችሁን አሳውቁ ከዚያም ለግለሰቡ ጠንካራ ጐኖችና ስጦታዎች ትገዙ እንደሆን ተወያዩ፡፡
- ይሄንን ሁሉ ሂደት ጊዜው እስከፈቀደ ድረስ ለእያንዳንዱ ሰው መድገም ወይም በሚቀጥለው ሳምንት ማድረግ፡፡

ለእርስ በእርሳችን ጠንካራጐኖች በመገዛት እርስ በእርስ ሙሉ እንሆናለን፣ ለምሳሌ ምናልባት እኔ አንተ ጠንካራ በሆንክበት ጉዳይ ደካማ ልሆን እችላለሁ ግን ደግሞ አንተ ደካማ በሆንክበት ጉዳይ ጠንካራ ነኝ፡፡ እንደ አንድ ሰው አብሮ በመስራት፣ በሁሉም አቅጣጫ ጠንካራ ጐኖች ሊኖሩን ይችላል፡፡

# ሥራ (አገልግሎት)

## ሌሎችን የሚያስተምሩና የሚያሰለጥኑ መሪዎችን ለማጐልበት

አገልግሎትና መልካም ስራዎች ከክርስቲያኖች ፍቅርና ከመንፈሳዊ ስጦታዎች የሚወጡ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ ኢየሱስ ሰዎችን ይመሩ ዘንድ የተወሰኑ ግለሰቦችን ጠርቷል፤ እናም ብዙውን ጊዜውን እነርሱን ወደ መሪነት በማጐልበት አሳልፏል፡፡ ዛሬም መሪዎችን ማጐልበት ይኖርብናል፣ ምክንያቱም ያለ እነርሱ ህዝቡ የክርስቶስን አገልግሎት ሊፈፅም አይችልም፡፡

> ***«በብዙ ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ፡፡»*** 2ጢሞዊዎስ 2÷2

> ***«አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤ ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው፣ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው፡፡»*** ኤፌሶን 4÷11-13

*«ማንም ኤጲስቆጶስነትን ቢፈልግ፣ መልካም ሥራን ይመኛል» የሚለው ቃል የታመነ ነው።* 1ጢሞቴዎስ 3፥1

*«በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም። ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤ የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን፤ የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና።»* ማቴዎስ 20፥26-28

**ደቀመዝሙርነትን መስራት (ማገልገል)** (አንድ ለአንድ በእያንዳንዱ ሳምንት አንድ ክፍል በማጠናቀቅ) (ለማጅ መሪው ወይም መሪው ያስተባብር)

- በዚህ የስልጠና ጊዜ አሰልጣኙና ሰልጣኙ ከዳይናሚክ መሰረታዊ አልያም ከዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ወይም ከዳይናሚክ ማካፈል አንድ ክፍል በእያንዳንዱ ሳምንት ለማጠናቀቅ በሚመቻቸው ሰዓትና ቦታ ይገናኙ።

- መንፈሳዊ ስጦታዎችን መገንዘብና በተግባር ላይ ማዋል።

- የራስህን የሕይወት ቡድን ጀምረህ ሳለ አንተ ለተተኪ መሪህ ለመምራት መማር ክፍለ ጊዜዎችን ስጥ።

- እንደ ሕይወት ቡድን መሪ በእድገትህ ለመቀጠል፣ በአሰልጣኞችሁ ክትትል ስር ሆነህ የሚመሩ መሪዎች ክፍለ ጊዜዎችን ተካፈል።

# የመንፈሳዊ ስጦታዎችን መለየት

ከእግዚአብሔር የተሰጠህን መንፈሳዊ ስጦታዎች እንድትለይና እንድታጕለብት ለማገዝ የተዘጋጀ መገምገሚያ

# የመንፈሳዊ ስጦታዎች መለያውን የመጠቀሚያ መንገድ

1. በራስህ በሕይወትህ እውነት የሆነውን ከ 0 - 4 ዋጋ ያለውን ዐ.ነገር በመምረጥ እያንዳንዱን ጥያቄ አንብብና ራስህን ገምግም

2. ጥያቄዎችን ስታጠናቅቅ ለእያንዳንዱ ተርታ ጠቅላላ ድምር አስቀምጥ ለምሳሌ፦ ተራ ሀ፣ለ፣ሐ ወ.ዘ.ተ

3. በርካታ ከፍተኛ ነጥቦችን አክብብ። ስጦታውን ለመለየት የነጥብ ማስፈሪያ ገፁን ግለጥና ከፍተኛ ነጥቦች ውስጥ ያሉትን ስጦታዎች ፃፍ።

4. የስጦታውን ትርጉሞች በማጥናት ከእርሱ ጋር የሚገኙትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች ተመልከት። ይሄ ስጦታህን እንድትገነዘብና እንድታደንቅ ይረዳሃል።

5. ይሄ የመለያ ሂደቱ አንድ ክፍል ብቻ ነው። እግዚአብሔር የሰጠህን ሌሎች ችሎታዎችህን ማረጋገጥ እንድትችል ሌሎች መንገዶችንም ተጠቀም። የሕይወት ቡድናችን አንዳችን ለአንዳችን ፀጋ ስንገዛና በፀጋችን ሌሎችን ስናገለግል ፀጋዎቻችንን ለማረጋገጥና ለመለማመድ ከተመረጡት ቦታዎች አንዱ ይሆናል።

# መንፈሳዊ ስጦታዎችን የመለያ ጥያቄዎች

1. ሰዎች የማያዩዋቸውን ከመድረክ ውጪ የሆኑ ጥቃቅን የሚመስሉ ቀዳዳዎችን መድፈን ደስ ይለኛል
2. በማንኛውም ነገር ላይ መሪ ሲጠፋ የተዝረከረከውን ነገር ለማስተካከል ራሴን ስመራ አገኘዋለሁ፡፡
3. የተቸገሩ ሰዎችን ማብላትና መጠለያ መስጠት ያረካኛል፡፡
4. በነገሮች መሃል የችግሮችን መንስኤ ለይቶ የማውጣትና የሚያስከፍለውን ዋጋ ከፍሎ መፍታት ደስ ይለኛል፡፡
5. ሐሳቦችን፣ ሰዎችንና ፕሮጀክቶቸን የማጠናቀርና የማደራጀት ብቃት እንዳለኝ ይሰማኛል፡፡
6. ሰዎች ጥሩ መንፈሳዊ ግንዛቤ እንዳለኝ ይነግሩኛል፡፡
7. ለእግዚአብሔር ክብር ትላልቅ ነገሮችን ማከናወን እንደምችል የልብ መተማመን አለኝ፡፡
8. በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ እንድዘምር ወይም መሣሪያ እንድጫወት ሰዎች ይጋብዙኛል፡፡
9. እግዚአብሔር በማላውቀው ቋንቋ ወንጌልን ለሌሎች እንድመሰክር ሲጠቀምብኝ አይቻለሁ፡፡
10. በፀሎቴ የማይቻል የሚመስለውን እግዚአብሔር ሲለውጥ አስተውያለሁ፡፡
11. በእጄ አንዳንድ የፈጠራ ሥራዎችን መሥራትና ቅርጻቅርጽ የመሥራት ችሎታ እንዳለኝ አውቃለሁ፡፡
12. በተደጋጋሚ በፀሎቴ ሰዎች ከበሽታ ሲፈወሱ አጋጥሞኛል ፡፡
13. ለተቸገሩ ገንዘብ መስጠት ደስ ይለኛል፡፡
14. በሆስፒታል፣ በእሥር ቤትና እንደዚሁም በመጠለያ ሥፍራዎች ያሉትን ሰዎች መጎብኘትና መርዳት ደስ ይለኛል፡፡
15. ብዙ ጊዜ ከባባድ ለሚባሉ ችግሮች መፍትሔን የማፍለቅ ጥልቅ መረዳት ያለኝ ይመስለኛል፡፡
16. በቤተክርስቲያን አካባቢ ለሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮች ሰዎች መፍትሄ ሲያጡባቸው በኔ ዘንድ መፍትሔአቸው እንዳለ የሚሰማኝ ጊዜ ብዙ ነው፡፡
17. ተስፋ ለቆረጡ ሰዎች ምክርንና መፅናናትን መስጠት ደስ ይለኛል፡፡
18. አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጥልቀት አጥንቼ የተረዳሁትን ነገር ለሌሎች መካፈል ደስ ይለኛል፡፡
19. አዳዲስ ክርስቲያኖችን ማሣደግ እንዳለብኝ ይሰማኛል፡፡ አሁን እንኳን በሥሬ ያሉ የማሣድጋቸው አዳዲስ አማኞች አሉ፡፡
20. ሌሎች ሰዎች መንፈሳዊ በሆኑ ጉዳዮች ስልጣን እንዳለው ሰው ያከብሩኛል፡፡
21. የውጪ ሃገር ቋንቋን የመማር ፍላጎትና ችሎታ እንዳለኝ አውቃለሁ፡፡
22. በሕዝብ ፊትና በመድረክ የመናገር ጥሩ ብቃት እንዳለኝ ይታወቀኛል፤ ሰዎችም ንግግሬን ይወዱልኛል፡፡
23. ከማያምኑ ሰዎች ጋር ስለጌታ እየተናገሩ ጊዜ ማሳለፍ ያረካኛል፡፡
24. ለረጅም ጊዜ በፀሎት መቆየት ደስ ያረካኛል፡፡

25. ፓስተሮቼንና ሌሎች አገልጋዮችን በመርዳት እነሱን ከውጥረት ማሣረፍ ያረካኛል፡፡
26. በሰዎች መካከል መሪ ሆኖ የመመረጥ ዕድል ብዙ ጊዜ ያጋጥመኛል፡፡
27. የሚጎበኙኝ እንግዶቼን ደስ ማሰኘትና ማርካት ያስደስተኛል፡፡
28. በትንሹም በትልቁም ሌሎችን ማገልገል ያረካኛል፡፡
29. በደንብ መዘጋጀትና ዕቅድ በማውጣት የማምንና የሚሳካልኝ ሰው ነኝ፡፡
30. የሰዎችን ባህሪ ለይቼ የማወቅና እንደዚሁም መንፈሣዊ ችግሮቻቸውን የመለየት ስጦታ ያለኝ ይመስለኛል፡፡
31. እግዚአብሔር አንዷን ቤተክርስቲያን በ10,000 ምዕመን ሊባርካት እንደሚችል አምናለሁ፡፡
32. በኳየር አገልግሎት ብሣተፍ ጥሩ የምዘምር ይመስለኛል፡፡
33. በልሳን መፀለይ ልዩ ትርጉምና ደስታ የሚሰጠኝ ሰው ነኝ፡፡
34. እግዚአብሔር በሰዎች የማይገመተውን በኔ አልፎ ሲሠራ አይቻለሁ፡፡
35. የስፌት ስራን፣ የብረት ስራንና የአናጢነት ሥራን የመሣሠሉ የእጅ ሥራዎች መሥራት እወዳለሁ፡፡
36. ፀሎቴ ሰዎችን ሲፈውስ ብዙ ጊዜ አያለሁ፡፡
37. ለቤተክርስቲያን ሥራ ከአሥራቴ በላይ መስጠት ደስ ይለኛል፡፡
38. ለተጎዱና መጽናናት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ርህራሄ ይሰማኛል ከነሱ ጋርም ጊዜ ማሳለፍ ያስደስተኛል፡፡
39. ሰዎች ግራ በሚገቡባቸው ነገሮች ላይ ጥንቃቄ የተሞላበት ምርጫ እንዳደርግ ብዙ ጊዜ ጌታ ይረዳኛል፡፡
40. በእግዛአብሔር ቃል ውስጥ የሚገኙ ከባባድ ጥቅሶችን ትርጉም ለመረዳት ጥረት የማድረግ ዝንባሌ አለኝ ፤ደግሞም ከሌሎች በተሻለ ይሳካልኛል፡፡
41. ሰዎች ችግሮቻቸውን ለኔ ለመንገር ይቀናቸዋል እኔም አበረታታቸዋለሁ፡፡
42. በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከባባድ ጥያቄዎች ሲነሱ ውስጤ መልሳቸውን በማግኘት ጥማት ይሞላል፡፡
43. ቅዱሳን በዚህ ዓለም ተፅዕኖ እንዳይጎዱና ሕይወታቸው እንዳይበከል ጥረት አደርጋለሁ፡፡
44. በየቦታው አዳዲስ አብያተክርስቲያናትን መክፈትና ማጠናከር የሚያስደስተኝ ያህል ሌላ ነገር የለም፡፡
45. አዳዲስ ቋንቋዎችንና አኗኗሮችን የመልመድ ተሰጥኦ አለኝ፡፡ በዚህም ምክንያት በማላውቀው አገር ወንጌልን ባገለግል ደስተኛ የምሆን ይመስለኛል፡፡
46. ሰዎች ያሉትን ቢሉም ያመንኩበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ መናገርና መስበክ አይከብደኝም፡፡

47. ብዙ ጊዜ ነፍሣት ጌታን እንዲቀበሉ መጋበዝ ዳገት አይሆንብኝም፡፡

48. ጌታ በፀሎቴ እንደሚታደጋቸው በማመን በቀን ቢያንስ ለግማሽ ሠዓት ስለሌሎች እፀልያለሁ፡፡

49. አሰልቺ በሆነ መንገድ የሆነ ስራ ለመስራት የሚጓዙትን ሰዎች የተሻለውን መንገድ ማሣየት ያረካኛል፡፡

50. አንድ ጠቃሚ አገልግሎትን ለቤተክርሲቲያን እንዲያገለግሉ ሰዎችን ማበረታታት አይከብደኝም፡፡

51. ቤቴን ለአንዳንድ ድግሶችና ማህበራዊ ፕሮግራሞች መስጠት ደስ ይለኛል፡፡

52. የማንም ምሥጋናና ሙገሳ ሳልጠብቅ ነገሮችን በጊዜው በመሥራት እረካለሁ፤ ደግሞም ይሳካልኛል፡፡

53. ወሳኝ የሆኑ ተልዕኮዎችን ለሰዎች አሣልፎ መስጠት አይከብደኝም፡፡

54. ሌሎች ሰዎች ለመለየት የተቸገሩባቸውን ውስብስብ የሆኑ መንፈሳዊ ፅንሰ-ሃሳቦችን ትክክል ይሁኑ አይሁኑ የመለየት ብቃት ይታይብኛል፡፡

55. ሌሎች የማይደፍሩዋቸውን ሥራዎች ደፍሮ የመጀመርና ዳር የማድረስ ልምድ አለኝ፡፡

56. በኳየር ውስጥ ሁነኛ ሥፍራ ይገቼ መዘመር እንደምችል አምናለሁ፡፡

57. አብዝተው በልሳን መፀለይ በሚወዱ ጉባኤ መካከል ማምለክ አይረብሸኝም፡፡

58. በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚታይ ተአምራት ለማድረግ ጌታ ተጠቅሞብኛል፡፡

59. ለቤተክርስቲያን  የማስጌጥ ሥራዎችንና ፖስተሮች መሥራት ደስ ይለኛል፡፡

60. በኔ እምነት ጌታ ብዙዎችን ሲፈውስ አይቻለሁ፡፡

61. ጌታ ከሚያስፈልገኝ በላይ ብር በማገኝበት ጥበብ ባርኮኛል፤ እኔም ለእግዚአብሔር ሥራ በልግሥና መስጠትን ተለማምጃለሁ፡፡

62. በዙሪያዬ ላሉ የተጎዱ ሰዎች ራሴን ጎድቼም ቢሆን የምችለውን ማድረግ ያረካኛል፡፡

63. ሰዎች ግራ ሲገባቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለማወቅ ምክር ሲጠይቁኝ ብዙ ጊዜ ያጋጥመኛል፡፡

64. ለአንዳንድ ጥያቄ መልስ ለማግኘት የተለያዩ ምንጮችን መፈተሽና ስለነገሩ በጥልቀት መረዳት ያረካኛል፡፡

65. ቅዱሳን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መምከር ያስደስተኛል፡፡ ይህንንም የማደርገው ሳልኮንናቸው ነው፡፡

66. በቃሉ ዙሪያ የማስተምረውን ትምህርት ሰዎች ይወዱልኛል፡፡

67. ያለኝን ትርፍ ጊዜ ሌሎችን ለማገልገል መጠቀም ያስደስተኛል፡፡

68. ብዙ ቅዱሳን የምሰጣቸውን ምክር ያለምንም ቅሬታ ይቀበሉኛል፡፡

69. በማያውቁኝ ሰዎች ዘንድ ወንጌልን መስበክ እመኛለሁ፡፡

70. ሰዎች ማድረግ የሚገባቸውን ያውቁ ዘንድ ከእግዚአብሔር ቃል ፈልፍዬ መልእክት የማምጣት ሸክም አለኝ፡፡
71. በማገኘው ዕድል ሁሉ የማያምኑትን ወንጌል የመንገር ማስተዋልና ሸክም አለኝ፡፡
72. ፀሎት አንድ ክርስቲያን ሊያደርገው የሚገባ ዋና ነገር እንደሆነ አምናለሁ፡፡
73. ፅሑፍ መፃፍን፣ ቀለም መቀባትንና ጋርደን ማስዋብን የመሳሰሉ ነገሮችን ለቤተክርስቲያን ማድረግ ያስደስተኛል፡፡
74. ለአንድ ዓላማ ሰዎችን ማስተባበርና መምራት አያስቸግረኝም፡፡
75. የግል ቤቴን ለእንግዶችና ለአዳዲስ አማኞች መክፈት ያረካኛል፡፡
76. መሸፈን ያለበትን ትንሽ የሚሰራ ክፈተት ሳይ ጊዜ ሳልወስድ መፍትሄውን ማፈላለግ ይቀናኛል፡፡
77. በሌሎች ቅዱሳን ላይ ያለውን የፀጋ ሥጦታ ለመለየት አልቸገርም፤ ውጤታማ እንዲሆኑም ማበረታት ደስ ይለኛል፡፡
78. እውነተኛውን ከስህተት መለየት ያቃታቸውን ሰዎች ለምክር ወደኔ ይመጣሉ፡፡
79. በጨላለመው ሰዓትም ቢሆን በእግዚአብሔር መታመን አይከብደኝም፡፡
80. መዘመር እወዳለሁ ሰዎችም ጥሩ ድምፅ እንዳለኝ ይነግሩኛል፡፡
81. ቅዱሳን በልሳን ሲናገሩ መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውን ትርጉም ያቀብለኛል፡፡
82. እግዚአብሔር የማይቻሉ ነገሮችን እለውጥ ዘንድ ፀሎቴን እንደባረከው ይሰማኛል፡፡
83. የተቸገሩ ሰዎችን በችግሮቻቸው መድረስ ያረካኛል፡፡
84. በነፍስም በሥጋም ለታመሙ ሰዎች መጸለይ ደስ ይለኛል፡፡
85. ሌሎች እረዳ ዘንድ ኑሮዬን ብጎዳ እንኳን አይቆጨኝም፤ እርካታ ስለሚሰጠኝ፡፡
86. ሥራ የሌላቸውን ሰዎችና የቤት ኪራይ መክፈል ያቃታቸውን ሰዎች ሳይ አያስችለኝም፤ የምችለውን ማድረግ እንዳለብኝም ይሰማኛል፡፡
87. ጌታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መርሆችን ለዕለታዊ የሕይወት ገጠመኞች እንዳውል ብዙ ጊዜ ይረዳኛል፡፡
88. ጥልቅ የሚባሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች በራሴ ለመረዳት ጌታ ብዙ ጊዜ ይረዳኛል፡፡
89. ሰዎች ለሌሎች የማይነግሩዋቸውን ሚስጥራት ከኔ ጋር ለማውራት አይቸገሩም፡፡
90. አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ለሌሎች ለመናገር በማደርገው ዝግጅት ይሳካልኛል፤ አንዳንዴ ለራሴም ይደንቀኛል፡፡
91. ከሰዎች ጋር አብሮ መሥራት ደስ ይለኛል፤ ሰዎች ለጌታ መሆን የሚችሉትን እንዲሆኑ መርዳት ያረካኛል፡፡
92. በሌሎች አገሮች ሣይቀር እንደ መንፈሣዊ ሥልጣን የምታይ ሰው ነኝ፡፡

93. በውጭ ሃገራት ወንጌልን የመስበክ ሸክም አለኝ፡፡
94. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋዎችን ለወቅታዊ ጉዳዮች ማዋል አልቸገርም፡፡
95. ለማያምኑ ጌታን መመስከርና ጌታን እንዲቀበሉ ማበረታት በውስጤ ተቀምጣል፡፡
96. ስለሌሎች የምፀልያቸውን ፀሎቶቼን ጌታ ብዙ ጊዜ ሰምቶልኛል፡፡
97. የማንንም ሙገሣ ሣልጠብቅ ሌሎችን መርዳት ያስደስተኛል፡፡
98. ሰዎች ሃሳቤን ያከብሩልኛል የምላቸውንም ለማድረግ አይከብዳቸውም፡፡
99. በቤቴ እንግዶችን ማስተናገድ እንደ አገልግሎት የምቆጥር ሰው ነኝ፡፡
100. ሰዎችን በችግሮቻቸው መርዳትና መድረስ እንደሚያረካኝ ሌላ ነገር አያረካኝም፡፡
101. በአስጨናቂ ሁኔታ ውስጥም ሆኜ እጅግ ጠቃሚ ውሳኔዎችን ለመወሰን አልቸገርም፡፡
102. አንድ ሰው በመንፈስ ሆኖ ሲናገርና የእግዚአብሄርን ክብር ሲያመጣ በቀላሉ ይገባኛል፡፡
103. እምነቴን በፀሎት እለማመደዋለሁ፤ እግዚአብሄርም በአስደናቂ ሁኔታ ፀሎቴን ሲመልስ አይቻለሁ፡፡
104. እግዚአብሄር በመዘምራን ውስጥ በዝማሬ መልዕክት እንዳስተላልፍ ይጠቀምብኛል ብዬ አምናለሁ፡፡
105. እኔ በልሳን ተናግሬ ሌሎች የተናገርኩትን ሲተረጉሙ ገጥሞኝ ያውቃል፡፡
106. እግዚአብሄር ለክብሩ ተዓምራትን በኔ ሲሠራ አይቻለሁ፡፡
107. ሰዎች የዕደ-ጥበብ ሥጦታ እንዳለኝ ይናገራሉ፡፡
108. ሰዎች ሲታመሙ እንድፀልይላቸው ይጠይቁኛል፡፡
109. ለአንዳንድ ሰዎች ብር ስሰጥ ብድራትን አልጠብቅም፤ የምሰጠውም እንደተቸገረ ለማምንበት
110. ሰዎች ዞር ብለው ከማያዩዋች የተቸገሩ ሰዎች ጋር መዋል ደስ ይለኛል፡፡ ለማንኛውም ሰው ያለልዩነት ነው፡፡
111. ሰዎች ያልኳቸውን ለማድረግ አይቸገሩም፤እንዲያውም የሰጠኋቸውን ምክር በሌላ ጊዜ የሚያስታውሱ አሉ፡፡
112. ሰዎች በምነግራቸው የእግዚአብሔር ቃል መረዳት ሲነኩና በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው ተግባራዊ ሲያደርጓቸው አያለሁ፡፡
113. ተስፋ የቆረጡትን ሰዎች ማጽናናት ደስ ይለኛል፤እንዲያውም እነሱን ሳጽናና ሌሎች ሥራዎቼን የምረሣበት ጊዜ አለ፡፡
114. ለዕለታዊ ኑሮ የሚበጁ ሰፋፊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ለብዙዎች መናገር የምችልበት ዕድል ሳገኝ ልቤ ሐሴት ያደርጋል፡፡
115. የደከሙና ጌታን የተዉ ክርስቲያኖችን ወደ ጌታ እንዲመለሱ ጥረት ማድረግ ያስደስተኛል፡፡
116. አብያተክርስቲያናት በሌሉበት አካባቢ ወንጌል መስበክና አብያተክርስቲያናትን ማቋቋም ያስደስተኛል፡፡
117. የዘር መድልዎ ወይም የተለየ ባህልና አኗኗር ያላቸውን ሰዎች ያለመቀበል ስሜት በውስጤ የለም፤እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችንም ለመቀበል አልቸገርም፡፡

118. ቃሉን በምናገርበት ጊዜ የጌታ ባርኮት ኃይልና ቅባት በውስጤ ሲያልፍ ይሰማኛል፡፡
119. ክርስቶስን ላልተቀበሉ ሰዎች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ድነትን እንዲያገኙ ትልቅ ጥማት አለኝ፡፡
120. በቤተክርስቲያኔ ውስጥ ያለኝ የምወደው አገልግሎት ፀሎት ነው፤ ለእርሱ በርካታ ጊዜዎችን አጠፋለሁ፡፡

# የመንፈሳዊ ስጦታ መለያ ነጥብ ማስቀመጫ ገፅ

በህይወትህ እውነት የሆነውን ዐ.ነገር ከ 0-4 ያለውን አንድ ዋጋ ምረጥ

**0 – በጭራሽ አይደለም**
**1 – በጥቂቱ**
**2 – በመጠኑ**
**3 – በብዙ**
**4 - በብርቱ**

| መልሶች | | | | | ጠቅላላ | ተራ | ስጦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | 25. | 49. | 73. | 97. | | ሀ | |
| 2. | 26. | 50. | 74. | 98. | | ለ | |
| 3. | 27. | 51. | 75. | 99. | | ሐ | |
| 4. | 28. | 52. | 76. | 100. | | መ | |
| 5. | 29. | 53. | 77. | 101. | | ሠ | |
| 6. | 30. | 54. | 78. | 102. | | ረ | |
| 7. | 31. | 55. | 79. | 103. | | ሰ | |
| 8. | 32. | 56. | 80. | 104. | | ሸ | |
| 9. | 33. | 57. | 81. | 105. | | ቀ | |
| 10. | 34. | 58. | 82. | 106. | | በ | |
| 11. | 35. | 59. | 83. | 107. | | ተ | |
| 12. | 36. | 60. | 84. | 108. | | ቸ | |
| 13. | 37. | 61. | 85. | 109. | | ኀ | |
| 14. | 38. | 62. | 86. | 110. | | ነ | |
| 15. | 39. | 63. | 87. | 111. | | ኘ | |
| 16. | 40. | 64. | 88. | 112. | | አ | |
| 17. | 41. | 65. | 89. | 113. | | ከ | |
| 18. | 42. | 66. | 90. | 114. | | ኸ | |
| 19. | 43. | 67. | 91. | 115. | | ወ | |
| 20. | 44. | 68. | 92. | 116. | | ዐ | |
| 21. | 45. | 69. | 93. | 117. | | ዘ | |
| 22. | 46. | 70. | 94. | 118. | | ዠ | |
| 23. | 47. | 71. | 95. | 119. | | የ | |
| 24. | 48. | 72. | 96. | 120. | | ደ | |

# ዋና ዋና ስጦታዎች

ሀ. እርዳታ

ለ. እንግዳ መቀበል

ሐ. ማስተዳደር

መ. እምነት

ሠ. ልሳናት

ረ. የእደጥበብ ሙያ

ሰ. መስጠት

ሸ. የጥበብ ቃል

ቀ. ማፅናናት

በ. እረኝነት

ተ. ሚሲዮናዊነት

ቸ. ወንጌላዊነት

ኀ. መሪነት

ነ. አገልገሎት

ኘ. መናፍስትን መለየት

አ. ሙዚቃ

ከ. ተአምራትን ማድረግ

ኸ. ፈውስ

ወ. ምህረት ማድረግ

ዐ. የዕውቀት ቃል

ዘ. ማስተማር

ዠ. ኃዋርያትነት

የ. ትንቢት

ደ. ምልጃ

# የስጦታ ምንነት

የሚከተለው የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምንነታቸውን ይጠቁመናል። ይሄ የማይለወጥ ወይም የመጨረሻ ነው ማለት፤ ባይሆንም፣ እነዚህ ትርጉሞችና ደጋፊ ቁጥሮች በመንፈሳዊ ስጦታዎች መጠይቅ ውስጥ ከተገለጹት ስጦታዎች ጋር የሚዛመዱ ናቸው።

ሀ. እርዳታ፡- በሌላኛው የአካል ክፍለ ህይወትና አገልግሎት ውስጥ ችሎታን የማዋል ብቃት ሲሆን ሌሎችን የራሳቸውን የመንፈሳዊ ስጦታዎች ጠቀሜታ እንዲያሳድጉ ያስችላል።

1ቆሮንቶስ 12÷28 ማርቆስ 15÷40-41
የሐዋ.ስራ 9÷36 ሮሜ 16÷1-2

ለ. መሪነት፡- ለወደፊት ካለው ከእግዚአብሔር ዓላማ አኳያ ግቦችን ማስቀመጥና ለእግዚአብሔር ክብር እነዚያን ግቦች ለመፈፀም በፍቃደኝነትና አብረው በመስማማት በመቀናጀትበሚሰሩበት መንገድ ለሌሎች እነዚያን ግቦች የማስተላለፍ ችሎታ።

ሮሜ 12÷8 የሐዋ.ስራ 15÷7-11
1ጢሞቲዎስ 5÷17 ዕብራውያን 13÷17

ሐ. እንግዳ መቀበል - ምግብና ማደሪያ ለሚፈልጉ ሰዎች ክፍት የሆነ ቤትና ሞቅ ያለ አቀባበል የማቅረብ ችሎታ።

1ጴጥሮስ 4÷9 የሐዋ.ስራ 16÷14-15
ሮሜ 12÷9-13 ሮሜ 16÷23 ዕብራውያን 13÷1-2

መ. አገልግሎት፡- ከእግዚአብሔር ስራ ጋር በሚገናኝ ተግባር ውስጥ ያልተሟሉ ፍላጎቶችን የመለየትና እነዚያን ፍላጎቶች ለማሟላትና የሚፈለጉትን ውጤቶች ለመፈፀም እንዲረዳ የተገኙትን ኃብቶች ለመጠቀም የመለየት ችሎታ።

ሮሜ 12÷7 የሐዋ.ስራ 6÷1-7 2ጢሞቲዎስ 1÷16-18

ሠ. ማስተዳደር፡- የአንድ የተለየ የክርስቶስ አካል ክፍል የአሁንና የረጅም ግዜ ግቦችን የመገንዘብና ለእነዛ ግቦች መፈጸም ውጤታማ ዕቅዶችን የመፍጠርና የማስፈፀም ችሎታ።

1ቆሮንቶስ 12÷28 የሐዋ.ስራ 6÷1-7

ረ. መናፍስትን መለየት፡- አንድ የተወሰነ ባህሪይ ወይም ሃሳብ የእግዚአብሔር፣ የሰው፣ ወይም የሰይጣን መሆናቸውን በእርግጠኝነት የማወቅ ችሎታ።

1ቆሮንቶስ 12÷10 የሐዋ.ስራ 5÷1-11 የሐዋ.ስራ 16÷16-18
1ዮሐንስ 4÷1-6

ሰ. እምነት፡- የእግዚአብሔርን ፍቃድና ዓላማ ከተለመደው መንገድ ውጪ በመተማመን የመለየትና አማኞችን የእግዚአብሔርን ተስፋ በንቃት ወደ ሚቀበሉበት የማክነፍ ችሎት።

1ቆሮንቶስ 12÷9 ሮሜ 4÷18-21 ዕብራውያን 11

ሽ. ሙዚቃ፡- በሙዚቃ ሌሎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ መምራት ልዩ ችሎታ፡፡ ንዳንዶች ምናልባት ይህንን በተፈጥሮ እንዳለ ተሰጥኦ ሊመለከተቱ ይችላል፣ ነገር ግን እነዚህም እንዲሁ ከእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፡፡

መዝሙር 98　　　　　መዝሙር 92÷1-4　　　　　1 ዜና 16÷4-7

ቀ. ልሳናት፡- የአንድ ሰው በጭራሽ ባልተማረው/በማያውቀው/ ቋንቋ፣ ነገር ግን መለኮታዊ መልዕክቶችን የመናገር ችሎታ፤ ዓላማው ወንጌል ለማሰራጨት የወንጌል መስሪያ ሆኖ ማገልገል ነው፡፡

1ቆሮንቶስ 12÷10　　　1ቆሮንቶስ 14　　　ማርቆስ 16÷17
የሐዋ.ስራ 2÷1-13　　　የሐዋ.ስራ 10÷44-46　　　የሐዋ.ስራ 19÷1-7

በ. ተአምራትን ማድረግ፡- የተለመዱ የተፈጥሮ ሁኔታዎችን መቀየራቸው በተመልካቾች እስከሚታዩ ኃይለኛ ስራዎችን በመስራትና በነርሱም እግዚአብሔር እንዲደሰት የሰው መካከለኛ ሆኖ የማገልገል ችሎታ፡፡

1ቆሮንቶስ 12÷10-28　　　የሐዋ.ስራ 9÷36-42
የሐዋ.ስራ 20÷7÷12　　　ሮሜ 15÷18-19

ተ. የእደ ጥበብ ሙያ፡- በጥበብና በእጅ ስራ የክርስቶስን አካል ለማገልገልና አምልኮተ እግዚአብሔርን የመጨመር ልዩ ችሎታ፡፡

1 ነገስት 7÷13-15

ቸ. ፈውስ፡- በአንድ ሌላ ሰው አካላዊ ወይም ስሜታዊ ፍላጐት የእግዚብሔር የፈውስ ኃይል በእርሱ እንደሚገለጥበት መካከለኛ ሆኖ የማገልገል ችሎታ፡፡

1ቆሮንቶስ 12÷9-28　　　የሐዋ.ስራ 3÷1-10
የሐዋ.ስራ 5÷12-16　　　የሐዋ.ስራ 9÷32-35

ኃ. መስጠት፡- በነፃነትና በልግስና ለጌታ ስራ ቁሳዊ ኃብትን የማበርከት ችሎታ

ሮሜ 12÷8　　　ማርቆስ 12÷41-44
2ቆሮንቶስ 8÷1-15　　　2ቆሮንቶስ 9÷2-8

ነ. ምህረት ማድረግ፡- በአካላዊ፣ በአዕምሮአዊ ወይም ስሜታዊ ችግር ለሚሰቃይ ሰው ኃዘኑን የመካፈል፣ ርህራሄ የሚሰማውና በክርስቶስ ፍቅር ርህራሄውን ወደ በጐ አድራጐት ስራዎች በመተርጐም ስቃዩን የማስታገስ ችሎታ፡፡

ሮሜ 12÷8　　　ሉቃስ 10÷25-35

ኘ. ጥበብን የመናገር - በበቂ መረጃ በመደገፍ አግባብነት ባለው መንገድ ለተለዩ ጉዳዮች መንፈሳዊ እውነትን የማዛመድና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ትክክለኛ ምርጫዎችን የማድረግ ችሎታ፡፡

1ቆሮንቶስ 12÷8　　የሐዋ.ስራ 17÷16-34　　　ያዕቆብ 3÷13-16
2ጴጥሮስ 3÷15

አ. የዕውቀት ቃል መናገር - ከአካሉ እድገትና ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች የመለየት፣ የመያዝ፣ የማገናዘብና የመለየት ችሎታ፡፡

1ቆሮንቶስ 12÷8　　　የሐዋ.ስራ 5÷1-11　　　ቈላስያስ 2÷2-3

ከ. ማበረታታት፡- ሌሎች ስራቸውን እንዲያጠናቅቁና እግዚአብሔር እነርሱ እንዲሆኑ የሚፈልገውን ሁሉ እንዲሆኑ ለመረዳት በእግዚአብሔር ቃል በማበረታቻ፣ በማፅናኛ፣ በማነቃቂያና በማነሳሻ ቃላት የማገልገል ችሎታ፡፡

| | |
|---|---|
| ሮሜ 12÷8 | የሐዋ.ስራ 14÷22 |
| 1ጢሞቲዎስ 4÷13 | ዕብራውያን 10÷24-25 |

ኸ. ማስተማር፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን በአግባቡ በተቀረጸ አቀራረብ የመጠቀምና ሌሎች ሊማሩ በሚችሉበት መንገድ ለአካሉና ለክፍሎቹ ጤንነትና አገልግሎት አግባብነት ያለውን መረጃ የማስተላለፍ ችሎታ

| | | |
|---|---|---|
| ሮሜ 12÷7 | 1ቆሮንቶስ 12÷28 | |
| የሐዋ.ስራ 18÷24-28 | የሐዋ.ስራ 20÷20-21 | ኤፌሶን 4÷11-14 |

ወ፡ እረኝነት/መጋቢነት፡- ለአንድ ለተወሰነ የአማኞች ቡድን ደህንነት የረጅም ጊዜ የግል ኃላፊነትን የመውሰድ ችሎታ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ኤፌሶን 4÷11-14 | ሕዝቅኤል 34 | |
| ዮሐንስ 10÷1-18 | 1ጢሞቲዎስ 3÷1-7 | 1ጴጥሮስ 5÷1-3 |

ዐ. ሐዋርያነት፡- በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ በተለየ ስልጣን በበርካታ አብያተክርስቲያናት ላይአጠቃላይ መሪ ሆኖ የመቀመጥና የመለማመድ ችሎታ፤ በእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት በድንገት የሚታወቅና የሚደነቅ

| | | |
|---|---|---|
| 1ቆሮንቶስ 12÷28 | የሐዋ.ስራ 15÷1-2 | 2ቆሮንቶስ 12÷12 |
| ገላትያ 2÷7-10 | ኤፌሶን 3÷1-9 | ኤፌሶን 4÷11-14 |

ዘ. ሚሲዮናዊነት፡- እግዚአብሔር ለተወሰኑ የክርስቶስ አካላት በሁለተኛ ባህል ውስጥ የያዙትን ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማገልገል የሰጣቸው ችሎታ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ማቴዎስ 28÷18-20 | የሐዋ.ስራ 1÷8 |
| ኤፌሶን 3÷7-12 | የሐዋ.ስራ 15÷3፣4 |

ዠ. ትንቢት፡- በእውነት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አረጋግጠው ስለ እርሱም አንዳች ነገር ያደረጉ ዘንድ በሰሚዎች ላይ ፅኑ እምነትን የሚያመጣ በመለኮታዊ ቅባት የእግዚአብሔር ቃልን የማወጅ ችሎታ፡፡

| | |
|---|---|
| 1ቆሮንቶስ 12÷10 | የሐዋ.ስራ 2÷37-40 |
| የሐዋ.ስራ 7÷51-54 | 1ቆሮንቶስ 14÷1፣3፣29 |

የ. ወንጌላዊነት፡- ወንጌልን ላላመኑት ወንዶችና ሴቶች የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር እንዲሆኑና የክርስቶስ አካል ኃላፊነት የወሰዱ አካላት እንዲሆኑ ወንጌሉን የመመስከር ችሎታ፡፡

| | |
|---|---|
| ኤፌሶን 4÷11-14 | የሐዋ.ስራ 8÷5-6፣26-40 |
| የሐዋ.ስራ 14÷21 | የሐዋ.ስራ 21÷8 |

ደ. ምልጃ፡- ከአማካኝ ክርስቲያን ከሚጠበቀው በሚበልጥ መጠን በመደበኛው ለረጅም ጊዜ በመጸለይ ለጸሎታቸው ተከታታይና ልዩ መልሶች እያዩ የመጸለይ ችሎታ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ዕብራዊያን 11÷6 | 1ዮሐንስ 5÷14፣15 | ሮሜ 8÷26 |

# መንፈሳዊ ስጦታዎችህን መለየት

መንፈሳዊ ስጦታዎችህን የመለየትን ሂደት ጀምረሃል፡፡ በመጠይቆቹ ለጊዜው የለየሃቸውን ስጦትዎች ስትመለከት፣ የትኛው በእውነት ያንተ እንደሆነና የትኛው ያንተ እንዳልሆነ ለመለየት ሞክር፡፡ ይህንን ለማድረግ ይህንን ባለ አምስት ደረጃ አቀራረብ ተከተል፡፡

1. **የመሆን እድሎችን መርምር፡-** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚናገሩትን ሦስት ዋና ዋና ምዕራፎችን በሙሉ አንብብ፡፡ (1ቆሮንቶስ 12፣ ሮሜ 12፣ ኤፌሶን 4) ወደ ፊት ስትሄድ የምትመለከተው አንድ የተጨበጠ ነገር ይኖርህ ዘንድ፣ ስጦታዎች ምን እንደሆኑ፣ ምን አይነት ባህሪያት እንዳላቸውና በክርስቶስ አካል ውስጥ እንደሚሰሩ ተማር፡፡

2. **የተቻለውን ያህል ስጦታዎችን መሞከር፡-** አሁን ያጠናቀከው የመንፈሳዊ ስጦታዎች ትንታኔ በተለያዩ ስጦታዎች ሙከራ እንድታደርግ ይረዳሃል፡፡ በመለያ ጥያቄዎች ላይ እየሰራህ እያለህ ስሜቶችህ ፣ አጸፋዎችህ እና በስጦታዎች ላይ ያለህ ጠቅላላ አመለካከት ተለክቷል፡፡ አሁን በትንታኔው በትክክል ባገኘሃቸው ስጦታዎች በመቀጠል ሙከራ ማድረግ ያስፈልግሃል፡፡ ይሄ ትንታኔ የገለፀልህን ስጦታዎች አስካልሞከርክ ድረስ፣ ይኑሩህ ወይም አይኖሩህ እንደሆን ለማወቅ አስቸጋሪ ጊዜ ይኖርሃል፡፡ እነዚህን ስጦታዎች እንድትሞክር በሚያስችልህ አንድ የአገልግሎት እንቅስቃሴ ውስጥ ግባ፡፡

3. **ስሜቶችህን መርምር፡-** ምክንያቱም እግዚአብሔር አካሉን በአንድነት ስላስቀመጠ፣ በትክክለኛ ቦታ ውስጥ ስታገለግል እርካታ ይሰማሃል፡፡ ስለሆነም፣ ያለምከውን ልዩ ፀጋ ለመጠቀም ከተደሰትክ ያ ፀጋ እንዳለህ ይሄ ጥሩ ምልክት ነው፡፡ ሆኖም በአንድ በተወሰነ ፀጋ ጋር በተያያዘ ያለውን የአገልግሎት እንቅስቃሴ የማትወድ ከሆነ ያ ፀጋ እንደ ሌለህ ይሄ ጥሩ ምልክት ነው፡፡

4. **ውጤታማነትህን ገምግም፡-** መንፈሳዊ ስጦታዎች ሌሎችን ለመጥቀም የተዘጋጁ በመሆናቸው ምክንያት፣ ስጦታዎችህን ስትጠቀምባቸው አዎንታዊ ውጤቶችን ማየት ይኖርብሃል፡፡ በአንድ ልዩ ስጦታ ስታገለግል ምንም አይነት ውጤት የማይታይ ከሆነ፣ ምናልባት ያ ስጦታ ላይኖርህ ይችላል፡፡ ነገር ግን ደግሞ ተገቢ ሙከራ ስላለደረክለት ወይም ስጦታውን በተዋጣለት መልኩ ለመጠቀም እንድትማር ዝም ብሎ ጊዜ እየወሰደ ሊሆን ይችላል፡፡ ስትገመግም፣ ለራስህና ለጌታ ታማኝ ለመሆን እንድትደፍር ጸልይ፡፡

5. **ከአካሉ ማረጋገጫን ጠብቅ፡-** አንድን ስጦታ ሁሉንም በራስህ መለየት፣ ማሳደግና መጠቀም አትችልም፡፡ ስጦታዎች የአካሉን ሌሎች ክፍሎች ለመገንባት የተሰጡ ናቸው፡፡ ስጦታ ካለህ፣ ሌሎች ክርስቲያኖች ያውቁትና ያረጋግጡልሃል፡፡ አንድ ልዩ ስጦታ እንዳለህ ቢሰማህ ነገር ግን አንድም ሰው ከአንተ ጋር ባይስማማ፣ ራስህን በጥንቃቄ በመመልከት እንደገና ራስህን ልትገመግም ይገባሃል፡፡

## የአሰልጣኝ ቃል መግቢያ ቅፅ

እኔ ________________________ ክርስቶስን እና የርሱን ቤትክርስትያን ለማገልገል እራሴን በእግዚአብሔር ፊት አሰጣለሁ። በእኔ ስር ያሉትንና አለምን በፍቅር ለመድረስ የአገልጋይ መሪነትን አገልግሎት ለመስጠት እፈልጋለሁ።

አድራሻ ________________________________________________________________

________________________________________ ስልክ ቁጥር __________________________________

ለቤተክርስቲያናችን እንደ አሰልጣኝ ከተመደብኩ እራሴን፡-

_____________________ በየቀኑ ለመፀለይ

_____________________ በእምነት እንደ መፅሀፍ ቅዱስ መመሪያ ለመኖር

_____________________መንፈስ ቅዱስ ህይወቴን እንዲቆጣጠር ለመፍቀድ

_____________________ ለጌታ አገልግሎት በመደበኛ አስራት ለማውጣት

_____________________ ለቤተክረስቲያንና ለመሪዎች ታማኝና የተሰጠ ለመሆን

_____________________ የአሰልጣኝ መሪዎች ስብሰባንና የስልጠና ጊዜን በመደበኛ ለመከታተል።

እራሴን ለመስጠት ቃል እገባለሁ

# የምስክር ወረቀት

ይህ የምስክር ወረቀት

ለ፡ ____________________________________________________________

***ለመምራት መማር - የተተኪ መሪ ስልጠና***

በሚገባ ስላጠናቀቁ ተሰጥቷቸዋል።

ቀን ______________________

______________________
አሰልጣኝ